ልሳነ
ኢኮኖሚክስ

# ECONOMIC FOCUS

Bulletin of the Ethiopian Economic Association (EEA)

VOL. 5 NO. 3
June 2003

Economic Focus is published bi-monthly by the Ethiopian Economic Association and partially sponsored by Friedrich Ebert Stiftung of Germany.

## ራዕይ 2020 በኢትዮጵያ

### በዚህ እትም

✓ ከአዘጋጁ

✓ ምን አለምንዐ የት ደረስን? ወዴትስ እያመራን ይሆን? / ከባሕሩ ዘውዴ

✓ What Did We Dream? What Did We Achieve? And Where Are We Heading? / Bahru Zewde

✓ የፕሮፌሰር ባህሩን አይታ ለስማ[illegible] ለውይይት ማጫሪያና ማዳበሪያ የቀረበ [illegible] በፈቃዱ ደገፌ

✓ አብዮት፣ ሌጂቲማሲና [illegible] አበይት ሂደቶችና ራዕይ 2020/ ከሽፈራው በቀለ

✓ ከኢትዮጵያ ረሀብን ለማጥፋት ብሎም ድህነትን ለመቀነስ የተደረገ ጥናት/ ከታደሰ ኃይለሥላሴ

EDITOR-IN-CHIEF

Assefa Admassie

GUEST EDITOR

Befekadu Degefe

EDITORIAL BOARD

Alemayehu Seyoum
Alemu Mekonnen
Eyob Tesfaye
Getachew Asgedom
Getachew Yoseph

Web Postmaster

Metasebia Zelalem

Ethiopian Economic Association (EEA)

All rights reserved.
No part of this publication can be reproduced, stored in a retrieval system or transmitted in any form without a written permission from the Ethiopian Economic Association.



| P. O. BOX | TELEPHONE | FAX | ADDIS ABABA |
|---|---|---|---|
| 34282 | 557459/ 128077 | 5555252 | ETHIOPIA |

E-mail Address: eea@telecom.net.et Website: www.devinet.org/eea

# *Vision 2020 Ethiopia*

*An EEA Forum for Personal Perspectives on Ethiopia's Future*

Policy discussions in Ethiopia have largely focused on contemporary issues facing the country with very little discussion about the future challenges it brings to the economic well being of the country and its people. Although dealing with contemporary issues is necessary, it is crucial that even those issues are discussed in relation to their consequences to future generations. Serious thinking towards developing a coherent vision at least one generation ahead have a number of advantages for society. First, it will enable policy makers to see the forest without being bogged down by the details of the individual trees. This benefit is not only useful for policy makers but equally importantly it is valuable for the whole community to think about the life they are inheriting their children. Secondly, a discussion about the challenges facing future generations is usually less emotional and acrimonious than contemporary issues. This can positively contribute to an improvement in the tone and over all culture of debate on various issues in the country. Third, a discussion about the future in a more coherent manner usually provides a sense of shared destiny in community. It has a tendency to minimize small differences that exist in a community by making the larger picture of a shared future at the forefront of the community's thinking and deliberation. This will certainly contribute to strengthening the sense of belongingness in a community that is crucial for cementing positive nationalism. Fourth, such a discussion will force disciplined thinking about policy issues that is sorely lacking in our country. Finally bringing together some of the personalities in government business, academics, religious leaders, artists, and civil society leaders in one forum to carefully think about the country's future could significantly contribute towards disentangling some of the most complex challenges that we are confronting as a country.

# ECONOMIC FOCUS

VOLUME 5 NUMBER 3
JUNE 2003

## VISION 2020 ETHIOPIA

# ራዕይ 20 በ 20:: ምንነቱና ምክንያቱ

ከአዘጋጁ

የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ራዕይ 20 በ20 በማለት የሰየመውን የውይይት መድረክ በመጀመሩ እጅግ ከፍተኛ ክብርና ኩራት ይሰማዋል:: ይህ መድረክ በአንድ በኩል ማህበሩ ባለፉት 5 ዓመታት ሲያካሄድ የነበረውን የክብ ጠረጴዛ የውይይት መድረክ የሚተካ ሲሆን በሌላ በኩል ግን ፈር ቀዳጅ መድረክ ነው::

አባላቶችና የውይይቱ ተካፋይ የነበሩት እንደሚያስታውሱት የክብ ጠረጴዛ መድረክ ወቅታዊ በሆነ ጉዳይ ላይ በመንግሥት በኩል የጉዳዩ ባለቤት የሆኑትን የፖሊሲ አውጭውንና የወጣውን ፖሊሲ ተግባራዊ የሚያደርገውን አካል በአንድ በኩል፣ ፖሊሲውና የፖሊሲው ተግባራዊነት የሚመለከታቸውን ተጠቃሚዎችን፣ በሌላ በኩል እንዲሁም ለውይይት በተመረጠው ጉዳይና መስክ በምርምርና በጥናት ጥልቅና ሰፊ እውቀት ያለውን ሰው በአወያይነት፤ እንዲሁም የማህበራችንን አባላትና እንግዶችን በተሳታፊነት በመጋበዝ ውይይት ሲያካሄድ ቆይቷል:: ውይይቱም በአዳራሹ በተገኙ ተሳታፊዎች ብቻ እንዳይወሰንና በውይይቱ ተሳታፊ ያልሆኑት የህብረተሰብ አካላትና አባላት እንዲያውቁትና እንዲወያዩበትና በማሰብ ለውይይት የቀረቡት ጽሑፎችና ይህንንም በተመለከተ «ልሳን ኢኮኖሚክስ» በእንግሊዝኛው "Economic Focus" ብለን በሰየምነው መጽሄታችን ሲታተም ቆይቷል::

የመድረኩና የውይይቱ ዓላማ የመርሃግብሩ ተጠቃሚ የሆነው የህብረተሰብ ክፍል በመርሃግብሩ ወይም በመርሃግብሩ አፈጻጸም ምክንያት ያጋጠመውን ችግር ለመርሃግብሩ አመንጭና ወይም አስፈጻሚ ለማሳወቅና ምን ይደረግ ለሚለው ጥያቄ የመስኩ አዋቂ፤ ተጠቃሚዎችና ሌሎችም ከሚያደርጉት ውይይትና ከዚህም ከሚገኘው የሚወጡትን የመፍትሄ ሃሳቦችና የተግባር እመሳከቻችን መንደርደሪያ በማድረግ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ተግቢውን የእርምት እርምጃ ይወስዳሉ የሚል ጠንካራ እምነት በመሰነቅ በከፍተኛ ስሜት የታሰመ፣ የተወጠነና የተዘጋጀ መድረክ ነበር::

ባለፉት አምስት ዓመታት በየሁለት ወሩ አንድ ጊዜ፣ በዓመት 6 ጊዜ በአምስቱ ዓመት 30 ጊዜ በተደረጉ ስብሰባዎች አሳሳቢና አንገብጋቢ በመሆናቸው አስቸኳይ ትኩረትና የእርምት እርምጃ ያስፈልጋቸዋል ተብሎ በታመነባቸው 30 ጉዳዮች ላይ ውይይት ተደርጓል:: በነዚህም ውይይቶች ተጠቃሚዎች ያጋጠሟቸውን ችግሮችና መፍትሄዎችን ለመርሃግብር አመንጭዎችና ለአስፈጻሚው አካላት ግልፕና አሳማኝ በሆነ መልክ ቀርቧል::

ማህበሩ የውይይቱን 6ኛ ዓመት ፕሮግራም ሲያስብ በዚህ የውይይት መድረክ የተደረገውን ጥረትና የተገኘውን ውጤት ገምግሟል:: ከግምገማው የተደረሰበት መደምደሚያ "ተግባርና ው ጤት" ያልተገናኙ መሆናቸው ነው:: በየጊዜው የተደረጉት ውይይቶች የችግሮችን መጠን፣ በኢኮኖሚውና በህብረተሰቡ ላይ ያደረሱትን ጉዳት ያመላከቱ ሲሆን በመንግሥት በኩል ግን እነዚያን ችግሮች ለማስወገድ ጥረት አለመደረጉን አረጋግጠዋል:: በመሆኑም የ6ኛውም ዓመት ዕቅድ የሚያተኩረው ቀደም ሲል በነበሩና ውይይት በተደረገባቸው ችግሮች እንደገና መወያየት ወይም በሌላ መተካት የግድ ነበር::

ምን ይደረግ? የሚተካስ ከሆነ በምን የሚሉ ጭብጦች ሲዳሰሱ የተነሣው ጥ ያቄ እስከዛሬ የተደረጉት የእርምት ጥረቶች ለምን ፍሬያማ አልሆኑም የሚለው ጭብጥም ተመርምሯል:: ከዚህም የተገኘው መልስ አገራችን ሰፊና ጠ ለቅ ባለ የችግር ማጥ ውስጥ መሆንዋ፣ ህዝብም ኑሮውን ለመለወጥና ሁኔታዎችን ለማሻሻል ብዙም ጥረት እንደማያደርግ፣

በአንፃሩም ተስፋ የመቁረጥ አዝማሚያ እንደሚታይበት በመንገዘቡ እስከዛሬ የተደረገው ጥረት የአባይን በጭልፋ ሙከራ አስመስሎታል::

ከእነዚህ ግኝቶች በመነሣት አገሪቷ ያለችበትን አሳሳቢ ሁኔታ በመገንዘብና ሕዝቡም ሁኔታዎችን ለመለወጥና ኑሮውን ለማሻሻል የሚያደርገውን ለዘብተኛ ጥረት በመረዳት የተስፋ መቁረጡ በብሩህ ተስፋ መተካት እንዳለበት፣ ይህንንም ተስፋ እውን ለማድረግም የአስተሳሰብ ለውጥና የማሰብ ድፍረት አማራጭ የሌለው መሆኑን በመረዳት ለዚህ ይሆናል የተፈለገውን ውጤት ያመጣል በማለት ነው ማህበራችን ይህን የራዕይ 20 በ 20ን የውይይት መድረክ የጀመረው::

የውይይት መድረኩ "ራዕይ 20 በ 20" የተባለበት ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩትም አንደኛው መጪውን ጥርት ባለ እይታ የማየት ችሎታን ለማዳበር ነው:: በተለይም ትኩረት የሚደረግበት ጭብጥ «ኢትዮጵያ ከ 20 ዓመት በኋላ አሁን ባለው ሁኔታ ብትቀጥል የት ትደርሳለች? እንዴት ሆና ልናያት እንፈልጋለን? ይህንን ምኞት እውን ለማድረግ ከዛሬ ጀምሮ ምን መደረግ አለበት?» የሚሉ ጥያቄዎችን መቃኘት ነው::

ከዚህም ሌላ ለነዚህና ከነዚህም ጋር ተዛምች ለሆኑ ጭብጦች የመፍትሔ ሐሳቦችና የተግባር መርሐግብሮች መመንጨት ያለባቸው የችግሩ ሰለባ ከሆነው ህዝብ መሆኑን አስምሮበታል:: ስለዚህም ለችግሮቻችን መፍቻ ተጠ ያቂው የመንግሥት አካላት ሳይሆኑ ወይም ከመንግስት እርዳታ ሳይጠበቅ እያንዳንዱ ግለሰብ በመወያየትና አቋም በመውሰድ ላይ ህይወቱን ለመለወጥ ኃላፊነት ወስዶ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ እንዳለበት የሚያመላክት ነው::

አቀራረቡም

ሀ/ ለውይይት መነሻ የሚሆን ኃሳብ ማቅረብ፣ በቀረበው ኃሳብ ላይ አስተያየት የሚሰጡ ተሳታፊዎችን መጋበዝ ናቸው::

ለ/ ወይይቱን ለማስጀመርና የተለያዩ ኃሳቦችን ለማጫር የሚችሉ ሰዎች ለውይይት መነሻ በቀረበው ጹሑፍ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግና

ሐ/ የመድረኩ ዓላማ ኃሳቦች እንዲፈልቁና መላው ሕዝብ እንዲወያይበት ማድረግ በመሆኑ ይህንንም ለማስቻል ወይይቱን በሬድዮ ( ከተቻለም በቴሌቪዥን) የሚሠራጭበትን ሁኔታ ማዘጋጀት ነው::

እዚህ ላይ በአጽንኦት መገለጽ ያለበት የውይይቱ አላማ መንግሥትንና የመንግሥት ባለሥልጣናትን መጠየቅ፣ መተቸትና በኃላፊነት የመያዝ ሳይሆን አገሪትዋ የሚያጋጥሟትን ችግሮች ህዝቡ እርስበርሱ ተወያይቶ፣ የመፍትሔ ሐሳቦችን የመፍጠርና ለነዚህም ተግባራዊነት ተገቢውን ጥረት የማድረግ ባህል እንዲያዳብር መርዳት ነው:: ችግር በመጣ ቁጥር እጅን አጣጥፎ መንግስትን መለመንና ፈጣሪንና መማለድ መፍትሄ ሊሆኑ አይችሉም:: የመንግሥትና የፈጣሪ እርዳታ የህዝብን ጥረት የሚያግዝ እንጂ የሚተካ አለመሆኑን መረዳት የግድ ይሏል::

ውይይቱን የሚጀመረው በፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ የውይይት ኃሳብ አቅራቢነት ነው:: ይህንን የመድረኩ መክፈቻ የመረጥንበትም ጉዳይ ዛሬ ላለንበት የተስፋ መቁረጥ፣ የሽሽት፣ የድህነት ወዘተ ... ሁኔታ ታሪካዊ መሠረቶችን ለማየትና ቀደም ካለው ተሞክሮአችንም ለመማርና ለመጪዎችም ውይይቶች ጽኑ መሠ ረት መጣል ነው::

ለዚህም መሠረቱ ሕዝብ በራሱና በአገሩ ጉዳይ መ ወያየት አለበት:: በውይይቱ የደረሰባቸውን ፋይዳዎችም መሪዎቻችን ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው:: የምንኖረው የራሳችንን ራዕይ መሆን አለበት::

የራዕይ 20 በ20 አላማም ሕዝብ ይህንን የማድረግ ችሎታ ለማዳበር የመቀስቀሻ፣ የማሳያና የማስቻያ መድረክ እንዲሆን ነው::

በፈቃዱ ደገፌ

# ምን አለምን? የት ደረስን? ወዴትስ እያመራን ይሆን?

ከባሕሩ ዘውዴ
የታሪክ ፕሮፌሰር

## መግቢያ

የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር ትልቅ የቤት ሥራ ሰጥቶናል:: የወደፊት የአገራችንን አቅጣጫ መተለም:: ያለንበትን ሁኔታ በቅጡ ለመረዳት እንኳን በእጅጉ በተቸገርንበት ወቅት ደግሞ ይህንን ማድረጉ ቀላል ነገር አይደለም:: ማንኛውም ይህንን የሚሞክር ሰው ከ20 ዓመት በኋላ ሳይሆን ባምስት ዓመት ውስጥ፣ ወይም ከዚያም ባነሰ ጊዜ፣ ግምቶቹ ሁሉ ፉርሽ ሆነው እንዳይገኙበት መስጋቱ አይቀርም::

ይህም አላግባብ አይደለም:: በሕይወታችን ውስጥ ስንት ያልጠበቅናቸውና ያላለምናቸው ክስተቶች አጋጥመውናል? ግማሽ ምዕት ዓመት ያስቆጠረው የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በወራት ውስጥ ተንዶ በአዲስ የፖለቲካ ሥርዓት ይተካል ብሎ ማን ገመተ? የሶቪየት ኅብረት መንግሥት ፈርሶ ዓለም ባንድ ኃያል መንግሥት መዳፍ ስር ትወድቃለች ብሎ ማን አሰበ? እያንዳንዱን አባወራ መቆጣጠር የሚችል የሥልጣን መረብ መዘርጋት የቻለውና በተለይ በአብዮት በዓል ሰልፍ ጊዜ ሰማይና ምድርን የሚዳኝ የሚመስለው ደርግ እንደዚህ እንደዋዛ ይገረሰሳል ብሎ ማን አሰመ? እንዲያ እጅና ጓንት ሆነው ደርግን የገረሰሱት ኢሕአዴግና ሻዕቢያ ከግማሽ አሠርት ዓመታት ብዙም ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሆድና ጀርባ ሆነው ሁለቱን ሕዝቦች ታይቶ ወዳልታወቀ ጦርነት ያመሩታል ብሎ ማን ተነበየ? አሥራ ሰባት ዓመታት በትግል ቃል ኪዳን ተሳስረው የነበሩ የሕወሓት ታጋዮች ሁለት ቦታ ተከፍለው የድርጅታቸው ሕልውናም አጠራጣሪ ሁኔታ ውስጥ ይገባል ብሎ ማን ደፍሮ መናገር ይችል ነበር?

ስለሆነም የመረጥኩት መንገድ በድፍረት የወደፊቱን አቅጣጫ ለመተንበይ ከመሞከር ይልቅ፣ ታሪክን መሠረት በማድረግ ያለፈውን ሂደታችንን፣ የደረስንበትን ሁኔታና የወደፊት አዝማሚያችንን መቃኘት ነው:: በርእሱ እንደተጠቆመውም ጽሑፌን በሶስት ዓቢይ ክፍሎች ለማቅረብ መርጫለሁ:: በመጀመርያው ክፍል ያለፉት ትውልዶች (የኛን ትውልድ ጨምሮ) ምን አለሙ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እሞክራለሁ:: በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ሕልማቸው ሰመረ ወይስ ቅዠት ሆኖ ቀረ የሚለውን ጥያቄ ከምንገኝበት ሁኔታ ጋር በማዛመድ ለማየት ጥረት አደርጋለሁ:: በሦስተኛውና የመጨረሻው ክፍል ደግሞ በሁለቱ ቀደምት ግኝቶች ላይ በመመሥረት ካለፈው ምን እንማራለን ወደፊትስ ወደለመረ ሕይወት እንዴት ልንሸጋገር እንችላለን የሚለውን ከበድ ያለ ርእስ ለመመልከት እሞክራለሁ::

እንዲህ ያለ ትንታኔ ባገሪቱ ታሪካዊና ነባራዊ ሁኔታ ላይ ብቻ ሊመሠረት እንደማይችል ከወዲሁ ግልፅ ሊሆን ይገባል:: ዓለም አቀፍ ክስተቶችና አህጉራዊ በተለይም አካባባዊ ሂደቶች የራሳቸውን ድርሻ አበርክተዋል፣ ያበረክታሉም:: የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ለዓመታት ሊጋሩ የነበረውን የአሜሪካን መንግሥት ድጋፍ ማጣቱ ለውድቀቱ የራሱ ድርሻ ነበረው:: ባንፃሩም የሶቪየት መንግስት መውደቅ ለደርግ መገርሰስ ትልቅ አስተዋፅዖ እንደነበረው አሌ የማይባል ሐቅ ነው:: አሁን ባለንበት ወቅትም ዓለም ላይ ጥላውን ያጠላው አዲሱ ግሎባላይዜሽን የኛንም ሕይወት እየተቆጣጠረ ነው:: የዚህ ነፀብራቅ የሆነው የአሜሪካ አምባገነንነትም በነባራዊ ሁኔታውም ሆነ የወደፊት አቅጣጫችን ላይ ጉልህና ዐቢይ ሚና እየተጫወተ ነው:: ወደአገራችን ቀረብ ብንልም በተለይ የኤርትራና የሶማሊያ የወደፊት እድገት ካገራችን ሕይወት ጋር ቀጥተኛ ትስስር ያለው ነው::

ይሁን እንጂ፣ ምንም እንኳ ዓለም አቀፋዊና አካባባዊ ሂደቶች ያላቸው ሚና ባይናቅም፣ ቁልፍ ስፍራውን የሚይዙት አገራዊ ክስተቶች እንደሆኑ ሊሰመርበት የሚገባ ሐቅ

ነው። አፄያዊው መንግሥት የወደቀው በየካቲት 66 ሕዝባዊ ማዕበል ነው። ደርግ የተገረሰሰው በአርነት ትግል ኃይሎች ነው። ወደፊትም የሚከሰቱ ሁኔታዎች፣ የውጭ ኃይሎች ሚና እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከሁሉም በላይ አገር ውስጥ በሚከሰቱ ሁኔታዎች ይሆናል።

## ምን አለምን?

የመጀመሪያው አላሚ ቴዎድሮስ ነበር። ሁላችንም እንደምናውቀው ከዘመናዊ የኢትዮጵያ ነገሥታት እንደ ቴዎድሮስ ለአፄያዊ ሥልጣን ገናናነትና ለሀገር አንድነት ተግቶ የሠራ፣ በሀገሪቱም ኋላቀርነት እጅግ የተቆጨ ንጉሥ የለም። ዘውዱን በዘመነ መሳፍንት ግፊት ከወደቀበት ማንሳትን ከእግዜር የተሰጠው ቅዱስ ተልእኮ አድርጎ ነበር የወሰደው። የተሰነጣጠሩትን የሀበሻ ግዛቶች እንደገና አዋህዶ የመካከለኛውን ዘመን ኃይልና ግርማ ለመመለስ ጣረ። ከሁሉም በላይ የሀገሪቱ ኋላ ቀርነት እንደ እሳት እያንገበገበው ዘመናዊ ሥልጣኔን ለማስረፅ የአውሮፓ መንግሥታትን፣ በተለይም የእንግሊዝን መንግሥት እርዳታ በብርቱ ተማጠነ። ይህን ኋላ ቀርነትም በማያሻማና በማያወላዳ ቋንቋ ነበር የገለጠው። ራሱንም ሕዝቡንም «እውር»፣ «ደንቆሮ»፣ «አህያ» እስከማለት ደርሶ ነበር።

ምንም እንኳ እንደምናውቀውና ዝቅ ብለን በዝርዝር እንደምናየው እሱ ያሰበው ባይሳካለትም፣ በዚህ ጥረቱ ተከታዮቹ ነገሥታት ሊከተሉት የሚገባቸውን ዱካ ትቶላቸው አለፈ። እሱ እራሱ ባቀጣጠለው የለውጥ እሳት ነዶ ቢቀርም፣ ተከታዮቹ ከሱ ጥፋት ተምረው፣ ስልታቸውን አለዝበው የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ በቁ። ምኒልክ አፄያዊ ሥልጣንን ለማደላደል፣ ኃይለ ሥላሴ ዘመናዊ ሥልጣኔን በከፊልም ቢሆን ለማስረፅ በቁ። ይሁንና በነገሥታቱ ስሌት ሥልጣን ማደላደል የመጀመርያውን፣ የሀገር እድገት ደግሞ ሁለተኛውን ደረጃ መያዛቸው ግልፅ ነበር።

ለሀገር እድገት ማለሙ በዘመናዊ ትምህርት የተኰተኰተው ትውልድ እጣ ፈንታ ሆነ። ለዚህ ትውልድ መፈጠርም ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ነገሥታት፣ ምኒልክና ኃይለ ሥላሴ፣ ዋናውን ሚና ተጫውተዋል። ይህን ትውልድ በሁለት ከፍለን ልናየው እንችላለን:- ቅድመ-ኢጣሊያን ወረራና ድኅረ ኢጣሊያን ወረራ። የቅድመ-ወረራው ትውልድ በአብዛኛው ምኒልክና ራስ ተፈሪን (ኃይለ ሥላሴ በአልጋ ወራሽነታቸው ዘመን እንደሚታወቁት) እንደ አጋርና አድባር ሲያያቸው፣ የድኅረ-ወረራው ትውልድ በአርአያነት የወሰደው በአብዛኛው ቴዎድሮስን ነበር። ስለዚህም ነው ስለሱ አያሌ መጻሕፍት የተጻፉት፣ አያሌ ተውኔቶች የተደረሱት፣ አያሌ ግጥሞች የተቀኙት። የፈረስ ስሙ ሳይቀር ከአብዮት በፊት ለኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር መጽሔት፣ ከአብዮት በኋላ ደግሞ ለግዙፍ የወታደር ማሰልጠኛ ካምፕ ስያሜ አገልግሏል። እንደምናውቀው ኢሕአዴግም ወደ መሃል አገር የተሸጋገረበትን ዐቢይ ዘመቻ «ዘመቻ ቴዎድሮስ» ብሎ ሰይሞታል።

ከቅድመ-ወረራ ምሁራን መካከል ለቴዎድሮስ የተለየ አድናቆት የነበረው የምሁራኑ ቁንጮ ሊባል የሚችለው ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ነበር። «አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ» በተሰኘው መጽሐፉ የሚከተሉት የአድናቆትና የቁጭት ቃላት ይገኛሉ።

> *ያ ቋረኛ ንጉሥ ተበጣጥሰው የነበሩትን ያበሻን መንግሥት ክፍሎች በሰላው ጕራዴው ቀጥቅጦ አዋደደው። ሕዝቡንም ከካህናትና ከሹሞች ቀምበር አርነት ሊያወጣ አገር በጀ ብሎ አወጀ፤ ትምሕርትንም ሊከፍት ተከራከረ። እንግዲ ሆይ በዚህ ጥረቱ ምን ተጠቀመ ይመስልሃል፤ በመላው ሕዝብ በካህናትና በሹሞች ተመክሮ ተነሳበት፤ አሳበደውም። በመጨረሻም ለባዕድ አሳልፎ ሰጠው በገዛ እጁም ሞተ። አእምሮ የሌለው ሕዝብና ልጁ ጠቃሚውን አይወድም። የቴዎድሮስ አሳብ ግን አልተፈጸመም እንጂ አልሞተም። አባ ታጠቅ ራሱ ቢከፋው የማይረሳውን አሳብ ተክሎ ሞተ።*

ቴዎድሮስ የፈነጠቀውና የሃያኛው መቶ ዓመት ምሁራን ያዳበሩት የለውጥ ሕልም ሦስት ዋና ዋና ገፅታዎች ነበሩት። እነርሱም ሥርዓታዊ አስተዳደር መዘርጋት፣ እርሶ አደሩን የምርቱ ባለቤት በማድረግ የገጠሪቱ ኢትዮጵያን ሕይወት መቀየርና፣ ፍትሕና እኩልነትን ማስፈን ነበሩ።

«ሥርዓት» የሚለው ቃል በተለይ በመጀመሪያው የለውጥ እንቅስቃሴ ምዕራፍ ጉልህ ሥፍራ ነበረው። ቴዎድሮስ ራሱ በመቅደላ አምባ ላይ የሕይወቱ ፍፃሜ ሲቃረብ ለወራሪው ጦር መሪ ለጀኔራል ናፒየር በጻፈው ኑዛዜ-መሰል ደብዳቤ «ያገሬ ሕዝብ ገብር ስራት ግባ ብየ ብለው እምቢ ብሎ ተጣላኝ። እናንተ ግን በስራት በተገዛ ሰው አቸነፋችሁኝ» በማለት የሸንፈቱን ምክንያት በቁጭት ተናግሯል። ገብረ ሕይወት

ባይከዳኝም የሥርዓታዊ አስተዳደርን አስፈላጊነት እንደሚከተለው በአጽንኦት ገልፆታል፡፡

*አእምሮ የሌለው ሕዝብ ሥራት የለውም፡፡ ሥራት የሌለው ሕዝብም የደለደለ ኃይል የለውም፡፡ የኃይል ምንጭ ሥራት ነው እንጅ የሠራዊት ብዛት አይደለም፡፡ ሥራት ከሌለው ሰፊ መንግሥት ይልቅ በሕግ የምትኖር ትንሽ ከተማ ሞያ ትሠራለች፡፡*

ሥርዓታዊ አስተዳደር ሲባል፣ ከሁሉም በላይ ገዥም ተገዥም የሚዳኙበትና የሚያከብሩት ደንብ ማለት ነው፡፡ ይህም ሕግንና ሕገ-መንግሥትን ያጠቃልላል፡፡ በተለይም ኃያላኑንም ደቂቃኑንም የሚዳኝ ሕገ-መንግሥትን የማርቀቁ ጥረት በሃያኛው መቶ ዓመት ባገራችን በተደጋጋሚ የታየ ክስተት ነው፡፡ በፅንሱ የተጨናገፈውን የእንዳልካቸው ዘመን ሕገ-መንግሥት ጨምሮ አምስት ሕገ-መንግሥቶች ታይተዋል፡፡ - ሁለቱ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት፣ ሦስተኛው በአብዮቱ መጀመሪያ ወራት፣ አራተኛው በዘመነ ደርግ፣ አምስተኛው በዘመነ ኢሕአዴግ፡፡

ሁለተኛው ዐቢይ ትልም የሀገሪቱ የጀርባ አጥንት የሆነው ገበሬ ጥሮ ግሮ የሚያገኘው ምርት ዋና ተጠቃሚ እንዲሆንና በተጓዳኝም ድህነትን ከኢትዮጵያ ምድር ለማጥፋት ነበር፡፡ በዚህ ረገድ የቅድመ-ወረራ ምሁራን የገበሬውን ብሶት ብሶታቸው አድርገው፣ መከራውንና ሰቆቃውን በሰላ ብዕራቸው ገልፀውታል፡፡ ገባሩ የሚደርስበትን እንግልትና ብዝበዛም በሰኑ በመቃወም ሥርዓት ያለው የግብር ሲስቴም እንዲመሠረት አበክረው ጠይቀዋል፡፡ በዘመኑ ይታተም የነበረው <u>ብርሃንና ሰላም</u> ጋዜጣ በእንዲህ ዓይነቱ ጽሑፎች የተሞላ ነው፡፡ ከምሁራኑ አንዱ የገባሩን የሰቆቃ ኑሮ አጥንት ድረስ በሚሰማ ቋንቋ ከገለፀው በኋላ «ይኸ ደህ ደሀው ገባር የሚለቁ፣ ከየት አገር ይሆን የፈለቀበቱ በሚል መሠረታዊ የሕልውና ጥያቄ ደምድሞታል፡፡

የድኅረ-ወረራ ምሁራንም ይህን ብሶት በማስተጋባት «መሬት ላራሹ» በማለት ጉዳዩን አብዮታዊ ፈር አስይዘውታል፡፡ በኢትዮጵያ የለውጥ ታሪክ ቁልፍ ሚና የተጫወተው ይህ መፈክር፣ መጀመርያ በተወረወረበት በ1957 ዓ.ም. የቀድሞ ምሁራን በፅኑ የታገሉት የገባር ሥራት እየከሰመ ነበር፡፡ በቦታው ግን በተለይ በደቡቡ የሀገሪቱ ክፍል አያሌ ገበሬዎች ለጭሰኝነት ተዳርገው ከላባቸው ፍሬ ከእርቦ እስከ ግማሽ ድረስ ለባለመሬቱ ለመገበር ተገደው ነበር፡፡ የመፈክሩ እንድምታም ምርትን ብቻ ሳይሆን ማምረቻውን መሬቱንም ለአምራቹ ለማድረግ ነበር፡፡

ሦስተኛው ትልም ፍትሕና እኩልነትን ለማስፈን ነበር፡፡ ይህ በተለይ የሃይማኖትና የብሔረሰብ ጭቆና ላይ ያነጣጠረ ነበር፡፡ የቅድመ-ወረራ ምሁራን ዋና ዒላማ የሃይማኖት እኩልነትን ማስፈን፣ መንግሥትን ከሃይማኖት መነጠል ሲሆን፣ ለብሔረሰብ እኩልነት መታገል ቀርቶ ብዙዎቹ የብሔረሰብ ጭቆና መኖሩንም በውል መገንዘባቸው አጠራጣሪ ነበር፡፡ ባንፃሩ የድኅረ-ወረራ ምሁራን በተለይም የተማሪው ንቅናቄ ዐቢይ ዓላማ የብሔረሰብ ጭቆናን አስወግዶ አሁን ተደጋግሞ እንደምንሰማው «በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተች ኢትዮጵያን መገንባት» ነበር፡፡

## የት ደረስን?

ተከታታይ ትውልዶች ላገራቸው ያለሙላት በግርድፉ ከላይ የተዳሰሰውን ሲመስል፣ ቀጥለን ልንመልሰው የሚገባን ጥያቄ ትልሙ ምን ያህል ሰመረ? የሚለው ነው፡፡ ካልሰመረስ ምን ላይ ስሕተት ተሠራ? ምን አጋጣሚዎች ሳትን? ምን ላይ ፈር ለቀቅን? ምን ላይ ባቡሩ ሐዲዱን ሳተ?

ከመጀመርያው አላሚ ከቴዎድሮስ ብንጀምር ሕልሙ ውብ ሲሆን ሕልሙን እውን ለማድረግ የመረጠው መንገድ ግን የተሳሳተ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ገብረ ሕይወት እንዳለው ቴዎድሮስ ሕዝቡን ቀጥቅጦ ለማዋደድ ነበር የጣረው፡፡ ከማስረዳትና ከማግባባት ይልቅ ሰይፍን ነበር የመረጠው፡፡ እጅና እግሩን የተቆረጠው፣ ቤት ተዘግቶበት የተቃጠለው፣ ከገደል አፋፍ የተወረወረው ሕዝብ ቁጥሩ ቀላል አልነበረም፡፡ ቃሉ ያኔ አይታወቅም እንጂ ቴዎድሮስ ዓላማውን ለመተርጎም እንቅፋት በሆነበት ወገን ላይ ሁሉ ቀይ ሽብር ነበር ያወጀው፡፡ በዚህም ሁኔታ ሕዝብ ቢያምፅበትና ቢያሳብደው አይገርምም፡፡

የቴዎድሮስ ሌላው ችግር ዘመናዊ ሥልጣኔን በኢትዮጵያ ለማስፈን የፈለገው የውጭ አጋር ኃይል አለመገኘቱ ነበር፡፡ በተለይ እንግሊዞችን ቢማፀናቸውም፣ (ከራሱ ቋንቋ ለመዋስ) ቢያቆላምጣቸውም ከመጤፍም አልቆጠሩት፡፡ ሌላው ቀርቶ

ለእንግሊዝ ባሕል እንግዳ በሆነ መንገድ ለዓፈው ደብዳቤ እንኳ ደርሶናል የሚል መልስ ነፈጉት:: ይህ ሌላ ያሳበደው ምክንያት ነበር:: ሩቅ ባሉት እንግሊዞች ተናዶም በቅርብ ያሉትን ፈረንጆች በሙሉ አገተ:: በዚህም ውድቀቱን አፋጠነ:: የሚገርመው ነገር ከጥቂት ዓመታት በኋላ ሁኔታዎች ተቀይረው ቴዎድሮስ የዘረጋውን እጅ የናቁት እንግሊዞችም ሆኑ ሌሎች አውሮጳውያን የተከታዮቹን ነገሥታት ቀልብ ለመሳብ የሳሰለ ጥረት ማድረጋቸው ነው:: ከዚያም አልፎ በተለይ ጣሊያኖች ካንዱም ሁለቴ ሀገሪቱን ለመያዝ መጣራቸው ነው::

የሃያኛው መቶ ዓመት ምሁራን የተለሙትን ውጤት ስንመለከት ደግሞ ስኬትም ጉድለትም እናገኛ ለን:: ሥርዓታዊ አስተዳደርን፣ በተለይም ሕገ-መንግስታዊ አገዛዝን ስናይ አምስት ጊዜ የሕገ-መንግስት ባለፀጋ ሆነናል:: ይሁንና በሕዝባዊ አመፅ ተፀንሶ በጥቂት ወራት ውስጥ የጨነገፈውን የ1966 ሕገ-መንግስት ወደ ጎን ትተን ሌሎቹን ስናጤን ሁለት ባሕርያት ይጋራሉ:: አንደኛው ሁሉም ከታች የመነጩ ሳይሆን ከላይ የተደነገጉ፣ የሕዝብና የመንግስት ቃል ኪዳን ሳይሆኑ የድል አድራጊዎች ቻርተሮች መሆናቸው ነው:: ሁለተኛው ደግሞ በተለይ መብትን በተመለከተ ቃልና አፈፃፀም ሁልጊዜ አለመጣጣማቸው ነው:: በሕገ-መንግስት የተረጋገጡ መብቶች በተግባር ሲሸሩ ይታያሉ::

በዚህ ረገድ ከ1983 ወዲህ የታየው ለውጥ ብዙ አበረታች ገፅታዎች ያሉት ነው:: የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት ሕዝቡን ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ መብት አረጋግጦለታል:: ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ሕዝቡ (በተለይ የአዲስ አበባ ሕዝብ) ሐሳቡን በነፃነት መግለፅ ችሏል:: የግል ጋዜጦች መበራከት የመንግሥትን የሚዲያ ሞኖፖሊ በመጠኑም ቢሆን ሰብሮታል:: መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የሲቪክ ማኅበረሰብ ድርጅቶች መስፋፋት ከመንግሥት ውጪ ሳገርና ለወገን ለመሥራት ዕድል ከፍቷል:: ይሁን እንጂ በየጊዜው የሚሰማው የመብት ረገጣ አቤቱታ ይህን ብሩኅ ተስፋ አደብዝዞታል:: በግሉ ፕሬስ ላይ በየጊዜው ከሚደርሰው ጥቃት ባሻገር፣ በቅርቡ የሚታየው አዝማሚያ ከፕሬሱም ባሻገር ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎችን የሚያቅብ ይመስላል::

የሥርዓታዊ አስተዳደር ሁኔታን ስናጠቃልል አንድ ልንገነዘበው የሚገባ ነገር አለ:: ይኸውም ከሕገ-መንግሥት በታች ሕጎች እንዳሉ ነው:: በዚህ ረገድ ትልቁ ውጤት የተመዘገበው በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ነው:: ይኸውም እስካሁንም የምንገለገልባቸው የፍትሐ ብሔር፣ የወንጀለኛና የንግድ ሕጎች መደንገጋቸው ነው:: እነዚህ ሕጎች ከሕገ-መንግሥቶቻችን የበለጠ ጽናትና ዘላቂነት አሳይተዋል:: ለመለወጥ የተደረገ ሙከራ ቢኖር በተለይ በዘመነ ደርግ ጭቆናን ለማጠናከር በተከታታይ ይወጡ የነበሩት ልዩ የወንጀለኛ ሕጎች ናቸው::

አርሶ አደሩን የምርቱና የመሬቱ ባለቤት በማድረግስ በኩል ምን ውጤት ታየ? የቀድሞ ምሁራን ጨኸት ነባራዊ ሁኔታ ሲፈቅድ ምላሽ አግኝቶ የገባር ሥርዓት ከአብዮት በፊት ከሞላ ጎደል ከሰመ:: የ«መሬት ላራሹ» ጥያቄ ደግሞ ሥር-ነቀል በሆነው የ1967 የመሬት አዋጅ መልስ ያገኘ መሰለ:: መሰለ እንጅ እውን አልሆነም:: ምክንያቱም የገጠርን መሬት የሕዝብ (ማለትም የመንግሥት) ያደረገው አዋጅ አርሶ አደሩን ሙሉ ነፃነት ሊሰጠው ስላልቻለ ነው:: እንዲያውም ከቀድሞው ባለመሬትና መልከኛ ባልተናነሰ ሁኔታ የሚያዘውና የሚዳኘው የገበሬ ማኅበር በላዩ ላይ ጫነበት:: እንኳን የመሬት ባለቤት ሊሆን ሰብሉንም በፈለገው ገበያና ያዋጣኛል በሚለው ዋጋ ለመሸጥ ተከለከለ:: ይህ ሁኔታ ለደርግ ውድቀት አንዱ ምክንያት ቢሆንም፣ ከዚያም በኋላ ቢሆን አርሶ አደሩ የመሬቱ ሙሉ ባለቤት ለሆን አልቻለም:: ስለዚህ የመሬት ላራሹ ጥያቄ ሐዲዱን የሳተ ባቡር ሆኗል ሊባል ይችላል::

በዚህ ረገድ ምን ያህል ትልማችን ግቡ እንዳልመታ የምንረዳው ሀገራችን በተደጋጋሚ ለአስከፊ ረሀብ መጋለጧ ነው:: እንዲያውም ረሀብ በዓለም የኢትዮጵያ ዋና መታወቂያዋ ሆኗል ማለት ይቻላል:: የረሀቡ ክፋትና ስፋትም ከዘመን ዘመን፣ ከመንግሥት መንግሥት እየጨመረ ነው የመጣው:: የሚገርመው ነገር የገጠሩን ኑሮ የማሻሻል እቅዱ በተራቀቀና ጥረቱ በጨመረ ቁጥር የረሀቡ ክፋትና ስፋት እያደገ መሄዱ ነው:: የ1977ቱ ረሀብ የ1965ቱን ቀልድ እንዳስመሰለው ሁሉ አሁን አፍጦ የመጣብን የረሀብ አደጋ ደግሞ የ1977ቱን የሚያስንቅ ይመስላል:: የገጠሩም ኅብረተሰብ የተደጋጋሚ ረሀብ ሰለባ እየሆነ እንኳን ለሀገሪቱ ሊተርፍ ራሱንም መቻል አቅቶታል::

ጊዜ እየጠበቀ የሚከሰተው ረሀብ የገጠሩን አሳሳቢ ሁኔታ አጉልቶ በየወቅቱ ያውጣው እንጂ የረሀቡ መሠረት የሆነው ድህነት ነባራዊ ሁኔታ ሆኖ ቀርቷል:: የገጠሪቱ ኢትዮጵያ ድኅነት ቀድሞም ያለ ሲሆን አሁን ደግሞ እየጎላ የመጣው የከተማ ውስጥ ድኅነት ነው:: ኢትዮጵያ በዓለም ካሉት

ከመጨረሻዎቹ ደሀ ሀገሮች የምትመደብ መሆኗ ገሀድ ሆኗል:: በ20ኛው መቶ ዓመት መጀመርያ ላይ ኢትዮጵያውያን ምሁራን የአፍሪቃ ጃፓን እንድትሆን የተመኙላት ኢትዮጵያ የድህነትና የረሀብ ተምሳሌት ሆናለች:: ይህ ሁኔታም ስለገጠር ልማት እስካሁን መንግሥታት የተከተሉትን ስሌት እንደገና መመርመር እንደሚያስፈልግ ግልፅ አድርጎታል::

የሃይማኖትና የብሔረ-ሰብን እኩልነት በተመለከተም ውጤቱ ድብልቅ ነው ማለት ይቻላል:: ነባር የሆነው የእስልምና ሃይማኖት ከ1967 ጀምሮ ደረጃ በደረጃ የሚገባውን እውቅናና ክብር እያገኘ መጥቷል:: ይሁን እንጂ በክርስቲያኑ በኩል አሁንስ በዛ በሙስሊሙ ወገን ደግሞ ገና ምን አገኘንና የሚሉ ተቃራኒ አስተያየቶች ይስተዋላሉ:: ካንድ የታሪክ አጋጣሚ በስተቀር (በግራኝ አህመድ ጦርነት ወቅት) ለዘመናት ተቻችለውና ተከባብረው የቆዩት ሁለት አንጋፋ ሃይማኖቶች ወደ ግጭት ጎዳና እንዳያመሩ በሁለቱም በኩል ጥበብና ትዕግስት የተመላበት አመራር የሚጠይቅበት ጊዜ ደርሰናል:: ከረር ያለ የፕሮቴስታንት እምነት በሚከተሉት በተለምዶ ጴንጤ በሚባሉትና በኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች መካከል እየተባባሰ የመጣው ፍጥጫም ሌላ የስጋት ምንጭ ነው:: እንጂ በመደብ፣ አሁን ደግሞ በብሔረሰብ ስትታመስ የቆየችው ኢትዮጵያ የወደፊት እጣፈንታዋ ከነዚህ ሁሉ የከፋው የሃይማኖት ጦርነት እንዳይሆን የብዙ ተመልካቾች ስጋት ነው::

በአሁኑ ወቅት ከሁሉም በላይ አወዛጋቢ እየሆነ የመጣው የብሔረ-ሰቦችን እኩልነት ለማረጋገጥ የተነደፈው ስልት ጉዳይ ነው:: በ1960ዎቹ እንደዋዛ የተወረወረው «የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል» የሚለው መፈክር አሁን ሕገ-መንግስታዊ እውቅና አግኝቷል:: ይሁን እንጂ በዚህ ዙሪያ ሦስት ተፃራሪ አቋሞች ሲንፀባረቁ ይታያል:: የሕገ-መንግሥቱ አርቃቂ በሆነው በመንግሥት ወገን የኢትዮጵያ የብሔር ብሔረ-ሰብ ጥያቄ አስተማማኝና የማያዳግም መፍትኄ አገኘ የሚል አቋም አለ:: ባንዳንድ ተቃዋሚ የብሔረሰብ አርነት ንቅናቄዎች ዘንድ ግን የብሔር ብሔረ ሰብ ጭቆና ባዲስ መልክና ሽፋን ቀጥሏል የሚል ነው:: በሦስተኛው ወገን የተያዘው አቋም ደግሞ ይህ ሙከራ ኢትዮጵያን ይበታትናታል የሚል ስጋትን ያዘለ ነው::

ሁኔታውን በጥሞና ስንመለከተው ድብልቅና ውስብስብ የሆነ ስዕል እናገኛለን:: እርግጥ ነው ብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋቸውን ለማበልፀግና ባሕላቸውን ለማዳበር ከመቼውም የበለጠ አንፃራዊ ነፃነት አግኝተዋል ለማለት ይቻላል:: ነገር ግን ከትግራይና ምናልባትም ከአማራ ክልል በስተቀር የክልሉች አስተዳደራዊ ነፃነት አጠያያቂ እየሆነ መጥቷል:: አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ግንባር ባገሪቱ ፍፁም የበላይነትን እስካገኘ ድረስ ክልሎች ከማዕከላዊ መንግሥት ነፃ ሊሆኑ ይችላሉ ማለት ዘበት ነው:: የፖለቲካ ሥልጣን የራሱ የሆነ ሉጂክ አለው፤ በቃል ኪዳንና ሕገ-መንግሥታዊ አንቀፅ ብቻ አይታሰርም::

ስለሆነም ቀድሞ ሲብላላ ቆይቶ ከ1983 ጀምሮ ባገሪቱ የተንሰራፋው የብሔር-ብሔረ ሰብ ፖለቲካ በአያሌ የታሪክ ምፀቶች የታጀበ ክስተት ሆኗል:: የነሌኒንን ስሌት ተከትሎ የብሔር ብሔረ-ሰቦችን እስከመገንጠል ያለ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ዕውቅና የመስጠት መርህ መጀመርያ በተማሪው ንቅናቄ ስር የሰደደው የኤርትራውያንን የመብት ትግል በመደገፍ ከሙሉ ነፃነት በመለስ መፍትኄ ለማግኘት እንደነበረ በወቅቱ የተማሪዎች ንቅናቄ የተሳተፍን ሁሉ የምናውቀው ነው:: ይሁንና ይህ ያልተቆጠበ ድጋፍ የተሰጣቸው የኤርትራ ግንባሮች የኛ ጉዳይ የብሔር ጥያቄ ሳይሆን የቅኝ ግዛት ነው፤ ትግላችንም የነፃነት ትግል ነው ሲሉ ስሌቱ ከሽፏል:: ግንባሮቹ፣ በተለይ ሻዕቢያ፣ ከዚያም አልፈው ነባሩን ታሪክ ፈፅሞ በመካድ፣ የሁለቱን ሕዝቦች ታሪካዊ ትስስርና ኤርትራውያን ላንድነት ያደረጉትን ትግል በመካድ፤ ኢትዮጵያና ኤርትራ በታሪክ ምንም የሚያገናኛቸው ነገር ኖሮ አያውቅም፣ ኤርትራውያን በሙሉ ከ1933 ዓ.ም. ጀምሮ ለነፃነት ሲታገሉ ነው የቆዩት የሚል አዲስ ታሪክ በመፍጠር እነሱም አምነውበት ዓለምንም ለማሳመን በቁ::

በዚህ ሁሉ መሐል ኤርትራ ነፃ ስትሆን የኤኮኖሚ መሠረቷ ምን ይሆናል? ከኢትዮጵያ ጋር የሚኖራት ግንኙነትስ ምን መልክ ይዛል? በኢትዮጵያ ምድር ባንፃራዊ ምቾት የሚኖሩት አያሌ ኤርትራውያን ዕጣ-ፈንታስ ምን ይሆናል? የሁለቱ ሀገሮች ድንበርስ ምን መልክ ይዛል? የሚሉት ዐቢይ ጥያቄዎች በትግሉ ወቅትም ሆነ ከድል በኋላ በሚገባ ሳይጤኑ አሁን የምንገኝበት ውስብስብ ሁኔታ ውስጥ ከተውናል::

በሌላ ወገን ደግሞ የኤርትራ ነፃነትም ሆነ የብሔር ብሔረ ሰቦች እስከ መገንጠል ድረስ ያለ መብት የትግራይን ሕዝብ እወክላለሁ

በሚል ድርጅት አስተናጋጅነት መታወጁ ሌላ የታሪክ ምፀት ነው:: ይህም በሁለት ምክንያቶች ነው:: አንደኛው ከማንም ብሔር ብሔረ ሰብ የበለጠ ከኤርትራ በተለይም ከደጋው ክፍል ጋር የተሳሰሩትና የዚህንም ክፍል ኢትዮጵያዊነት የሚያውቁና የሚረዱ የትግራይ ተወላጆች በመሆናቸው ነው:: ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በቁጥር አናሳ የሆነ ብሔረሰብ ባንድ በኩል ማዕከላዊ የፖለቲካ ሥልጣን እንደያዘ ለመቆየት ፈልጎ በሌላ ወገን ደግሞ የብሔር ብሔረ ሰቦችን ያልተገደበ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ማወጁ ነው::

ሦስተኛው የታሪክ ምፀት የኤርትራ ግንባሮችን የትግል ስልት በመገልበጥ (የፈጠራ ታሪኩም ሳይቀር) የኦሮሞ ሕዝብ መብት የሚረጋገጠው ከኢትዮጵያ በመገንጠል ነው የሚል ንቅናቄ ማቆጥቆጡ ነው:: ምፀቱ በሁለት መልክ ነው:: ባንድ ወገን የኦሮሞ ብሔር ከሌላ ማንኛውም ብሔር ብሔረ ሰብ በሕዝብ ቁጥር የበለጠ መሆኑ እየታወቀ ማዕከላዊ ሥልጣንን ከመጨበጥ ይልቅ የመገንጠልን መስመር መከተሉ ነው:: በሌላ መልኩ ደግሞ የኦሮሞ ብሔር ከማንኛውም ብሔር ይልቅ ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረ ሰቦች በታሪክ፣ ባሕልና ማኅበራዊ ኑሮ የተሳሰረ በመሆኑ ነው:: በዚህ ረገድ በቅርቡ የኦሮሞን ሕዝብ መብት በኢትዮጵያ ክልል ለማረጋገጥ መታገል አለብን የሚል አዝማሚያ መታየቱ አበረታች ሁኔታ ነው::

አራተኛውና የመጨረሻው የታሪክ ምፀት ደግሞ ከሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች ይልቅ የዘመናት ጭቆናና በደል የደረሰበት የደቡብ ሕዝብ ሁኔታ ነው:: ባለፉት ምዕት ዓመታት መሬቱን ከመነጠቅ አንስቶ በጅምላ በባርነት እስከመጋዝ ድረስ የተለያዩ ግፎች ተፈፅመውበታል:: ይሁን እንጅ ባዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት የተረጋገጠለት ራስን በራስ የማስተዳደር መብት አሽሚና አወዛጋቢ ሆኗል:: ማንኛውንም ብሔር ብሔረሰብ የማይወክል፣ የማናቸውንም ቋንቋ ወይም ታሪክ የማያንፀባርቅ ክልላዊ አስተዳደር ከመዘርጋቱም በላይ የርስ በርስ ግጭትም ሆነ የታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ጥቃት የሰፈነበት አካባቢ ሆኗል:: ይህም ሆኖ (ይህ ደግሞ የምፀቱ ሌላ ገፅታ መሆኑ ነው) ከማንኛውም ክልልና አካባቢ ባላነሰ፣ አንዳንዴም በበለጠ፣ እኳኋን የኢትዮጵያዊነት ስሜት የሚታይበት ይኸው የደቡብ ክልል ነው::

ለነገሩ የክልላዊ አስተዳደር መዋቅር አርቲፊሽያልነት በደቡብ ክልል ብቻ የተወሰነ አይደለም:: የአማራና የኦሮምያ ክልሎችንም ብናይ፣ ከሞላ ጐደል አንድ ዓይነት ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦችን ከማጠቃለላቸው በስተቀር፣ ታሪካዊ መሠረትም ሆነ አስተዳደራዊ rationality እንደሌላቸው እንገነዘባለን:: በመካከለኛው ዘመን ደቡብ ወሎና ሰሜን ሸዋ አካባቢ አማራ የሚባል ግዛት ከመኖሩ በስተቀር፣ ከዚያ በኋላ በዚህ ስም የሚጠራ አስተዳደራዊ ክልል ኖሮ አያውቅም:: ሁላችንም እንደምናውቀው የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ታሪካዊ ግዛቶች ጐንደር፣ ጎጃም፣ ወሎ፣ ሸዋ... ወዘተ ነበሩ:: እንደዚሁ ሁሉ ኦሮሞዎችን ሁሉ የሚያጠቃልል ኦሮምያ የሚባል እንዲህ እንዳሁኑ የተንሰራፋ ግዛት መቼም ኖሮ አያውቅም:: የነበሩት አርሲ፣ ባሌ፣ ሲዳ፣ ጅማ ... ወዘተ ነበሩ:: በአስተዳደር ረገድም ከአንኮበር እስከ አርማጭሆ የሚገኙትን አማሮችም ሆነ ከጊኒር እስከ ጊዳሚ ያሉትን ኦሮሞዎች ባንድ ክልላዊ መንግሥት ለማስተዳደር መሞከር አመቺ ሊሆን እንደማይችል እሙን ነው::

የነዚህ ምፀታዊ ክስተቶች ሁሉ ማሳረጊያው በሕዝቦች መካከል የታለመው መፈቃቀድ ቀርቶ ከመቼውም የበለጠ ጥርጣሬና ክዚያም አልፎ ጥላቻን መፈጠሩ ነው:: ጥቂት የየብሔረሰቡ አባላት ባገኙት ሥልጣን ተጠቅመው ኑሯቸውን ባመቻቹ፣ ብሔረሰባቸው በሙሉ እንደተሳታፊና ተጠቃሚ የሚወገዝበት ጊዜ መጥቷል:: ከኢትዮጵያውያንም በላይ ኢትዮጵያውያን የሆኑ ሰዎች የታዩባት ኤርትራ ነፃ ከመሆንም አልፋ ከኢትዮጵያ ጋር አዲስ የጦርነት ምዕራፍ ውስጥ ገብታለች:: የኢትዮጵያ መሠረት ልትባል የምትችለው ትግራይ በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ሀገር የሚያፈራርስ ንቅናቄ ምንጭ ሆና ለመታየት በቅታለች:: ከማንም ያላነሰ ኢትዮጵያውያን የሆኑት ኦሮሞዎች ከኢትዮጵያ ጋር የሚያገናኛችሁ ምንም ታሪካዊ ትስስር የለም በሚል እንቅስቃሴ ሲታመሱ ይታያሉ::

ከሕወሓት መከፋፈል ወዲህ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የብሔር ብሔረሰብ ፖለቲካ ውስጣዊ ቅራኔዎች ይበልጥ ገሀድ እየሆኑ መጥተዋል:: በክፍፍሉ ምክንያት የዚህ ፖለቲካ ዋና አራማጅና ተጠቃሚ የነበረው ሕወሓት ከመዳከምም አልፎ እየከሰመ የሚሄድ ይመስላል:: ይህም አሁን እየታየ ያለውን ኢሕአዴግን ወደ ኅብረ-ብሔራዊ ፓርቲ የመለወጥ እንቅስቃሴ ወልዷል:: ፈታችን የተደቀነው ትልቁ ጥያቄ የዚህ እንቅስቃሴ የመጨረሻ ውጤት ምን ይሆናል የሚል ነው:: ለሌሎችም እስካሁን ማዕቀብ ተደርጎባቸው ለነበሩ ኅብረ-ብሔራዊ ፓርቲዎች

አዲስ ዕድል ይከፍታል ወይስ ኢማሌድኅን ወደ ኢሠፓ የቀየረው ሂደት ያመጣውን ዓይነት አምባገነንነት ያስከትላል? የብሔር ብሔረሰቦች መብት በኢትዮጵያዊነት የታረቀበት አስተዳደር ይዘረጋል ወይስ የተማከለን አስተዳደር መልሶ ይጭናል? ይህ የቅርቡ ዓመታት ሂደት የሚፈታው ጥያቄ ይሆናል።

ይህን «የት ደረስን?» የሚለውን ክፍል ከመዝጋታችን በፊት፣ ያመለጡ ዕድሎች ወይም የተሳቱ መንገዶችን ለማመልከት መሞከሩ ከቁጭት ባሻገር የተወሰነ የግንዛቤ ፋይዳ ይኖረዋል ብዬ እገምታለሁ። ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ስንጀምር፣ ያ ዘመን ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ዘመናዊ አስተዳደርና ሥልጣኔ የታየበት ዘመን መሆኑ አያጠያይቅም። ይልቁንም በትምህርት መስፋፋትና የመሠረተ ልማት አውታሮች መዘርጋት (የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ቴሌኮሙኒኬሽን፣ አውራ ጐዳና... ወዘተ) ከፍተኛ ውጤቶች ተመዝግበዋል። ከአብዮት ወዲህ ኢትዮጵያውያን የደረሰባቸው መከራና እንግልትም ያን ዘመን በተለየ ናፍቆት (nostalgia) እንዲመለከቱት አድርጓቸዋል።

ይሁን እንጂ ያ ሥርዓት በሁለት ዐቢይ መስኮች ባሳየው ጉድለት ከነቀፌታ ሊያመልጥ አይችልም። እነዚህም አስተዳደርን ሊበራላይዝ ለማድረግና መለስተኛ እንኳን ሊባል የሚችል የመሬት ይዞታ ማሻሻል ለማምጣት ይህ ነው የሚባል ጥረት ባለማሳየቱ ነው። ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለማረጋገጥ፣ ሥልጣን ያለው ፓርላማና የራሱን ካቢኔ የሚሰይምና የሚመራ ጠቅላይ ሚኒስትር ለመፍቀድ፣ ባጠቃላይም እንደ እንግሊዝና ስካንዲናቪያ አገሮች ለሕገ-መንግሥት ተገዥ የሆነ ንጉሠ ነገሥታዊ ሥርዓት (constitutional monarchy) እንኳን ለመዘርጋት ሳይችል ቀርቷል። በመሬት ይዞታ በኩልም የዘመኑ ፓርላማ ስር-ነቀል የመሬት ይዞታ አዋጅ ሊደነግግ ቀርቶ ሥርዓት ያለው የጭሰኝነት ደንብ ማውጣት አቅቶት አልፏል።

እንዲህ ዓይነት ለውጦች ለማምጣት ካንዴም ሁለቴ አጋጣሚዎች ነበሩ። ከከሸፈው የነመንግሥቱ ንዋይ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ፣ በመክሸፉ ከመኩራራት ይልቅ ከመከሰቱ ትምህርት በመውሰድ በሁለቱም ከላይ የተጠቀሱ ዘርፎች ጠቃሚ የሆኑ የለውጥ እርምጃዎች ለማድረግ በተቻለ ነበር። ከዚያም በኋላ አብዮት ከመፈንዳቱ ሁለት ዓመት በፊት ዓለም ሁሉ እንደጠበቀው ንጉሠ ነገሥቱ የ80ኛው ዓመት የልደት በዓላቸውን የሽግግር ሥርዓት መሠረት መጣያ ባደረጉት ነበር። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የተረፈው ፌሽታ፣ ፈንጠዚያና ባገሪቱ ባንዲራ ቀለሞች የተሸለሙ የመንገድ መብራት አምፖሎች ብቻ ነው። ስለሆነም በእርጋታ ሊመጣ ያልቻለ ለውጥ በሕዝባዊ አመፅ ተረግዞ በወታደራዊ ነፍጥ ታወጀ። ውጤቱም ባብዛኛው ደምና እንባ ሆነ።

ባሁኑ ጊዜ የአብዮቱ ዋና አጋፋሪ የነበረውን የተማሪዎች ንቅናቄ ከመተቸትም አልፎ መኮነን እየተለመደ መጥቷል። ንቅናቄው ብዙ ድክመቶችና ግድፈቶች እንደነበሩት ባይካድም የሥርዓቱ ውጤት መሆኑን መገንዘቡ በጭፍን ከማውገዝ እንድንቆጠብ ይረዳናል። ከድክመቶቹና ግድፈቶቹ ምናልባት ዋነኛው እስካሁንም ደብዛው ያልጠፋው የጽንፈኝነት ባሕል ነው። ይሁን እንጂ ይህ ጽንፈኝነት የመጣው ትርጉም ያለው ለውጥና መሻሻል ባለመታየቱ ነው። አብዮት የሚከሰተው እርባና ያለው ሪፎርም ሲጠፋ ነው። አብዮት የሚፈነዳው መተንፈሻ ቀዳዳ ሲጠፋ ነው።

የአብዮቱ መፈንዳትና የጽንፈኝነት ባሕል መንሠራፋት የእንዳልካቸውን ካቢኔ በማስወገድ ለወታደራዊ አገዛዝ መንገድ ጠረገ። ከዚያም አልፎ አሉ የተባሉት ኅብረ-ብሔራዊ ግራ ኃይሎች (በተለይ ኢሕአፓና መኢሶን) የዚሁ የጽንፈኝነት ባሕል ተገዥ በመሆናቸው ጥቃቅን ልዩነቶቻቸውን ማቻቻል ተስኗቸው ተራ በተራ የደርግ ሰለባና ጭዳ ሆኑ። እነዚህ ግራ ኃይሎች ለኢትዮጵያ ከደርግ የተሻለ አስተዳደር ያመጡላት ነበር ወይ የሚለው ጉዳይ አከራካሪ ሊሆን ይችላል። የማያከራክረው ግን የነሱ መመታት መድረኩን ለብሔራዊ አርነት ግንባሮች አመቻችቶ በመጨረሻም በደርግ መቃብር ላይ አሁን የምንገኝበትን የታሪክ ምዕራፍ መክፈቱ ነው።

በመጨረሻም የኤርትራ ችግር የተፈታበት መንገድ ባለፉት ዓመታት ለደረሰብን ጦርነትና መከራ መንስዔ እንደሆነ ግልፅ እየሆነ መጥቷል። ራሱ ሻዕቢያ በትግል ዘመን ለሬፈረንደም የሰጣቸው አማራጮች ሰፋ ያሉ ሲሆኑ (ማለትም ውኅደት፣ ፌዴሬሽን፣ ወይም ነፃነት) በ1985 ግን «ነፃነት ወይስ ባርነት» የሚለውን ምርጫ-የለሽ መልክ ይዞ ቀርቧል። በወቅቱ የነበረው የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥትም ሬፈረንደሙን ሻዕቢያ በመረጠው መንገድ ከማስፈፀም ባሻገር በኢትዮጵያዊነታቸው የሚያምኑትን ኤርትራውያን መብት ለማስከበርም ሆነ የኢትዮጵያን ዘላቂ ጥቅም ለማረጋገጥ (ለምሳሌ ወደብን በተመለከተ) ምንም ዓይነት እርምጃ ለመውሰድ ፈቃደኛ አልነበረም።

## ወዴትስ እያመራን ይሆን?

ከዚህ በላይ የቀረበው ታሪካዊ ትንታኔ አበረታችና ተስፋ-ሰጭ

እንዳልሆነ ይሰማኛል:: የትንተናው ዓላማ ግን ተስፋ ለማስቆረጥ ሳይሆን ወደፊት ለምናልመው ጉዳና እውነተኛውን መነሻ ለማስጨበጥ ነው:: በኔ ግምት የዚህ ተከታታይ ውይይት ዓላማ ተስፋ ለማስቆረጥ ወይም እንገት ለማስደፋት ሳይሆን፣ አገራችን ከምትገኝበት ውስብስብ ችግር ባሻገር ሊኖር የሚችለውን ብሩኅ ተስፋ ለመፈንጠቅ ነው:: ከድቅድቅ ጨለማ በስተቀር ምንም የማይታየን ከሆነ እንደ ሀገርም እንደ ሕዝብም አለቀልን ማለት ነው:: ጨለማን ለመተንበይ ደግሞ ድርስትም ውይይትም አያስፈልግም:: ከኢትዮጵያ ታሪክ የምንገነዘበው አንድ ሐቅ ቢኖር፣ ካንዴም ሁለቴ አለቀላት፣ ፈረሰች ተብሎ ከተደመደመ በኋላ እንደገና እንዴት እንዳንሰራራችና አዲስ ሕይወት እንደዘራች ነው:: በአክሱም ዘመን ፍፃሜ፣ በ16ኛው መቶ ዓመት፣ በዘመነ መሣፍንትና በዘመናችንም በአብዮቱ ወቅትና በደርግ ውድቀት ጊዜ የታየው ሁኔታ ይኸው ነው:: ይህ እንደገና የማንሰራራት ችሎታ ሀገሪቱ በዘመናት የታሪክ ሂደት ያካበተችው ሰብዓዊና ባሕላዊ እሴቶች ውጤት ይመስለኛል::

መግቢያዬ ላይ እንደጠቀስኩት ከሃያ ዓመት በኋላ የኢትዮጵያ ሁኔታ ይህን ይመስላል ብሎ በድፍረት መናገር ይከብዳል:: ስለዚህ ማንኛውም ራዕይ እስኪተወሰን ደረጃ ምኞት-አዘል መሆኑ የማይቀር ነው:: ይሁንና ራዕዩ ልቅ ምኞት ሆኖ እንዳይቀር ራዕዩን እውን ለማድረግ ምን ምን ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው በሚል ትንተና መታጀብ ይኖርበታል:: የኔም አቀራረብ ይህን ስልት የተከተለ ይሆናል:: ከውይይቱ መድረክ አዘጋጆች የተሰጠን መመሪያም ይህንኑ መንገድ የሚጠቁም ነው::

መሠረቱ እኔ የሚኖረኝ ራዕይ ካለፉት ትውልዶች እምብዛም የተለየ አይደለም:: የሚለይበት ነገር ቢኖር፣ ካለፉት ስሕተቶችና ግድፈቶች በመማር ራዕዩ እውን የሚሆንበትን መንገድ እንዴት እናመቻች እሚለው ነጥብ ላይ ነው:: እንደ እውነቱ ከሆነ እኔ የሚኖረኝ ራዕይ ከሌሎች አያሌ ኢትዮጵያውያን ምኞትና ተስፋም እምብዛም የተለየ አይሆንም ብዬ እገምታለሁ:: በዚህ ረገድ የእውነተኛ ሕገ-መንግሥታዊ አስተዳደር መስፈን አሁንም ትልቁ አጀንዳችን ነው:: ሕገ-መንግሥቱ ከላይ የሚጫን ሳይሆን ከሥር የሚመነጭ፣ በወረቀት ላይ ብቻ የሚቀር ሳይሆን በተግባር የሚተረጎምና የሚከበር እንዲሆን የብዙዎች ምኞት ነው:: የሕገ-መንግሥቱም መመሪያና ዓላማ በማንኛቸውም ቅፅል ያልታጀበ (ሕዝባዊ፣ አብዮታዊ፣ ወዘተ) ዴሞክራሲን ማስፈን መሆን ይኖርበታል:: ዴሞክራሲ ዞሮ ዞሮ አንድና አንድ ነው:: ይኸውም ተራው ሕዝብ ሞግዚት ወይም ወኪል የሚሆንለት ሊቅና ጠቢብ ሳያስፈልገው የመጨረሻው ዳኛና ወሳኝ የሚሆንበት ሥርዓት ነው::

ሁለተኛና ከዚሁ ጋር ተያይዞ፣ ፍትሕና እኩልነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን ማየቱ አሁንም በታላቅ ጉጉት የሚጠበቅ ሁኔታ ነው:: ፍትሕ ሲባልም ከሁሉም በላይ የሕግጋት መሟላት ወይም መራቀቅ ሳይሆን፣ ከመንግሥት ተፅዕኖ ነፃ የሆነ የዳኝነት ሥርዓት መዘርጋት ነው:: እኩልነት ሲባልም ባንድ በኩል በሕግ ፊት ሁሉም ዜጋ እኩል መታየት እንዳለበት ለማስረገጥ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች በእኩልነትና በመከባበር እንዲኖሩ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ነው::

በታሪካዊ ትንታኔዬ ላይ የዚህ የኋለኛው ነጥብ አተረጓጎም ያስከተለውን ችግር ስላተትኩ፣ በምን መልክ ቢታይ ይሻላል በሚለው ነጥብ ላይ አንዳንድ አስተያየቶችን ማከል እፈልጋለሁ:: ኢትዮጵያ ውስጥ የብሔር ብሔረሰብ ጭቆና አልነበረም ብሎ የሚሟገት ሰው ያለ አይመስለኝም:: ቢኖርም የሀገሪቱን ታሪክ በቅጡ ያልተገነዘበ መሆን አለበት:: በተለይ በደቡቡ የሀገሪቱ ክፍል ብሔር ብሔረሰቦች ለሰፋና ለከፋ ጭቆና ተዳርገዋል:: የሰሜኑ አስተዳደር ተጭኖባቸው፣ ቋንቋቸውና ባሕላቸው ተንቋል:: አያሌዎቹ መሬታቸውን ሲነጠቁ አንዳንዶቹ በባርነት ተሸጠዋል:: የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ይህን ሁኔታ በማጋለጥና እንዲወገድም በመታገል ትልቅ አዎንታዊ ሚና ተጫውቷል::

ይሁን እንጂ ለዚህ ችግር የታለመለት መፍትኄ እስካሁን ሲያወዛግበን ቆይቷል:: በብሔር ብሔረሰቦች ላይ የተመሠረተው የፌዴራል ሥርዓት አወቃቀርም በየጊዜው አዳዲስ ችግሮችን እየወለደ ይገኛል:: ኢትዮጵያ በፌዴራል ሥርዓት መተዳደር እንደሚገባት ፅኑ እምነት አለኝ:: በመሠረቱም የተማከለ አስተዳደር በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በሃያኛው መቶ ዓመት ብቻ (ማለትም በአፄ ኃይለ ሥላሴና በደርግ ዘመን) የታየ እንግዳ ሥርዓት ነው:: ይሁን እንጂ ይህ ፌዴራላዊ አወቃቀር ታሪካዊና ኢኮኖሚያዊ መሠረት እንዲኖረውና ለቀልጣፋ አስተዳደርም ምቹ እንዲሆን ያስፈልጋል:: ስለሆነም አወቃቀሩ የሶቪየት ኅብረትን የብሔር ብሔረሰቦችን ፌዴሬሽን ሳይሆን የአሜሪካን ግዛታዊ ፌዴሬሽን ስልት ቢከተል ይመረጣል::

ብሔር ብሔረሰቦች የራሳቸው የአስተዳደር ክልል እንዲመሠርቱና ከዚያም አልፎ ከፈለጋችሁ መገንጠል ትችላላችሁ ብሎ ከማወጅ ባሉበት ማንኛውም የኢትዮጵያ ግዛት ቋንቋቸውና ባሕላቸው የሚከበርበት ስልት ማውጣቱ የተሻለ አማራጭ ሆኖ ይታየኛል:: ምክንያቱም እስካሁን የተሞከረው ክልላዊ አስተዳደር የጥቂት ባለሥልጣኖችንና የወገኖቻቸውን ኑሮ ከማደላደል

አልፎ ለአብዛኛው የክልል ሕዝቦች ያመጣው ፋይዳ እስከዚህም ጎልቶ የሚታይ ባለመሆኑ ነው:: የግዛታዊ ፌዴሬሽንን መሠረት አድርጎም የአፍሪቃ ቀንድ አገራት (ኢትዮጵያ፣ ኤርትራ፣ ጅቡቲና ሶሚሊያ/ሶማሊላንድ) በኮንፌዴሬሽን ሥርዓት ተዋቅረው የሕዝቦቻቸውን መወራረስና የሀገሮቹንም ጂዎግራፊያዊና ታሪካዊ ትስስር የሚያጎለብቱበት ሁኔታ ሲፈጠር ማየት እፈልጋለሁ::

ሦስተኛ፣ በኢኮኖሚው ረገድ እንደ እያሌ ኢትዮጵያውያን ረሀብን ብቻ ሳይሆን ድኅነትንም አስወግደን ገጠሬውም ከተሜውም የተደላደለ ሕይወት የሚኖሩበት ሥርዓት ሲመሠረት ማየት እፈልጋለሁ:: ኢትዮጵያ የሃያኛው መቶ ዓመት መጀመርያ ምሁራኖቻችን እንዳለሙት የአፍሪቃ ጃፓን መሆን እንኳን ቢያቅታት፣ የአፍሪቃ ጭራ ከመሆን ድና፣ ታሪካዊ እሴቶቿና ነባራዊ ሀብቶቿ የሚፈቅዱላትን መሪ ስፍራ ይዛ እንድትገኝ ማየት እፈልጋለሁ:: እነዚያ ምሁራን በፅኑ የታገሉት የገባር ሥርዓት እንደከሰመ፣ አርሶ አደሩም ላይ የተጫነው ሳይሠራ የሚበላ መደብ እንደተገረሰሰ ሁሉ፣ አርሶ አደሩ ከራሱ ጉርስ አልፎ ለሀገርና ለውጭ የሚተርፍ ምርት ሲያመርት ማየት እሻለሁ::

እነዚህ ራዕዮች እውን እንዲሆኑ ግን እያሌ ነባራዊ ሁኔታዎች መመቻቸት ይኖርባቸዋል:: እነዚህን ሁኔታዎች በሦስት ከፍለን ማየት እንችላለን::- ዓለም አቀፍ/ግሎባል፣ አህጉራዊና አካባቢያዊ፣ ሀገራዊ:: ዓለም አቀፉ ሁኔታ ዕድልም አደጋም ያዘለ ነው:: በመጀመርያው ረድፍ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መስፋፋትና የከፈተው የዕድገትና የሥልጣኔ በር ነው:: ይህ ቴክኖሎጂ ባንድ በኩል ዓለም አቀፍ ዕውቀትንና መረጃን ለመቋደስ የሚያስችል አዲስ ዕድል ከፍቶልናል:: በዚያው መጠን ግን አዲስ የባዕድ ተፅዕኖና ቁጥጥር እንዳይጋብዝብን የራሳችንን አቅም ማጎልበት ይጠይቃል::

በሁለተኛው ረድፍ ደግሞ ከሶቪየት ኅብረት መፍረስ ወዲህ የተፈጠረው የአንድ ኃያል መንግሥት መግነን ነው:: በተለይ ጥበብን ያልታደለና በትምክሕት የተወጠረ አመራር ነጩ ቤተ መንግሥት ሲቆጣጥ ምን ዓይነት ጥፋት ሲደርስ እንደሚችል በቅርቡ በኢራቅ ላይ በታወጀው ጦርነት ለማየት በቅተናል:: እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ደሀና ደካማ ሀገሮች ትልቁ አደጋ እንዲህ ያለ መንግሥት ዘፈኔን ካልዘፈናችሁ፣ እስክስታዬን ካልወረዳችሁ እያለ ክብራችውን ከመንካትም አልፎ ማለቂያ ወደሌለው ጦርነትና ውጥረት ውስጥ እንዳያስገባቸው ነው:: በአሜሪካ ዳፋ ኢትዮጵያ ከዐረቦችና ሙስሊሞች ጋር ተጣላች ማለት ከውጭም ከውስጥም በእሳት ስትለበለብ ኖረች ማለት ነው::ስለሆነም የአሜሪካ አምባገነናዊ የበላይነት መገታት በተለይ ድኩማን መንግሥታት በፅኑ የሚታገሉለት ዓላማ ነው:: በዚህ ረገድ የአውሮጳ ኅብረትና የቻይና መጠናከር የኃይል ሚዛኑን ለማስከበርና አሜሪካ አደብ እንድትገዛ ለማድረግ ወሳኝ ጉዳይ ነው::

አዲሱ ዓለም አቀፍ ሥርዓት (The New World Order) እየተባለ የሚሞካሸው የአሜሪካ አምባገነንነት በፖለቲካው መስክ ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚውም ጥላውን ዓለም ላይ አጥልቷል:: በተለይም ሁለቱ የገንዘብ-ነክ ተቋሞች - አይ ኤም ኤፍ እና የዓለም ባንክ - እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ደሀ ሀገሮችን በመዳፋቸው ሥር ለማድረግ ከመቼውም ጊዜ የላቀ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል:: እንዲህ ያሉ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ወጥመዶችን አልፎ የሀገር እድገትና ብልፅግናን ለማምጣት በማዕበል በሚናወጥ ባሕር ላይ መርከብ ነድቶ በሰላም ወደብ መድረስን ያህል ከባድ ነው::የኢኮኖሚ ሊቃውንቶቻችን ለዚህ ጉዞ የሚሆነውን ፕላን (navigation chart) የመንደፍ ታላቅ ኃላፊነት ወድቆባቸዋል::

ሌላው በዓለም አቀፉ ረድፍ አሳሳቢ እየሆነ የመጣው ጉዳይ የአካባቢ አየር ብክለት ነው:: የረሀብ ምንጭ ድርቅ ብቻ ነው ባይባልም ዙሮ ዙሮ ረሀብን ገሀድ የሚያወጣው የድርቅ መከሰት እንደሆነ ተደጋግሞ የታየ ነገር ነው:: ለዚህ ዓለም አቀፍ እየሆነ ለመጣው የድርቅ ክስተት ደግሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣው የአካባቢ አየር ብክለት፣ በተለይም የአዞን ሌየር መሳሳት፣ እንደሆነ ግልፅ እየሆነ መጥቷል:: በዚህም መስክ ቢሆን የቡሽ አስተዳደር ይህን አደጋ ለመቋቋም ታቅዶ የተረቀቀውን የኪዮቶ ስምምነት አልፈርምም በማለት ያሳየው እምቢተኝነት ሌላው የማንአለብኝነቱ ነፀብራቅ ነው:: (ይህን የአየር መዛባት ግሎባል ምንጮች መጠቆሙ ግን እኛው ራሳችን የአየር ንብረታችንን በመንከባከብ ረገድ ያለብንን ኃላፊነት ለማደብዘዝ አለመሆኑ መታወቅ ይኖርበታል:: በተለይ ደኖቻችንን በመንከባከብ ረገድ እስካሁን የታየው ቸልተኝነት እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ ነው::)

በሁለተኛ ደረጃ የኢትዮጵያ የወደፊት ዕድል ከአፍሪቃ አህጉር፣ በተለይም ከአፍሪቃ ቀንድ፣ ዕጣ ፈንታ ጋር በእጅጉ የተሳሰረ ነው:: አህጉራችን ሁላችንም እንደምንገነዘበው በሦስት ዐቢይ መቅሰፍቶች ተወጥራ ተይዛለች - ድኅነት፣ ጦርነትና በሽታ:: ከነፃነት አባቶች ጀምሮ እስካሁን የአፍሪቃ ኅብረት እስከተቋቋመበት ጊዜ ድረስ አህጉራዊም ሆነ ክልላዊ አንድነት ለመመሥረት የሚደረገው ጥረት ሁሉ የነዚህ መቅሰፍቶች ሰለባ ሆኗል:: ይሁንና እነዚህ መቅሰፍቶች ካልተወገዱ፣ እነዚህ ጥረቶች ካልሰመሩ፣ አህጉራችን በዓለም አቀፉ ሥርዓት ውስጥ

ተገቢ ሥፍራዋን ማግኘቷ ይቅርና ከፈጣኑ የእድገት ባቡር ተሽቀንጥራ እንዳትወረወር ያሰጋታል::

ከሁሉም በላይ ለሀገራችን የወደፊት ዕድል አሳሳቢ እየሆነ የመጣው ደግሞ የአፍሪቃ ቀንድ ሁኔታ ነው:: በሶማሌ መንግሥት መፍረስ ምክንያት አካባቢው የታመሰው አልበቃ ብሎ፣ ኢትዮጵያና ኤርትራ ባካባቢው ታይቶ ያልታወቀ አስከፊ ጦርነት ውስጥ ገቡ:: ይህን ዓይነቱ ውጥረት ከቀጠለ፣ የአካባቢው ሀገሮች፣ ካላቸው የኀላ የድኅነትና የበሽታ ችግር ጋር ተዳምሮ፣ አካባቢውን የማያባራ ሰቆቃ ውስጥ እንዳይከተው ያሰጋል:: ከላይ እንደተጠቀሰው፣ የአካባቢው ችግር ዘላቂ መፍትኄ በመከባበርና በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ኮንፌደሬሽን ነው:: የአፋሮችን፣ የሳሆዎችን፣ የሶማሌዎችንና የትግርኛ ተናጋሪዎችን ጂዎግራፊያዊ ስርጭት ስንመለከት እነዚህን አንድ መሠረት ያላቸው ሕዝቦች የከፋፈለው የቅኝ ግዛት አጥር በመጠኑም ቢሆን ገርበብ መደረግ እንዳለበት እንገነዘባለን:: ይህን የኮንፌደሬሽን ራዕይ እውን ለማድረግ፣ ከታሪካዊ ሚናዋ፣ ጂዎግራፊያዊ አቀማመጧና ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብቶቿ አንፃር ኢትዮጵያ የተለየ ኃላፊነት ይጠበቅባታል::

ሀገራችን የተደቀኑባትን ዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊና አካባቢያዊ ችግሮች ለማሸነፍ ግን ከሁሉ በፊት ቤታችንን ማፅዳት ይኖርብናል:: በኔ ግምት ካገራችን ውጭ ካሉ ችግሮች ይበልጥ ይህ በቁጥጥራችን ስር ያለና አስፈላጊውን ጥረት ካደረግንም ለመወጣት የተሻለ ዕድል ያለን ነው:: በዚህ ረገድ ማድረግ ያለብን ጉዳዮች አያሌ ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ እሞክራለሁ::

ከሁሉም በፊት ከአብዮቱ ዘመን (የቅድመ-አብዮቱን ግራ-ዘመም ንቅናቄ ጨምሮ) የወረስነውን የጽንፈኝነትና የመጠፋፋት ባሕል አስወግደን በምትኩ የመቻቻልና የመደማመጥ ባሕል መኮትኮት ይኖርብናል:: ባለፉት ሠላሳ ዓመታት ሀገራችን ያየችው መከራ (ቀይ ሽብርን ጨምሮ) የዚህ የጽንፈኝነት ባሕል ውጤት ነው:: ስለሆነም ሁሉን እውቃለሁ ከማለት የሌሎችንም ሐሳብ ለማዳመጥ ዝግጁ መሆን፣ ሁሉንም ጠቅልዬ ልያዝ ከማለት ለመጋራት መዘጋጀት፣ በተለይም ከሁሉም በላይ በስሙ የምንገዳደልለት ሠፊ ሕዝብ የሚበጀውን አሳምሮ እንደሚያውቅ ተገንዝበን ከሱ መሬት የቆነጠጠ እውቀት ለመማር ዝግጁ መሆን ይኖርብናል::

ሁለተኛ ነገር ለሰው ሀብታችን ልዩ አክብሮትና እንክብካቤ ማሳየት ይኖርብናል:: ባለፉት ሠላሳ ዓመታት በተለይ በተማረው የሰው ሀብታችን ቁማር ስንጫወት ቆይተናል ማለት ይቻላል:: በቀይ ሽብር የረገፉት ብርቅ ልጆች አንስ ብሎ፣ ከዚያ ወዲህ የተረፈው ለእንግልትና ለስደት ተዳርጓል:: በቅርቡ የዓለም አቀፍ ፍልሰት ጽሕፈት ቤት ይፋ እንዳደረገው በምሁራን ፍልሰት ኢትዮጵያ ከአፍሪቃ ቀዳሚውን ሥፍራ ይዛለች:: ለከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቻችን፣ በተለይም ለአንጋፋው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የሚሰጠው ግምት እስካሁን ባለው ሁኔታ ከቀጠለ፣ ይህ ሁኔታ እየከፋ ቢሄድ እንጂ ከቶም ሊሻሻል አይችልም:: ዩኒቨርሲቲው ላለፉት 12 ዓመታት ቃል የተገባለት ራሱን የሚያስተዳድርበት ቻርተር እንደ በረሃ ሚራዥ ሲቀርቡት እየራቀ የሚሄድ ነገር ሆኗል:: በምትኩ ያልተብላሉና ከጥራት ይልቅ ቁጥር ላይ ያተኮሩ የትምህርት ዘይቤዎች ቤተ-ሙከራ እየሆነ ነው:: በ12 ዓመት ውስጥ አምስት ፕሬዚዳንት በማየትም Guinness Book of Records ሳይገባ አይቀርም:: በእንደዚህ ያለ ሁኔታ እንኳን የረጅም ጊዜ የዕድገት አቅጣጫ ለመተለም የዕለት ተዕለት ጉዳዮችንም በቅጡ ለማከናወን ያዳግታል::

ሌላው ከእንክብካቤም ይልቅ ሠፊ ዕድል ሊሰጠው የሚገባው የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ነው:: ባገራችን ታሪክ መንግሥት በግሉ ኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረው ጫና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል:: በአፄያዊ አገዛዝ ዘመንም ቢሆን የመንግሥት ቁጥጥር ያልተለየው ይህ ክፍለ-ኢኮኖሚ፣ በዘመነ ደርግ እስከናካቴው እንዲጠፋ ተደርጎ ነበር:: የግሉ ክፍል ዕድል ከተሰጠው የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ እንዴት ያለ ኢጋዥ ኃይል ሊሆን እንደሚችል በአብዮቱ ዋዜማና አሁንም ከመንግሥት ለውጥ በኋላ በ1980ዎቹ የመጀመርያ ዓመታት ፍንጭ አሳይቷል:: ይሁንና ስር የሰደደው የመንግሥታዊ ቁጥጥር ባሕል አሁንም የግሉ ሴክተር በሙሉ አቅሙና ችሎታው እንዳይሠራ አግዶ ይዞታል:: በሌላ በኩል፣ በደርግ መጨረሻ ዓመታት ያቆጠቆጠው የአየር ባየር ወይም የቶሎ ልክበር ባሕል ሐቀኛና ንፁሕ የንግድ እንቅስቃሴን በብርቱ እየተፈታተነው ይገኛል:: በተጓዳኝም እጅግ አይን-አውጣ እየሆነ የመጣው ሙስና ሌላ ትልቅ ፈተና ነው::

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች መሟላት ለሚተለመው የእድገት አቅጣጫ ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው:: የተማረ የሰው ኃይላችንን ተንከባክቦ መያዝ፣ ለግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ሠፊ ዕድል መስጠት የዕድገታችን መሠረት ነው:: ያም ዕድገት ሊመጣ የሚችለው ለዘመናት የዳከርንበትን፣ ግን የትም ያላደረሰንን፣ በጥቃቅን የገበሬ ማሳዎች ላይ የተመሠረተውን የእርሻ ኢኮኖሚ ትተን ወደ ኢንደስትርያል ኢኮኖሚ በፍጥነት የምንሸጋገርበትን ስልት ስናወጣ ነው:: ከእርሻ ኢኮኖሚው ያገኘነው ቋሚ ድህነትንና ተደጋጋሚ ረሀብን ብቻ ነው::

# What Did We Dream? What Did We Achieve? And Where Are We Heading?

Bahru Zewde

## Introduction

The Ethiopian Economic Association has given us a daunting assignment: to predict the future course of our country? At a time when we find it extremely difficult to determine even our present state, it is far from easy to embark on such an undertaking. Whoever dares to attempt that does so with trepidation, lest his/her predictions turn to prove wrong in five years or even less, let alone in 20 years.

And this is not without reason. How often have we been surprised by unexpected turn of events in our own lifetime? Who would have expected that the Haile Sellasie regime, which had held sway for half a century, would be swept away in a matter of months and be replaced by a new political order? Who would have foreseen the collapse of the Soviet state and the domination of the world by one superpower? Who would have dreamt that the Derg, which had set up a power structure that could control each and every family and that, especially during Revolution Day parades, appeared to be invincible, would be swept away with such ease? Who would have predicted that the EPRDF and EPLF, who fought hand in glove to destroy the Derg, would fall out in less than half a decade and drag the two peoples into a war of unprecedented ferocity? Who would have asserted with confidence that the TPLF, united in struggle and death for seventeen years, would be split in two and the very existence of their organization put in question?

Hence the mode I have chosen in my presentation is not so much to predict the future as to base myself on history and survey our past course, describe our present state and indicate our future directions. As suggested in the title, I have divided my paper into three major parts. In the first section, I shall attempt to answer the question of what past generations (including our own) had dreamt. In the second, I shall make an effort to see, in the light of our present condition, whether our dream has come true or whether it had turned into a nightmare. In the third and last section, I shall tackle the more difficult subject of what, based on the answers to the two earlier questions, we learn from the past and how we can chart a better future.

It should be clear from the outset that such an analysis cannot be based entirely on the country's past and present condition. Global and continental and even more so sub-regional developments have continued and will continue to have their share of influence. The withdrawal of the support of its long time ally, the United States, contributed to the demise of the Haile Sellassie regime. Likewise, it is incontrovertible that the collapse of the Soviet

state had a considerable role in the disintegration of the Derg regime. At present, the new globalization that had cast its shadow over the entire world is controlling our life. American hegemony, which is a reflection of this globalization, is exercising a clear and preponderant role in our present state and our future direction. When we come closer to home, the future fate of Eritrea and Somalia in particular is directly linked to our country's future.

Nevertheless, while the influence of global and regional developments should not be denied, it should be emphasized that national developments play the preponderant role. The imperial regime was swept away by the popular upsurge of February 1974. The Derg disintegrated under the barrage of liberation forces. Likewise, the country's future direction will be determined above all by internal developments.

## What Did We Dream?

The first dreamer was Tewodros. As we all know, of all the modern emperors, he strove hardest for the restoration of imperial power and glory and felt most distressed by the country's backwardness He took the lifting of the crown from the depth to which it had sunk during the *Zamana Masafent* as a divine mission entrusted to him by God. He strove to reunite the fragmented Abyssinian polities and restore the power and majesty of the medieval empire. Above all, he felt anguished by the country's backwardness and ardently sought the support of the European states, particularly that of England, to introduce modern civilization. He was unambiguous in expressing this backwardness, calling himself and his people "blind", "ignorant", "donkey".

As is common knowledge and as we shall see in greater detail below, he failed in his dream. But he left behind an ideal that inspired his successors. Although the fire of change that he lit consumed him, his successors learnt from his mistakes, moderated their style and achieved better results. Menilek managed to consolidate imperial authority while Haile Sellassie succeeded in introducing, even if in modest measure, modern civilization. However, in the thinking of these emperors, national development took second place to the consolidation of imperial power.

It became the destiny of the educated elite to . pire for national development. The two emperors mentioned above, Menilek and Haile Sellassie, played the principal role in the creation of that elite. We can divide those elite into two generations: the pre-Italian invasion and the post-Italian invasion ones. Whilst the pre-invasion generation looked up to Menilek and *Ras* Tafari as patron and ally, the post-invasion generation was inspired above all by Tewodros. That is why so many books and plays were written about him, and so many poems composed. His horse name (Tateq) was adopted as the name of the journal of the Ethiopian Students' Union in Europe before the Revolution while, afterward, it came to be used by the Derg as the name of a huge military training camp. As is well known, EPRDF also used that very name to christen the campaign that catapulted it to the central provinces.

Of the pre-invasion intellectuals, Gabra-Heywat Baykadañ, who could be described as their

leader, was particularly fascinated by Tewodros. We find the following words of admiration and remorse in his booklet entitled "Atse Menilek and Ethiopia":

> That king from Qwara (Tewodros's birthplace) forcibly united with his sharp sword the fragmented components of the Abyssinian state. In order to liberate the people from the yoke of priests and officials, he declared himself lord over all the land; and he struggled to introduce education. Dear Reader! What, do you think, did he get for his trouble? The priests and officials instigated the people against him and drove him mad. Finally, they put him at the mercy of invading forces, and he committed suicide. An ignorant people is like a child: They do not like their benefactors. However, Tewodros's dream may not have been realized; but it did not die. Abba Tataq may have been distressed, but he died leaving behind an enduring idea.

The dream for change first kindled in Tewodros's mind and later developed by the intellectuals of the twentieth century had three major facets. These were: instituting ordered governance, changing the life of rural Ethiopia by making the peasant owner of his produce, and ensuring justice and equality.

The word *ser'at* (equivalent to ordered governance) was prominent in the first chapter of the struggle for change. In a letter-cum-testament that Tewodros wrote to the commander of the invading British force, General Napier, as the former was facing death on his solitary stronghold, Maqdala, he explained with bitterness the cause of his defeat thus: "My countrymen rose against me because I told them to submit to *serat*. You defeated me because you had marshaled a force that respected *ser'at*". Gabre Heywat Baykadañ also underscored the importance of ordered governance in the following words:

> An ignorant people does not have *ser'at*. And a people without *ser'at* has no stable power. The source of power is *ser'at*, not the multitude of an army. A small town governed by law is much better than a big state without *ser'at*.

When one talks of ordered governance (*ser'at*), one has in mind above all rules and regulations that govern and are respected by both the ruler and the ruled. This means essentially laws and constitutions. The drafting of a constitution that governs the mighty and the weak is a phenomenon that has been seen more than once in our country in the twentieth century. If we include the constitution of the Endalkachaw period that was aborted in its embryonic state, we have seen five constitutions - two of them during the imperial regime, the third during the first months of the Revolution, the fourth under the Derg, and the fifth one under EPRDF.

The second principal dream was to see the backbone of the country, the peasant, become the main beneficiary of the product of his toil and at the same time to eradicate poverty from Ethiopia. In this respect, the pre-invasion intellectuals felt the peasant's suffering as their own and described his misery and pain in trenchant language. They opposed ardently the exploitation and suffering of the *gabbar* (as the tribute-paying

peasant was known) and demanded the introduction of an equitable system of taxation. The contemporary weekly, *Berhanena Salam*, is full of such writings. One of those intellectuals, after describing the miserable lot of the *gabbar* in passionate terms, concludes his essay with the following existential question: "These poor people who go by the name of *gabbar*, which country is it that they come from?"

The post-invasion intellectuals echoed this sentiment and gave the whole matter a revolutionary direction by raising the slogan of "Land to the Tiller". When this slogan, which has played such a key role in the country's history of revolutionary change, was thrown out in 1965, the *gabbar* system that the pre-war intellectuals had fought so ardently was disappearing. In its place, particularly in the southern parts of the country, many peasants had been forced into tenancy and were paying from a quarter to half of their produce to the landlord. The thrust of the slogan was to give the producer not only the produce but also the means of production, land.

ፕሮፌሰር ባህሩ እንደገለጡት ቴዎድሮስ፤ ቀደም ሲል የነበሩና መሪዎችና ከሳቸውም በኋላ የመጡት በጎ አሳቢ መሪዎች የነበራቸው ሕዝብን የማበልጸግና ገርን የማሠልጠን ምኞቶች እስከዛሬ እንድም እርምጃ ያልተራመደ መሆኑን ነው። ሥርዓት እየተሻሻለ ሣይሆን እየተበላሸ መሄዱን በኛ እድሜ እንኳን ያየነው ጉዳይ ነው። ጊዜው ሕግና ሥርዓት እየተዛነፉ፤ ወግና ባህል እየተበረዘ የሚሄድበት ዘመን ሆንዋል። ለህዝብ ተስፋ መቁረጥ አንዱና መሠረታዊው ጉዳይ የዚህ የህግ ልዕልና መሟሟትና በየደረጃው የማንአለብኝነት ባህርይ መንገሥ ነው። ሠርቶ ለማግኘትና አግኝቶ ለመክበር እጅግ አስፈላጊ የሆነው የህግ ልእልና ቀደም ሲል እንደነበረው ሁሉ ዛሬም በምኞት ደረጃ ያለ ጉዳይ ነው። ለምን እንዲህ ሆነ? ለማሻሻል ምን መደረግ አለበት የሚለው ጥያቄ መልስ የሚሻውና ተግባራዊ መሆንም ያለበት ነው።

ፕሮፌሰር ባህሩ ያነሱት ሌላው ምኞት የገጠሩና በተለይም የገበሬው ሁኔታ ነው። ገበሬው ዛሬ የሚገኝበት ሁኔታ ቀደም ሲል ከነበረው እምብዛም የተሻሻለ አይመስልም። አሁንም ጥያቄው ለምንና እንዴት ሁኔታውን ለመለወጥ ይቻላል የሚለው ነው። የዚህ ጉዳይ አሳሳቢ የሚሆነው ድህነትን ለመቀነስ የሚደረግ ማንኛ ውም ጥረት ማተኮር ያለበት በገጠሩ አስከፊ ኑሮ ላይ በመሆኑ ነው።

ለ) እንዴት?

ለሃገራቸው ያላቸውን ራእይና ይህንንም የማስገኛ ስልት የዘረዘሩት ፕሮፌሰር ባህሩ ኢትዮጵያና ከዚያም አልፎ ጎረቤቶችዋ በሰላምና ብልጽግና ለመኖር የሚያስችላቸውን በጎና የተቀደሰ ምኞት በማዘላቸው ነው። ሆኖም ግን ይህን በውስጠ-ታዋቂነት ይደረስበታል ብለው ያሰቡት ብልጽግና እንዴት ሊመጣ እንደሚችል አልገለጡም። በድርሰታቸው የተመኙት የህግ ሉአላዊነት፤ ፍትህና እኩልነት፤ ለሰው ኃብታችን የምንችረው እንክብካቤ፤ ከጎረቤት አገሮችና ባጠቃላይም ከአለም ህዝብ ጋር ሊኖረን የሚገባው ጤናማ ግንኙነት ወዘተ ሁሉ ለእድገትና ለብልጽግና

መሠረት ናቸው:: የነዚህ ፋይዳዎች መስፈን ማለት ድህነት ጠፋ ማለት ላይሆን ይችላል:: ከዚህም ሌላ እነዚህ እሴቶች የሚገኙትና የሚጥሙት በእድገትና በልማት ውስጥ ነው:: የሚቀመስ በጠፋበት፣ የሚለበስ በሌለበት፣ ከቀን ሀሩር ከለሊት ቁር መካለያ በጠፋበት የነዚህ እሴቶች መኖርና ቢኖሩም በድሕነት አረንቋ ለሚዋኙ ወገኖች እንዴት ከችግራቸው የመውጫ ሊሆን እንደምንችል ልንረዳ ይገባናል:: እዚህ ላይ መሠረታዊው ጉዳይ እነዚህን በጎ የሕብረተሰብ እሴቶች ለምን አጣናቸው? ለዚህ ከታሪክ የምንማረው ምንድነው? የሚሉት ጥያቄዎች መታየትና መነሣት ይገባቸዋል::

ከሌላ አንጻር ሲታይ ደግሞ እነዚህ የህብረተሰብ እሴቶችና ባህርያት የልማትና የእድገት ውጤት መሆናቸው መረሳት የለበትም:: ስለዚህም እነዚህን ተደጋጋፊ ቁምነገሮች እንዴት ለማስረጽ እንደሚቻልና የኢትዮጵያ ህዝብ ካለበት የከፋና ተስፋ የሚያስቆርጥ ድህነትና ችግር ተላቆ የህግ ሉአላዊነት፣እኩልነትና ፍትህ በሰፈነበት አገር ለመኖር የሚያስችል ስልት ቢያከሉበት ትልቅ እገዛ ያደርግ ነበር የሚል እምነት አለኝ::

ከዚህም ሌላ የቅደም ተከተል ጉዳይ አለ:: ሁለት የትግል መስኮች ከፊታችን ተደቅነዋል:: አንዱ ችጋርና ችግር ሲሆን ሁለተኛው የህግ ልእልናና፣ ፍትህ ናቸው:: እነዚህም በራሳቸው የሚመጡ ሳይሆን ከፍ ያለ መስዋእትነትን የሚያስከፍል የትግል ውጤቶች መሆናቸው የታወቀ ነው:: ጥያቄው እነዚህ ተፈላጊ ሁኔታዎች በተራ በተራ ነው ወይስ ሁሉቱንም በአንድ ጊዜ ለማስፈን ይቻላል:: በተራ በተራ ከሆነስ የትኛው ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል?

ይህ ጉዳይ ትልቅ ፋይዳ ያለው ሰፊና ጠለቅ አድርጎ መታየት የሚገባው ነው:: እስከዛሬ ድረስ ያለው ታሪክ ሲቃኝ መጀመሪያ ልማትና እድገት ቀጥሎ መብት የሚሠፍኑበት ሂደት ነው የሚታየው:: የኛም እንዲሁ ነው ወይስ ሁሉቱንም አንድነት ወይም መብትን ልናስቀድም የምንችልበት ስልት ልንቀይስ እንችላለን?

## ሐ) የማን ራእይ?

የኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ ደሃ ነው:: በራሱ መኖር አቅቶት ከቀረው ዓለም በሚሰበሰብ እርዳታ ነው የሚኖረው::

መሪዎቻችን የሕዝባቸውን ኢኮኖሚያዊ ደሕንነት የማረጋገጥ ኃላፊነት እንዳለባቸው የዘነጉ ይመስላሉ:: ድርቅ መኖሩ ታውቆ ሲከሰት ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመከላከል የሚያበቃ በቂ ዝግጅት አለማድረግ ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል የነበረውን ጥረት የማክሸፍ ተግባርና መሠረተ ልማቶችን መፍረስ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ተግባራዊ ሆንዋል:: ለምን እንዲህ ይደረጋል የሚል ጥያቄ ማንሳት አግባብነት አለው?

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ የደኸየው ተፈጥሮ ነፍጋው ወይም በራሱ ስንፍና ሳይሆን ሠርቶ ለመክበር በማያመች ሥርዓትና ገዥዎች ባሳደሩበት ተጽእኖ መሆኑ የታወቀ ነው:: ስለዚህም መሪዎች ከጣሉበት እግረሙቅ ተላቆ እራሱን ከድህነት ነጻ ማውጣት የሚያስችለውን ሥርዓት እንዴት ማስፈን ይቻላል?

## ለ) «የምናባቱ ይሆናል» ፖለቲካ

ይህ ጥያቄ አግባብነት ያለው በአገሪትዋ ውስጥ ለረዥም ዘመን ሰፍኖ የኖረው የአገዛዝ ሥርዓት ከህዝብ የወጣና ለአገርና ለህዝብ የሚያስብ አለመሆኑን ስንገነዘብና ለልማት አመቺ የሆነ ሥርዓት ማስፈን አስፈላጊ መሆኑን ስንረዳ ነው:: እስከ ፍጻሜ ዘውድ የነበረው ሥርዓት ኃይማኖትን መሠረትና ተገን በማድረግ ለመገልገል እንጂ ለማገልገል የልተፈጠረ መሆኑን በይፋ አውጆ የኖረ ሥርዓት ነው:: እግዚአብሔር ንጉሠነገሥቱን፣ መርጦና ባርኮ በቀደሳት አገር ላይ እንደራሴው አድርጎ ቅብአቅዱስ ቀብቶ ያነገሳቸው በመሆኑ አለመታዘዝና ፈቃዳቸውን አለመፈጸም የሚያስኮንን ነበር:: ህዝብ የሚኖረው እሳቸውንና በሳቸውም በኩል እግዚአብሔርን ለማገልገልና ለማመስገን ነው:: ስለዚህም ንጉሱና እሳቸው የሾሙት ሁሉ ከነሱ በታች ትዕዛዝ ሰጪ፣ ተገልጋይ ነበሩ:: ይህም በመሆኑ ነው የገባር ሥርዐት ለዘመናት ተንሰራፍቶ የኖረው::

ከዘውድ ሥርዓት መገርሰሥ በኋላ የመጡት ሁለት ሥርዓቶች የሥልጣንን ባለቤት ከሰማየ ሰማያት አውርደው ለ«ሰፊው» ህዝብ ካስረከቡ በኋላ ራሳቸውን ወኪሉ በማድረግ በህዝብ ላይ ነገሡ:: ጠያቂ የሌለበት ሙሉ ሥልጣን ይዘው አገርን እንዳሻቸው አድርገዋል:: በህዝብ ስምና ለህዝብ ህዝብን አምሰዋል:: እነሱ ህዝብ ሆነው ሃሳባቸውን፣ የተቃዋወመው ጸረ ህዝብ ሆንዋል:: ይህ መሆን እንደሌለበት ህዝብ ተረድቷል::

እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ የመሪዎችን ራእይና ፍላጎት እንዴት ከህዝብ ራዕይና ፍላጎት ጋር ማሳማማት ይቻላል የሚል ነው:: ካልሆነ እንዴት ማስተካከል ይቻላል?» ምን አይነት ቁጥጥርስ ሊደረግባቸው ይገባል? ፕሮፌሰር ባሕሩ ኃሳብ የሚያጭሩ ውይይትና ክርክር የሚያስነሱ የታሪክ ትምህርትና እይታ ለግሠውናል:: ከዚህ ወዴት እንደምንሄድ ናውቃለን፣ ንዴትና በምን ፍጥነት ንደምንሄድ መወሰን የኛ ፈንታ ነው፣ በመሆኑም እንወያይ! እንነጋገር!

**ANNOUNCEMENT**

We are glad to inform our esteemed readers that Ethiopian Journal of Economics Volume VIII Number 2 is now on sale.

# አብዮት፣ ሌጂቲማሲና ፖለቲካ፦ ሶስት አበይት ሂደቶችና ራዕይ 2020

ሺፈራው በቀለ
ታሪክ ክፍል አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ይህ አጭር ጽሁፍ ዶ/ር ባህሩ ዘውዴ ባቀረበው ጽሁፍ ላይ አስተያየት ለመስጠት የተጻፈ ነው። እኔ እንዱ አወያይ ስለነበርኩ እንዱ ተግባሬ የዶ/ር ባህሩን ጽሁፍ አስመልክቶ ሊነሱ የሚችሉ ጭብጦች ላይ "መተቸት" ሲሆን ሌላው ደግሞ ለውይይት አመቺ የሆኑትን ነጥቦች ለይቶ ማውጣት ይሆናል።

በመጀመሪያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበርን ማመስገን የምፈልግባቸው ሁለት ጉዳዮች አሉ። አንደኛው ሙያዊ ጥናቶች በማድረግ የሚያወጣቸው መጽሀፍትም ሆኑ መጽሄቶች ሰፊ ጥቅም ያላቸው ስለሆኑ ማህበሩ ሊመሰገን ይገባዋል። ሁለተኛ ይህንን የራዕይ 2020ን የውይይት መድረክ በመክፈቱ ብቻ ሳይሆን፣ የመጀመሪያውን ተናጋሪ የታሪክ ምሁር በማድረጉ ላመሰግነው እወዳለሁ። ይህ እድል ለወደፊት በሚደረጉት ውይይቶችም ላይ በጉ ተጽዕኖ ይኖረዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ስለዚህም ምክንያቴ ግልጽ ይመስለኛል፦ ራዕይ 2020 ትርጉም የሚኖረው፣ አስተዋጽኦ ሊያደርግ የሚችለው በሂደቶች (ወይም trends) ላይ የተመሰረተ ሲሆን ብቻ ነው። ሂደቶችን ለይቶ ማውጣት የውይይቱ እምብርት መሆን ያለበት ይመስለኛል። አለበለዚያ የህልም ልውውጥ ብቻ ይሆንና ብዙም ፋይዳ የሚኖረው መድረክ ላይሆን ይችላል።

ከዚህ አንጻር ስናየው ዶ/ር ባህሩ ፈር የቀደደ ይመስለኛል። ወደኋላ ምዕተ ዓመት ተኩል በመሄድ የኢትዮጵያን ታሪክ በመዳሰስ አንኳር አንኳር የሆኑ ጉዳዮችን ለማንሳት ሞክሯል። ሁላችንም እንደምናውቀው ከእንደዚህ ዓይነቱ ውስብስብ ታሪክ ውስጥ ጥቂት አበይት ሂደቶችን ፈልፍሎ ማውጣት በጣም ያስቸግራል። የቱ ሂደት ከየቱ ይበልጣል የሚለው አእምሮን የሚያስጨንቅ ጥያቄ ነው።

ይህንን ካልኩ በኋላ አላማዬ እሱ ያላቸውን መድገም አለመሆኑን መግለጽ እወዳለሁ። እሱ ካለው ላይ ተነስቼ ግን ሶስት ሂደቶችን (ወይም trends) በመለየት በነሱ ላይ አስተያየቴን በመስጠት ጽሁፌን አጠናቅቃለሁ። የዶ/ር ባህሩ ጽሁፍ ያጠነጠነው በምሁራን ራዕይ ላይ ነው። በዚህ ዘመን ከነበሩት መሪዎች ውስጥ ያተኮረው በቴዎድሮስ ላይ ብቻ ነው። ምሁራንን ግን በሁለት ትውልድ ከፍሎ በሰፊው አይቷቸዋል። በቅድመ ጣሊያን ወረራ ጊዜ የነበሩትን ምሁራን በመጀመሪያ ከዳሰሰ በኋላ ወደድህረ ጣሊያኑ ዘመን ሄዷል። የምሁራኑን ትንተናዎችና ራዕዮች አሳጥሮ ለማቅረብ ሞክሯል። አቀራረቡ ባብዛኛው ትክክል ነው።

ይሁንና አንድ ነጥብ መጨመር ያለበት ይመስለኛል። ይህም

ቅድመ-አብዮት የነበረው አብዛኛው ወጣት ምሁር የነበረው ትልቁ ራዕይ አብዮት ማምጣት ፡ ሀገሩን በአብዮት መለወጥ ነበር። በዚህም የተነሳ የተማሪዎች ንቅናቄ ለሥር ነቀል ለውጥ ታገለ። የወቅቱን ሥርዓት ገዘገዘ። አገሪቱንም እንደተመኘው ለአብዮት ዳረጋት። ወይም በሌላ አገላለጽ በ66 ለፈነዳው አብዮት ዋነኛው አስተዋጽኦ የምሁራን፣ በተለይም የተማሪዎች ነበር። አብዮቱ ከፈነዳ በኋላ ግን የራሱን እቅጣጫ ተከትሎ ወደፊት ማስገምገም ጀመረ። እንደተጠበቀው ሳይሆን ቀርቶ የደም ጐርፍ ተንጀረጀረ፤ አገሪቱም በእንባና ዋይታ ተሞላች።

እዚህ ላይ ማተኮር ያለብን ግን በስቆቃው ላይ ሳይሆን በአብዮቱ

ባህርያት ላይ መሆን አለበት ባይ ነኝ። የአብዮቱን ዋና ዋና ፀባዮችና የወለዳቸውን ሂደቶች ሳያጤኑ ራዕይ መቅረጽ ራዕዩን የተሟላ አያደርገውም። እኔም ብሆን የተሟላ የአብዮቱን ትንታኔ ለማድረግ ሰቅድ የለኝም፤ ጊዜውም ቦታውም አይፈቅድም። ሶስት ነጥቦች ብቻ በማንሳት ጉዳዩን ለውይይት በመክፈት አልፋዋለሁ። አንዱና አብይ ከሚባሉት ማህል የሚጨመረው የአብዮት ፀባይ ጽንፈኛነት መሆኑን ነው። ፕ/ር ባህሩ ጽንፈኝነትን ለይቶ በማውጣት የሚያስከትለውን ጉዳት በአጽንኦት ገልጿል። ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ። እሱ ባቀረበው ላይ የማክለው ነጥብ ጽንፈኝነት የአብዮት አካል መሆኑን ብቻ ነው።

እርግጥ ጽንፈኝነት የማንም አብዮት ተብዬ ክስተት አካል ነው ማለት አይደለም። ይሁንና የክላሲካል አብዮቶች ባህርይ መሆኑን በአጽንኦት መግለጽ እፈልጋለሁ። የኢትዮጵያ አብዮት ደግሞ የሶስቱ ትላልቅ የአለም ክላሲካል ሶሻል አብዮቶች (የፈረንሣዩ፣ የራሽያውና የቻይናው) ዓይነት መሆኑ ቢያንስ ኢትዮጵያን በሚያጠኑ ምሁራን መካከል ስምምነት አለ። ክላሲካል ሶሻል አብዮቶች ደግሞ የመደጋገም ባህርይ አላቸው። በአንድ አብዮት አያበቃም፤ አብዮቱ ሌላ አብዮት ይወልዳል። ፈረንሣይ ቢያንስ በአራት አብዮቶች ተንጣለች። አሁን በቅርቡ የተደረገውንና ሶቭየት ህብረትን ያፈራረሰውን ለውጥ ከጨመርነው ራሽያ ቢያንስ በሶስት አብዮቶች ተናውጣለች። ቻይናም እንዲሁ። የኢትዮጵያ አብዮት ሌላ አብዮት መውለዱንና አሁን የምንገኘው በሁለተኛው አብዮት 12ኛ ዓመት ላይ መሆኑን ብዙዎቻችን እንገነዘባለን የሚል ተስፋ አለኝ።

አብዮት አብዮትን የመውለድ ትሬንድ የሚያሳየው በልዩ ልዩ ምክንያቶች ሊሆን ይችላል። ከነዚህም አንዱ የሊጅቲማሲ ጉዳይ ነው። የክላሲካል አብዮት አንዱ ዓላማ የወደቀውን ሥርዓት ሊጂቲማሲ ማጥፋት ነው። አብዮቱ ሲፈነዳ ስልጣን የሚይዘው ግሩፕ የሚቸገርበትም ዋናው ጉዳይ ይኸው ሊጂቲማሲ ነው።

የኛን አገር እንደምሳሌ ብንወስድ ደርግ ገና አበጁ ብሎ ፖለቲካን ሲጀምር አፍጥጦ የመጣበት ችግር ሊጅቲማሲ ነበር። ዋና ዋናዎቹ የአብዮቱ ኃይሎች ደርግን "አብዮቱን ማጅራት መቺ" ስልጣንን የተቆናጠጠ ቡድን ይሉት ነበር። "ማጅራት መቺ" የሚለው አገላለጽ ችግሩ ሊጂቲሚሲ እንደሆነ ፍንትው አድርጎ ያሳያል። በሌላ ቋንቋ usurper ማለት ነው። ደርግም ሊጂቲማሲ ለማግኘት ያልፈነቀለው ድንጋይ እንደሌለ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

ይህ አንገብጋቢ የሊጅቲማሲ ጥያቄ ፕ/ር ባህሩ ወዳነሳው ትልቅ ጉዳይ ይወስደናል፦ ህገመንግሥት። ኢትዮጵያ እስካሁን አራት ህገመንግስቶች አይታለች የእንዳልካቸው መንግስትን ሙከራ ሳይጨምር። ይህም ቀላል ቁጥር አይደለም። እነዚህ አራት ህገ መንግሥቶች የሚለያዩትን ያህል የሚጋሯቸው ባህርያትም አሏቸው። በዚህ በኩል ፕ/ር ባህሩ ያቀረበውን ትንታኔ ሙሉ በሙሉ እቀበለዋለሁ። አንዱን ብቻ መድገም እንዲፈቀድልኝ እጠይቃለሁ። ይኸውም አራቱም ባሸናፊ ኃይሎች የተቀረጹና ከላይ የተጫኑ ናቸው የሚለው ነጥብ ነው። ይህ ትክክል መሆኑን በአጽንኦት ስናገር የኋለኞቹ ሁለቱ ስርዓተ መንግስቶችም (ደርግና ያሁኑ) የኛ የተለየ ነው፤ የኛ ከህዝብ የመነጨ ነው በማለት ህዝብን ለማሳመን ያደረጉት የነበረውን ልፋት ዘንግቼው አይደለም። እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ጥያቄ ለምንድነው ሶስቱም ስርዓተ መንግሥታት (የዓፄው፣ የደርግና የወያኔ) ህገመንግስት ላይ ይህን ያህል ጉልበት፣ ሪሶርስና ጊዜ የሚያጠፉት የሚለው ነው። ለዚህ ጥያቄ መልስ ስናፈላልግ አንደኛ ይህ የህገመንግሥት ጉዳይ ነጠላ ነገር ሳይሆን ሂደት መሆኑንና ሁለተኛም የህገመንግሥት ጥያቄ ሊጂቲሚሲን ለማግኘት የሚደረግ ትልቅ ጥረት መሆኑን እንገነዘባለን።

የዓፄ ኃ/ሥላሴን ታሪክ ስንመረምር ዓፄው ወደ ህገመንግሥት ቀረጻ የሄዱት ሊጂቲማሲ ፍለጋ እንደነበር በቀላሉ መረዳት ይቻላል። የሳቸው የሊጂቲማሲ ችግር የሥርዓተ መንግሥቱ ሳይሆን የግላቸው ነው። የንጉሥታት ተወላጅ መሆናቸው ቢታወቅም ቅሉ በቀጥታ ከመጣው ከሣህለ ሥላሴ ኃ/መለኮት ምኒልክ ግንድ ላይ ሳይሆኑ ቅርንጫፍ ነበሩ። ችግሩ ሌሎችም አያሌ ቅርንጫፎች ነበሩ፣ ልክ እንደሳቸው ዘውዱ ይገባናል የሚሉ። የአፄው ፍላጎትና ራዕይ ደግሞ ዘውዱን በሳቸው ራስ ላይ ብቻ ሳይሆን በልጅ ልጆቻቸውም ላይ እንዲቀመጥ ነበር። የሸዋ መሳፍንት ብቻ ሳይሆኑ የትግራይ፣የጐጃምና የጐንደር መሳፍንትም ለዘውዱ ተገቢነት አለን በሚል ቢያንስ

በሆዳቸው ነገር ማጠንጠናቸው የአደባባይ ምስጢር ነበር፡፡ ስለዚህ አፄው ህገመንግስትን መሣሪያ አድርገው (ኢኮኖሚስቶች ኢንስትሩመንት የሚሉት ዓይነት ማለት ነው፡፡) የራሳቸውንና የልጅ ልጆቻቸውን ሌጅቲማሲ ለመትከል ፈለጉ፡፡ ህገ መንግስቱን ስናነብ ይህ ጉዳይ በጉልህ ይታያል፡፡

ዓጼ ኃይለ ሥላሤ ግን ህገ መንግሥቱን ለሌላም ጉዳይ በመሣሪያነት ሊጠቀሙበት አቅደው ነበር የመኳንንቱንና የባላባቱን ክፍል ከማዕከላዊ መንግሥታቸው ጋር ማስተሳሠሪያ ማድረግ፡፡ ይህንንም በተለይ ከእንግሊዝ House of Lords የወሰዱት ነገር ነበር፡፡ የመኳንንቱንና የባላባቱን መደብ በፖርላማ ውስጥ በማስወከልና የዘውዱ አማካሪ በማድረግ ለዘውዱ ሠፊ ሶሻል መሠረት መስጠትም ይፈልጉ ነበር፡፡

የዓጼ ኃ/ሥላሴን ሙከራ ሰፋ አድርጊ ያየሁት ደርጉ ህገመንግሥትን በሚመለከት የወሰዳቸው እርምጃዎች የቅርብ ጊዜ ትዝታ ስለሆኑ ብዙም ማለት አያስፈልግም በማለት ነው፡፡ ደርጉ ህገመንግስቱንና ኢህድሪን ሲያቆም ሌጅቲማሲ በተሟላ መልኩ አገኝባቸዋልሁ ብሎ ማሰቡ አልቀረም ነበር፡፡ አልተሳካለትም እንጂ፡፡ የዚህን መንግሥትስ ጥረት ከዚህ ውጭ ማየት ይቻላል?

ስለዚህ በኢትዮጵያችን ባለፉት አያሌ አሠርታት የምናየው አንድ ረጅም ሂደት ህገመንግስትን የሌጅቲማሲ መሣሪያ አድርጉ መጠቀም ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ጉልበት፣ ሪሶርስ፣ ጊዜ ከለመጠን ይፈስበታል፡፡ ይህ ሁሉ አስፈላጊ ነው ወይ? ቢያንስ የቅርቡ ታሪካችን የሚያዋጣ መንገድ እንዳልሆነ በእንክሮ ያሳያል፡፡ ሌጅቲማሲን ለማምጣት በቅጡ መታሰብ አለበት፡፡ የፖለቲካ ኃይሎችና የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን በዚህ ጉዳይ ተጨንቀው ተጠበው መፍትሄ ማፈላለግ አለባቸው፡፡ ምክንያቱም ሌጂቲማሲ የሌለው ሥርዓተ መንግስት በድቡሽት ላይ እንደተሠራ ቤት ነውና፡፡ ወደፊት 25 ዓመት ስንመለከት ኢትዮጵያ ሌጂቲማሲ ያለው መንግስት ሊኖራት ይችላል ወይ ብለን መጠየቅ አለብን፡፡ ሌጅቲማሲ ያለው መንግሥት ካላት ጽንፈኝነት ያበቃለታል፡፡ በህዝቡ ሙሉ ትብብር፣ ሙሉ ጉልበትና ኃይል አገር መገንባቱን መያያዝ ይቻላል፡፡ ፖለቲካም የተከበረ ፕሮፌሽን ይሆናል፡፡

አብዮት ካመጣቸው ብዙ መዘዞች ውስጥ አንዱ የፖለቲካ ፕሮፌሽናል ደረጃ እየወደቀ መሄድ ነው፡፡ ፖለቲካ ማለት መቀላመድ፣የመንግሥትን እና የህገርን ሀብት ልፎ ለልጅ ለልጅልጅ፣ ለዘመድ አዝማድ፣ ለአምቻ ለጋብቻ፣ ለዝርያ ለጉሣ "ጮማ መቁረጥ ጠጅ ማፍሠሥ" ማለት ሆኗል፡፡ በኢትዮጵያውያን አእምሮ ውስጥ በፖለቲካና ማፍያ መካከል ልዩነቱ እየደበዘዘ ሄዷል ማለት ይቻላል፡፡ በመሠረቱ ግን ፖለቲካ በምዕራቡ አለም እጅግ የተከበረ ፕሮፌሽን ነው፡፡ ጥንትም በሀገራችን እንዲሁ ነበር፡፡ በመጀመርያው አብዮት ዘመን ግን ደረጃው እየወረደ ሄዶ አሁን እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ ደርሷል፡፡

ፖለቲካና ፖለቲሺያኖች የተከበሩ ካልሆኑ፤ ጨዋ የጨዋ ጨዋ ካልሆኑ፣ ሳገር አሳቢ ለወገን ተቆርቋሪ ካልሆኑ፣ የሚናገሩት መሬት ጠብ የማይል ካልሆኑ ምንም ያህል ውብ ውብ ራዕዮች ስንደቀድቅ ብንውል ራዕዮቻችን ዋጋ አይኖራቸውም፡፡ ከ25 ዓመት በኋላ ፖለቲካ ከወደቀበት አዘቅት ወጥቶ የተከበረ ሙያ ሊሆን ይችላል ወይ? ይህ ልናሰላስልበት የሚገባ ጥያቄ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በምን መልክ ብንሠራ፣ ብናስተምር፣ ብንጽፍ፣ብንታገል ነው ፖለቲካ አሁን ካለበት አዘቅት ወጥቶ የተከበረ ፕሮፌሽን ሊሆን የሚችለው ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን፡፡ የፖለቲካ ፕሮፌሽን ግርማ ሞገስና አክብሮት መጐናጸፍ በቀጥታ ከሌጂቲማሲ ጋር ይቆራኛል፡፡ በሚመጡት 25 ዓመቶች ውስጥ ሌጂቲማሲ ያገኘ ሥርዓተ መንግሥት ማየት እንችላለን ወይ? ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን፡፡ ተሳክቶልን (ወይም በልምድ እንደሚባለው እግዜር ብሎልን) ሌጅቲማሲ ያለው ሥርዓተ መንግሥት ቢዋቀር ያብዮት ድግግሞሽም ፣ የርስ በርስ ጦርነትም፤ ድንፈኝነትም አበቃላቸው ማለት ነው፡፡ አለበለዚያ ሁሉም ነገር ታጥቦ ጭቃ ነው የሚሆነው፡፡

ስለዚህ በእነዚህ ሶስት ሂደቶች ላይ፦ ማለትም አብዮትና ድግግሞሹ፣ ሊጂቲማሲ ማጣትና የፖለቲካ ፕሮፌሽናል ስታንዳርድ መውደቅ ላይ በእንክሮ ልንወያይባቸው ይገባል ባይ ነኝ፡፡ ራዕያችንንም ስንጽፍ እነሱን ግንዛቤ ውስጥ አስገብተን መሆን አለበት፡፡

# ከኢትዮጵያ ረሀብን ለማጥፋት ብሎም ድህነትን ለመቀነስ የተደረገ ጥናት

ከታደስ ኃይለሥላሴ (ኢንጅነር)

## መግቢያ

ድህነትና ረሀብን ከኢትዮጵያ ለመቀነስ፣ ከተቻለም ለማጥፋት፣ ምን መደረግ አለበት በሚለው አርእስት ላይ በመላው ኢትዮጵያ ባለፈው ዓመት ሰፊ ውይይት በልዩ ልዩ መድረክ ሲካሄድ እንደነበር ከሁላችሁም የተሰወረ አይደለም:: እኔም በኢትዮጵያ መሐንዲሶች ማህበር ስብሰባ ላይ ተገኝቼ፣ መፍትሄ ሊሆን ይችላል ብዬ ያቀረብኩትን ሀሳብ ለእናንተ ለመግለጽ እድል ስለሰጣችሁኝ አመሰግናለሁ ::

## ችግሩ ምንድነው? እውነት ችግር አለ ወይ? እውነት ረሀብ እና ድህነት በኢትዮጵያችን አሉ ወይ?

ረሀብ በአገራችን ተንሰራፍቶ እንደነበረና በአሁኑ ወቅትም በመከሰት ላይ እንደሚገኝ የሚያጠያይቅን አይደለም:: ለአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት መውደቅ ዋና ምክንያት ተደርጎ የተወሰደው የ1966 ዓ.ም. የወሎ ረሀብ ነው:: የደርግን መንግሥትም ያንበረከከው፣ ይህው ለረሀብ መፍትሄ ያለማግኘት ነው:: አሁንም የኢህአዴግ መንግሥት ትልቁ ሥራው ረሀብን ለመቅረፍ መሯሯጥ ነው:: ረሀብ በአገራችን ለሚቀጥሉት ዓመታት ከኛ ጋር እንደሚኖር ብዙ ፍንጮች ያመለክታሉ:: በዚህ ሀሳብ ላይ ከተማመንን፣ ብዙ ኢትዮጵያውያኖች ለምን ረሀብተኞች ሆኑ የሚለውን ቀጥሎ በተመለከተው ሁኔታ ለመመለስ እሞክራለሁ ::

## ሥራ ፈትነት ውጤቱ ረሀብና ድህነት ነው

ባዘኔነት = ረሀብና + ድህነት

ኢትዮጵያውያኖች:- ረሀብተኛና ደሀ የሆንነው በምን ምክንያቶች ነው? 85% ወይም 50 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ በግብርና ሥራ መሰማራቱን ብዙ ጊዜ ተገልጾልናል:: ታዲያ ይህ ሁሉ ሰው ሥራ ካለው፣ ካመረተ፣ ለምን ረሀብተኛና ድሀ ሆንን ?

እነዚህን ሁለት ሀሳቦች እንደኛው፡ 50 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን በግብርና ተሰማርተዋል:: ሁለተኛው፡ ኢትዮጵያውያኖች ለዘላለም ረሀብተኞች ናቸው:: የሚለውን በጥልቀት በማጤን እውነቱ ላይ መድረስ አለብን:: ሁለቱ ሀሳቦች እርስ በእርሳቸው ይጋጫሉ አንዱ ሌላውን ያፈርሳል::

የኢትዮጵያ ህዝብ 63 ሚሊዮን ያህል ይደርሳል:: ከዚህ ውስጥ 85% በግብርና ሥራ ተሰማርቷል:: 10 ሚሊዮን የገበሬ አባወራዎች እንዳሉ ይነገረናል:: ይህ አባባል ብዙ ኢትዮጵያውያኖች በግብርና ሥራ መሠማራታቸውን ይገልጻል፣ ያሳውቀናል:: ይህ የመጀመሪያው እውነታ ነው::

ሁለተኛው እውነታ ብዙ ኢትዮጵያውያኖች ዓመት ከዓመት ረሀብተኛና ድሀ ናቸው :: ከአፄ ምንሊክ ጀምሮ በነበሩት መንግሥታት ረሀብና ድህነት ከኢትዮጵያችን አልጠፋም::

እነዚህ ሁለት ሀሳቦች እርስ በእርሳቸው ስለሚጋጩ ከነዚህ ሁለት ሀሳቦች አንዱ አሸንፎ ሌላውን መጣል አለበት እንጂ ሁለቱንም ልንቀበላቸው አንችልም::

## የትኛውን ውድቅ አድርገን የትኛውን እንያዝ?

በእኔ እምነት፣ ቁልጭ ብሎ የሚታየውን፣ ለብዙ አመታት በአይናችን ያየነውን፣ ኢትዮጵያውያን ረሀብተኛና ድሀ መሆናቸውን ብንቀበልና የኢትዮጵያ ህዝብ 85% በግብርና ተሰማርቷል የሚለውን ውድቅ አድርገን ብንመለከተው የሚሻል ይመስለኛል::

ይህን ጥያቄ ስንገፋበት፡ የምንደርስበት እውነተኛ ጉዳይ፡ 85% ወይም 50 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያኖች በማሳ ላይ ስፍረዋል:: መሬቱን ይዘዋል:: ገበሬ ነን ይላሉ:: ግን ትክክለኛውን የግብርና ሥራ እንደማይሰሩ እንደርስበታለን፡ ምርታማ ገበሬ እንዳይደለ ከሥራ ውጤታቸው እናገኘዋለን:: እንገነዘባለን:: የኢትዮጵያ ገበሬ፡ በስም እንጂ በሥራ የለም፡ ቀጥለን ምርታማ የግብርና ሥራ ምንድን ነው ? የሚለውን በዝርዝር እንመልከት:: አንድ ሰው ምርታማ ገበሬ ለመሆን የሚከተሉትን 6 ነጥቦች አቀናጅቶ መገኘት አለበት እነሱም፡-

1. መሬት
2. የሰው ጉልበት
3. ውሀ
4. ምርጥ ዘር
5. የፀሀይ ሙቀት
6. ዲሞክራቲክ መንግሥት

ምርታማ ገበሬ፡ ሊፈጠር፣ ሊኖር፣ የሚችለው ቢያንስ፡ እነዚህ 6 ነጥቦች በሚገባ ተቀናጅተው ሥራ ላይ ከዋሉ ነው:: ከነዚህ 6 ነጥቦች አንዱ ከጎደለ ፡ ወይም በአመርቂ ሁኔታ ካልተገኘ ፡ ምርታማ ገበሬን ማግኘት አንችልም::

በአገራችን የነዚህ 6 ነጥቦች እውነታ እንዴት እንደሆነ ቀጥዬ በዝርዝር ስናገር በጥሩ ሁኔታ ከሚገኙት በመነሳት ማነቆ ወደ ሆኑት እወርዳለሁ

## 1. የፀሀይ ሙቀት

ኢትዮጵያ በአለም መቀነት አካባቢ ስለምትገኝ፤
30 ዲግሪ ሴንቲግሬድ - የቀን ሙቀት፤
15 ዲግሪ ሴንቲግሬድ - የሌሊት ሙቀት ዓመቱን ሙሉ በብዙ በእርሻ ማሳዎቻችን ስለሚገኝ ይህ የሙቀት መጠን ደግሞ ለብዙ አዝርዕቶች በጣም ተስማሚ ስለሆነ በዚህ የፀሀይ ሙቀት ኢትዮጵያውያኖች የታደልን ይመስለኛል:: ለጊዜውም ቢሆን በነፃ ያገኘነው ሀብት ነው::

## 2. የሰው ሀይል

2.1 በአሁኑ ጊዜ 63 ሚሊዮን ያህል ስንሆን
2.2 ከዚህ ውስጥ በጡረታ እድሜ 3 ሚሊዮን ያህሉ
2.3 ከህጻን አንስቶ እስከ ትምህርት መጨረሻ (እስከ 20 ዓመት እድሜ ውስጥ) 36 ሚሊዮን ያህል
2.4 ለሥራ ዝግጁ የሆነ (ከ20 እስከ 60 ዓመት ያለ) 24 ሚሊዮን ያህል

ይህ እሀዝ ኢትዮጵያ በሰው ሀይል ከፍተኛ ሀብት እንዳላት ያሳያል፤ 25 ሚሊዮን አምራች ኃይል ያላቸው አገሮች በአለም በቁጥር ትንሽ ናቸው:: ሆኖም፡ ወሳኙ ቁጥሩ ሳይሆን፡ የነቃ ፡ የተደራጀ ፡ የተማረ፡ መሆኑ ላይ ነው:: ኢትዮጵያችን በዚህ ጥያቄ ጠቃሚ አቋም እንዳላት ይታያል፡ ድክመቶቻችንን ማሻሻል ብቻ ይጠበቅብናል!

## 3. ምርጥ ዘር

በጣም ተፈላጊ የሆነውን የምርጥ ዘር፣ ማግኘት፡ አያቅትም:: በአሁኑ ጊዜ ተስፋ ሰጭ ዜናዎች፡ ከግብርና የምርምር ማዕከሉችና፡ ከግብርና ዩኒቨርስቲዎች በመስማት ላይ እንገኛለን:: የግብርና ሳይንቲስቶች ከተበረታቱና ባጀቱ ከተፈቀደላቸው ተዓምር ሠርተው ምርጥ ዘሮችን (ለእያንዳንዱ ወረዳ ተስማሚ የሆኑ) አዘጋጅተው ለማበርከት እንደሚችሉ በርካታ ጥቆማዎች አሉ! በዚህ ጥያቄ ጥሩ አቋም አለን::

## 4. መሬት

ኢትዮጵያውያኖች ፡ ብዙ ሚሊዮን ሊመግብ የሚችል 1.12 ሚሊዮን ስኳየር ኪሎ ሜትር መሬት አለን:: ከዚህ ውስጥ አብዛኛው ጥሩ የእርሻ ማሳ ይወጣዋል::

በዚህ በመሬት ጥያቄ፡ የኢትዮጵያውያኖች ችግር ከእውቀት ማነስ የተነሳ የምንሠራውን፣ የምንናገረውን አለማወቃችን ላይ ነው:: ተማሪ በነበርኩ ጊዜ መሬት ላራሹ የሚለውን መፈክር በአዲስ አበባ አውራጎዳናዎች እንግበው ከተዘዋወሩት ዜጋዎች አንዱ ነኝ:: ይህ መፈክር፡ የአገራችንን ህዝብ፡ ብዙ ያበጣበጠ፣ ያጋደለ፣ ሶሺሊዝምን በአገራችን በኢትዮጵያ፣ በአፍሪካ፡ እንዲገባ ያደረገ፡ መፈክር ነው:: ሆኖም ይህን መፈክር ለ30 ዓመታት፡ ሙህን፡ ሙህን፡ ያመጣነው ውጤት የለም፡ የበለጠ እንድንራብ፡ የበለጠ ደሀ እንድንሆን፡ የበለጠ እርስ በእርሳችን እንድንናከስ፡ አድርጎናል:: የዚህ መፈክር ውጤት በአይን የሚታየው የኢትዮጵያን ህዝብ ረሀብተኛ፣ ደሀ ያደረገ ነው!

በመላው አገራችን በተለየም በደቡብ፣ በምሥራቅና፣ በምዕራብ ክፍለ ሀገራት ከሚገኙ አውራጎዳናዎች፡ 2 እና 3 ኪሎ ሜትር ገብቶ፡ የሚገኘው ቦታ፡ የሰው እግር ረግጦት የማያውቅ መሬት ነው:: ብዙ ማሳዎች ዓመት ከዓመት - አይታረሱም፡ የሚታዩን፡ መቀማት የምንፈልገው፡ ሌላው ጎበዝ ኢትዮጵያዊ፡ ያለማውን ነው:: ይህ ጭፍን ምቀኝነት ሲሆን፡ ከእውቀት ማነስ የመጣ አስተሳሰብ ነው፡

የመሬት ላራሹ መፈክርን፡ ያስተጋባነው ሁሉ ራሳችንን መርምረን፡ እውነቱ ላይ

እንድንደርስ፡ ጥሪዬን አቀርባለሁ:: በእኔ እምነት፡ ንሰሀ፣ ሰባአ፡ ገብተን፡ መሬት ላራሹ የሚለውን መፈክር በመለወጥ ከላይ የዘረዘርኳቸው 6 ነጥቦች፡ ተቀናጅተው፡ ምርታማ ገበሬ የምናፈራበትን ዘዴ፡ መቀየስ አለብን:: ውሀ ላራሹ ብለን አቀናጅተነው ቢሆን ኖሮ ዛሬ ረሀብተኛ አንሆንም ነበር::

ይህን ነጥብ ለመዝጋት፡ ኢትዮጵያችን በቂ የእርሻ መሬት አላት፡ በመሬት ጥያቄ ያለንን እውቀት በማዳበር፡ ይህ ሁሉ መሬት ከእኛ ተርፎ የአለምን ህዝብ እንዲመግብ የመሬት ይዞታ በማን እጅ ቢሆን? ማን ቢያስተዳድረው? ለሁላችንም ጥቅም የሚሰጥበትን መንገድ ፈልገን ማወቅ ይኖርብናል::

## 5. ዲሞክራቲክ መንግሥት

ምርታማ ገበሬ ለማግኘት፡ ዲሞክራቲክ መንግሥት ለምን አስፈለገ? ትሉኝ ይሆናል:: በእኔ እምነት ያለንበት ዘመን፡ አብሮ የመስሪያ እንጂ፡ በነጠላ የምንቀሳቀስበት ጊዜ አይደለም:: የምንወስደው ማናቸውንም እርምጃ፡ ሌላውን፡ ጎረቤታችንን፡ እንደሚነካ ማወቅ አለብን:: ከማህበር፣ ከቀበሌ፣ ከወረዳ፣ ከክፍለሀገር፣ ከአገር፣ ወጥተን፡ የአለም አንዱ ክፍል መሆናችንን በመቀበል በሥራ መተርጎም ይገባናል:: በአሁኑ ዓመተ ዓለም፡ በዘመኑ ቴክኖሎጂ በመጠቀም፡ በጣም ቅርብ ስለሆንን ፡ የአንዱ ሥራ ፡ ጎረቤቱን የሚነካው ስለሆነ የሁላችንም፡ ሥራችን፣ እርምጃችን፡ መቀነባበር አለበት፡ ዲሞክራቲክ መንግሥት ማለት ይህን ቅንብር በሥራ ላይ የሚያውል አካል ነው:: በእኛ በኢትዮጵያችን ይህን 50 ሚሊዮን በገጠር የሚገኝን ህዝብ፡ አስተባብሮ፡ እንዲሠራ፡ ምርታማ፡ የሚያደርግ፡ ለሁሉም ሰው እንደአባት፡ ሆኖ በፍቅር፡ በመተሳሰብ ልንሠራ፣ ልናመርት የምንችለውን በማሳመን ሥራ ላይ እንዲያስማራን፣ የምንፈልገውን በማቅረብ እንዲረዳን፡ በሌላው መልኩ፡ እንደ ፖሊስ ሆኖ፡ ሰነፉን፣ ወርበላውን፣ ሌባውን፣ በጥባጩን፡ በማስተማር፣ በመቅጣት፡ እርምጃ የሚወስደው አካል መንግሥት ይባላል::

መንግሥት ሲባል ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እና ሚኒስትሮች ብቻ አለመሆናቸውን በመገንዘብ፡ ፖስተኛው፣ ስልከኛው፣ ዘበኛው፣ ፖሊሱ፣ ወታደሩ፣ የቢሮ ፀሀፊዋ፣ ዳኞች፣ የፓርላማ ተወካዮች፣ አስተማሪዎች፣ ነርሶች፣ ዶክተሮችን የሚያጠቃልል መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል:: እነዚህ ሁሉ፡ ከዚያም ባሻገር መላው ህዝብ፡ በዲሞክራቲክ ሲስተም ራሱን መግዛት፣ ማስተዳደር፣ ረሀብንና ድህነትን ለማጥፋት ምርታማ ገበሬ ለመፍጠር፡ የሚቻለው በዚህ በዲሞክራቲክ መንግሥት ሲተዳደር ብቻ መሆኑን እንተማመን፡ እንቀበል::

በአገራችን ዲሞክራቲክ መንግሥት ለመፍጠር ብዙ እርምጃዎች እየተወሰዱ መሆናቸውን መካድ አልችልም:: በእኔ እድሜ፡ በዚህ ባለፉት 60 ዓመታት ብቻ ብዙ ወደፊት ተራምደናል:: መሪዎቻችን በእግዚአብሄር የተሰየሙ፣ የተመረጡ፣ ናቸው ከማለት ተላቀናል፡ እንደኛው ሰው መሆናቸውን ተቀብለን፡ ሥራቸውን ውሳኔአቸውን፡ መተቸት ጀምረናል::

የዛሬ 40 ዓመት አፄ ኃይለሥላሴ ዘንድ ቀርቤ እጅ ሳልነሳ በቀጥታ መልስ ለመስጠት ስጀምር ግድንግድ የሚያክለው የክቡር ዘበኛ አንገቴን አንቆ አስወጥቶኛል :: አሁን ሁኔታው ፡ በልዩ ልዩ መድረክ እና በነጻ ጋዜጦች፡ መሪዎቻችንን በዝርዝር እየተቹን ነው:: ብዙ ተራምደናል:: ግን አሁንም ብዙ ይቀረናል:: በስነስርዓት መወያየት፣ ሀሳብን መግለጽ፣ መብታችንን ግዴታችንን፡ ማወቅ አለብን:: እጅግ በፍጥነት በመራመድ ዲሞክራሲን እንገንባ ብንል፡ ተሰባብሮ መውደቅ እንዳለም፡ እንርሳ! እንግሊዞች አሁን የደረሱበት ደረጃ ለመድረስ 800 ዓመት ፈጅቶባቸዋል::

በመደምደሚያ ለዚህ ለያዝነው ውይይት ዲሞክራቲክ መንግሥት በአገራችን ካልተመሰረተ በምንም ዓይነት ምርታማ ገበሬ በማፍራት ረሀብንና ድህነትን ከኢትዮጵያ አናጠፋም::

## 6. ውሀ

ይህ የውሀ ጥያቄ ምርታማ ገበሬን ለማግኘት ለኢትዮጵያ ከባዱ እና ወሳኙ ነጥብ ነው:: የሚገርመው አገራችን ብዙ ውሀ እያላት ሳትጠቀምበት መቅረቷ ነው:: 130 ቢሊየን ሜትር ኩብ ውሀ ከአገራችን በየአቅጣጫው ወደ ሌሎች አገሮች በየአመቱ ይፈሳል:: ከዚህ ከ130 ውስጥ 2 ብቻ አስቀርተን ለእርሻ ብናውለው 10 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ከረሀብ እናላቅቃለን:: አንድ ቢሊየን ሜትር ኩብ ውሀ ለእርሻ መሬት ብናውል 5 ሚሊዮን እንመግባለን፡ 25 ቢሊየን ሜትር ኩብ ውሀ ብናቀርብ 150 ሚሊዮን ሕዝብ ለመመገብ እንችላለን::

ታዲያ ምንድን ነው ችግሩ! ለምን ይህን መፍትሄ ሥራ ላይ አላዋልነውም? አለም ብዙ ተራምዷል:: ጨረቃ ላይ ደርሰዋል:: (ነፍስ እየፈጠሩ ነው::) እኛ ከረሀብ አልተላቀቅንም፡ ኢትዮጵያዊ መባል የሚያሳፍር፡ በአለም መጨረሻው ድሀ ህዝብ

ከመባል የበለጠ ውርደት የለም! በሩጫ አንደኛ ሆነናል ሁላችንም ሮጠን ባህር ብንገባ ከዚህ ውርደት እናመልጣለን መሰለኝ!

በመሐንዲስነቱ፡ ረሀብንና ድህነትን ከኢትዮጵያችን ለመቀነስ ብሎም ለማጥፋት ያገኘሁት ዘዴ ለአንድ አባወራ 2 ሄክታር መሬት ከ10 ሺህ ሜትር ኩብ ውሀ ጋር በዓመት ብናቀርብ ይህን ችግራችንን እንሳቀቃለን የሚል ነው።

በዝናብ ተማምኖ፡ እርሻን ማካሄድ፡ ጉም እንደመጨበጥ የሚቆጠር ያህል ነው፡ የኢህአዴግ መንግሥት በኤክስቴንሽን ፕሮግራም ገበሬውን ምርታማ ለማድረግ ብዙ እየጣረ ነው። ይህውም ለ10 ዓመታት ተሞክሯል፡ ግን ከረሀብ አላወጣንም። የዚህ ፕሮግራም ትልቁ ድክመት በዝናብ ላይ የተመሠረተ እቅድ ስለሆነ ነው። ናሳም የአየር ፀባይ መተንበይ እስከአሁን አልቻለም። እኔ ኃይለሥላሴም ከሜትሮሎጂ ትንበያ የአህያ ጆሮን መመልከት ይሻላል ብለው ነበር። የመሬት ላራሹን መፈክር ተሸክመን በዞርንበት ጊዜ ዲሞክራቲክ መንግሥት ለአራሹ! ውሀ ለአራሹ! ብለን እነዚህንም ሁለት ጉዳዮች አብረን ዘምረን እስተጋብተን ቢሆን ኖር ዛሬ ምርታማ ገበሬ እናገኝ ነበር።

በጥናቱ ላይ ትኩረት የሰጠሁት፡ ገበሬውን ምርታማ ለማድረግ፡ ውሃ እንዴት እናቅርብለት የሚለውን በመመለስ ላይ ነው። ለአንድ ገበሬ ምርታማ ሆኖ እንዲሠራ ምን ያህል ውሃ ያስፈልገዋል? የሚለውን መጀመሪያ መመለስ አለብኝ ።

የውሃን ብዛት ለመወሰን ስፊ ምርጫ አለ! ብዙ ዝርዝር ጥናት እና ሁኔታዎችን ማመዛዘን ያስፈልጋል። የውሀን ብዛት የሚወስነው፡ የእዝርዕቱ ዓይነት፡ የአፈሩ ሁኔታ፡ የአየሩ ሙቀት፡ ለእርሻው የሚደረገው የካፒታል ወጭ፡ የገበሬው ንቃተ ህሊና፡ እነዚህን ሁሉ አጣምሮ፡ አይቶ፡ አመዛዝኖ፡ ይወሰናል።

ለኢትዮጵያውያኖች፡ በአሁኑ ጊዜ፡ ከተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት፡ ለአንድ ገበሬ 2 ሄክታር እና በዓመት 10 ሺ ሜትር ኩብ ውሀ ብናቀርብለት እስከ 30 ሺህ ብር የሚያወጣ ምርት ያገኛል። ይህን ያህል ካመረተ እጅግ በጣም ጥሩ ይሆናል! ምርታማ ገበሬ ሆነ ማለት ነው።

ስለዚህ :-

1. 1 ቢሊየን ሜትር ኩብ ውሃ ብናገኝ 100ሺ አባወራዎችን በማስፈር 5 ሚሊየን ኢትዮጵያውያን ለመመገብ ይቻላል።
2. 2 ቢሊየን ሜትር ኩብ ውሀ ብናገኝ 200ሺ አባወራዎች እንዲያመርቱ በማንቀሳቀስ 10 ሚሊየን ኢትዮጵያውያኖች ለመመገብ ይቻላል።
3. 25 ቢሊየን ሜትር ኩብ ውሃ ብናገኝ 2.5 ሚሊየን አባወራዎችን በማሠማራት 125 ሚሊየን ኢትዮጵያውያን ለመመገብ ይችላል።

በዚህ ጥናት ለመጠቆም የሞከርኩት እንዴት አድርገን :-

በእቅድ 1 = 1 ቢሊየን ሜትር ኩብ ውሀ
በእቅድ 2 = 2 ቢሊየን ሜትር ኩብ ውሀ
በእቅድ 3 = 25 ቢሊየን ሜትር ኩብ ውሀ

ልናገኝ ለገበሬው ልናደርስ እንችላለን የሚለውን ነው። ለግንዛቤ እንዲረዳችሁ አሁን በአገራችን ያለው የአዋሽ ወንዝ በዓመት 1 ቢሊየን ሜትር ኩብ ፍሳሽ ሲኖረው ይህም ከቆቃ አንስቶ እስከ ተንዳሆ ያሉት የእርሻ ድርጅቶች የሚጠቀሙበት ነው!

ሶስት እቅዶች አቀርባለሁ !

እቅድ አንድ 1 ቢሊየን ሜትር ኩብ ውሃ ( ወይም አንድ ተጨማሪ አዋሽን ለማቅረብ።)

እቅድ ሁለት 2 ቢለየን ሜትር ኩብ (ወይም ሁለት ሌሎች የአዋሽ ወንዞችን ለማቅረብ።)

እቅድ ሶስት 25 ቢሊየን ሜትር ኩብ (ወይም 25 አዋሾችን ለመፍጠር ናቸው።)

### እቅድ አንድ

አላማው አንድ ቢሊየን ሜትር ኩብ ውሀ በዓመት ለገበሬው ማቅረብ ሲሆን የሚፈጀው 500 ሚሊየን ብር ያህል ይገመታል፡ ለመሥራትም 3 ዓመታት ይፈልጋል።

ሥራው፣

አንደኛ፡ ከደቡብ ኢትዮጵያ በቡታጅራና ሆሳዕና አካባቢ የሚመነጩ ሁለት ትልልቅ ወንዞችን (ብላቴን እና ደጀን) በመገደብ አቅጣጫቸውን አስለውጦ ወደ ዝዋይ ሀይቅ እንዲፈሱ ማድረግ። እነዚህን ወንዞች፡ አሁን አባያ እና ሻላ ሀይቆች ውስጥ እየገቡ ነው። ዘመናዊ እውቀትን ተጠቅመንኢንጂነሮመንቱን በማይጎዳ መልኩ ለሁላችንም ኢትዮጵያዊያኖች ጥቅም ብናውላቸው፡ ማንም ሰው ሀሳቡን የሚቃወም አይመስለኝም።

ሁለተኛ፡ አሁን ያለውን የአዋሽ ወንዝ ዝቋላ ተራራ ሲደርስ አቅጣጫውን በማስለወጥ ወደ ዝዋይ ሀይቅ እንዲፈስ ማድረግ። የአዋሽ ወንዝ፡ በፍጥነት መፍሰሱን፡

ፈረሰኛ መሆኑን ትቶ፡ ረጋ ብሎ፡ አርፎ፡ በረጅም ጉዞው ያግበሰበሰውን ደለል አራግፎ፡ ንፁህ ውሀ ብቻ ይዞ፡ ዝዋይ ሀይቅ እንዲገባ ይደረጋል። ለአዋሽ ማረፊያ የሚሆን ሰፊ ሜዳ በዝቋላ ተራራና በዝዋይ ሀይቅ መሀከል ይገኛል። እነዚህ "Silting Basins" ከሞሉ በኋላ ተራ በተራ በየዓመቱ ወደ እርሻ ማሳ ይለወጣሉ። ይህ ዕቅድ ማንንም ሳይጎዳ ለብዙ ኢትዮጵያውያኖች በጣም ለም የሆኑ የእርሻ ማሳዎች በየአመቱ እያዘጋጀ መስጠት ይሆናል።

ሶስተኛ፡ የዝዋይ ሀይቅ - በደጋውና በቆላው አገራችን መሀል በመገኘቱ ሀይቁም 450 ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት ያለው በመሆኑ፡ 2 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሀን በ 4 ሜትር የከፍታ ጭማሪ ብቻ ለመያዝ ይችላል። ይህ የ 4 ሜትር ጭማሪ በአካባቢው የጎላ ጉዳት አያደርስም። በሀይቁ ዙሪያ የሚገኙ የአትክልት ማሳዎችን ማጥለቅለቁ አይቀርም፡ ሆኖም ከ 200 ሺ ሄክታር ማልማት ጋር ስናነጻጽረዉ የሚደርሰዉ ጉዳት ኢምንት ነው። የምናገኘው ጥቅም እጅግ በጣም ያመዝናል። ዝዋይ ከተማም እንዳይጥለቀለቅ ለማድረግ ዘዴ አለው ።

አራተኛ፡ በዝዋይ ሀይቅ የተከማቸውን ሁለት ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሀ በተፈለገዉ ጊዜ እየለቀቁ፡ ከዚያም ከቆቃ ግድብ በታች ያለውን የአሁን የአዋሽ ወንዝ፡ አስፍቶ አጠናክሮ ለእርሻ ቦታ ለተመረጠው አልይ ደጌ ሜዳ ማድረስ ይቻላል። (አልይ ደጌ ሜዳ ከዝዋይ ሀይቅ 200 ኪሎ ሜትር ይርቃል) አሁንም ይህን ውሃ አለምንም ፓምፕ አዋሽ ሚሊ አሳይታ ከተሞች ድረስ በግራቪቲ ማጓጓዝ ይቻላል። ይህን አንድ ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ በፓምፕ ገፍተን የምንወስድ ቢሆን የአረቦች ነዳጅ በሙሉ ያስፈልገን ነበር። እግዚያብሔር የሰጠን የመሬታችን አቀማመጥ ትልቅ ጸጋ ያለው መሆኑን እዚህ ላይ እንገንዘብ!

<u>ከእቅድ አንድ የምናገኛቸው ጥቅሞች</u>

1. ለ100 ሺህ አባወራዎች ቋሚ ሥራ እንፈጥራለን።

2. እነዚህ 100 ሺህ ምርታማ ገበሬዎች 5 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ከረሀብ ያወጣሉ።

3. ከዚህ 1 ቢሊየን ሜትር ኩብ ውሀ 200 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ሀይል አሁን ባሉት ሶስት ማመንጫ ጣቢያዎቹ በተጨማሪ በጥቂት ወጭ እናገኛለን።

4. የውሀ ላይ መጓጓዣ እስከ 100 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ማግኘት እንችላለን።

5. አሁን በአዋሽ ወንዝ የሚጠቀሙት ወንጂ ሸዋ፣ መተሀራ መሀከለኛ አዋሽ፣ አሚባራ ትንዳሆ ያሉት የእርሻ ማሳዎች እና ሶስቱ የመብራት ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች የመኖር እድሜአቸው ይረጋገጣል። የእርማት እርምጃ ከአሁኑ ካልተወሰደ የቆቃ ሀይቅ በሚቀጥሉት 20 - 30 ዓመታት በደለል ስለሚሞላ እነዚህ ድርጅቶች ይጠፋሉ።

6. የቆቃን ሀይቅ ወደ እርሻ መሬት መለወጥ እንችላለን ሶስት ወንጂን የሚያህሉ ድርጅቶች በመፍጠር ለ30 ሺህ አባወራዎችም የሥራ እድል እንፈጥራለን።

<u>እቅድ ሁለት</u>

2.1 አላማው፡ 2 ቢሊየን ሜትር ኩብ ውሀ ለገበሬው ለማቅረብ ሲሆን የሚፈጀውም 4 ቢሊየን ብር ያህል ይገመታል። ለጥናትና ለኮንስትራክሽን 6 ዓመት ይፈልጋል።

2.2 ሥራው

1. በሰሜን ሸዋ ዞን በ2600 ሜትር ከፍታ የሚገኙ 13 ወንዞችን በመገደብ በክረምት ጊዜ ወደ ውጭ አገር ይዘውት የሚሄዱትን ውሀ በማጠራቀም በአንድ ቦይ መርቶ በአዲስ አበባ በኩል አሳልፎ መተሀራ አጠገብ አዲስ በሚፈጠረው ሀይቅ ማከማቸት።
2. በምሥራቅ ሸዋ የሚገኙትን ከሰምና ቀበና ወንዞችን ገድቦ መተሀራ አካባቢ በሚፈጠረው ሀይቅ ማከመቸት
3. በመተሀራ አካባቢ ሶስት ቢሊየን ሊይዝ የሚችል አዲስ ሀይቅ መሥራት የዚህ ሀይቅ ከፍታው 1040 አካባቢ ይሆናል ።
4. ከዚህ ሀይቅ ለመተሀራ እርሻ ልማትና ለሌሎችም እርሻዎች ውሀ የሚያቀርቡ አዳዲስ ቦዮች በመፈጠር ውሀ ማከፋፈል።

<u>ከእቅድ ሁለት የሚገኙ ጥቅሞች</u>

1. ለ200 ሺህ አባወራዎች ቋሚ ሥራ መፍጠር::
2. እነዚህ 200 ሺህ ምርታማ ገበሬዎች 10 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያኖችን ከረሀብ ያላቅቃሉ::
3. ይህን ውሀ ከሰሜን ሸዋ ወደ መተሀራ ስንወስደው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ወይም አጠገብ ስለምናሳልፈው ለአዲስ አበባ ከተማ የሚያስፈልገውን (ከ100 - 200 ሚሊዮን ሜትር ኩብ ውሀ) ለማቅረብ ያስችለናል:: ከተማው ለዘላለም ከውሀ ችግር ይላቀቃል::
4. ተጨማሪ ጥቅም እንድናገኝ ከፈለግን ይህን ውሀ ከሰበታ እንስቶ የአዲስ አበባ ከተማን <u>ለሁለት ሰንጥቆ ሰገዳዴ የሚደርስ</u> ትልቅ የውሀ ቦይ በመፍጠር: የአዲስ አበባ ህዝብ በጣም ትንሽ በሆነ የትራንስፖርት ወጭ በውሀ ላይ ሲጓጓዝ የሚችልበት መንገድ ልንፈጥርለት እንችላለን:: ርዝመቱም 40 ኪሎ ሜትር ይሆናል::
5. ይህ ውሀ ከሰሜን ሸዋ ከ2500 ሜትር ከፍታ ተነስቶ መተሀራ ድረስ ሲጓዝ 1500 ሜትር ወድቀት ስላለን ከዚህ ውሀና የከፍታ ልዩነት 1000 ሜጋ ዋት የመብራት ኃይል ማመንጨት እንችላለን::
6. ይህን ውሀ ከሰሜን ሸዋ መተሀራ ድረስ በምናጓጉዝበት ጊዜ በቦዩ አካባቢ ለሚገኙ ገበሬዎች ምርታቸውንና ራሳቸውን ለማጓጓዝ የሚረዳ የውሀ ቦይ በውሀ ልክ በመሥራት ከ300 ኪሎ ሜትር ያላነሰ የመጓጓዣ መንገድ ልንፈጥርላቸው እንችላለን::
7. ይህ ውሀ: ከሰሜን ሸዋ ተነስቶ ፍቼ ከተማ ደርሶ: ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ ከቦዩ በምዕራብ በኩል የሚገኘው አገር በጣም ገደልማ ቢሆንም: ከዚህ ቦይ ውሀ በመጥለፍ: ልዩ ልዩ ጠቃሚ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች የሚያመርቱ ማሳዎች በመፍጠር: ገበሬው ሊጠቀምባቸው ይችላል:: የሰሜን ሸዋ ህዝብ ምርታማ ገበሬ እናደርገዋለን:: ዋናው ቁም ነገር በክረምት ወራት የምናገኘውን ውሃ ፈሶ እንዳያልቅ መያዙ ላይ ነው::

<u>እቅድ ሶስት</u>

3.1 አላማው 25 ቢሊየን ሜትር ኪብ ውሀ ለ2.5 ምርታማ ገበሬዎች ለማቅረብ የሚፈጀው ግምት 7 ቢሊየን ብር የኮንስትራክሽን ጊዜ ፯ ዓመታት ::

3.2 ሥራው

1. አባይን ከመርጦ ማርያም በታች ባለው ቦታ በ300 ሜትር ከፍታ መገደብ:: ወንዙን ከፍ አደረግን እንጂ መፍሰሱን አናቆምም::
2. <u>ከተለያዩን እና ተሬ ወንዞች</u> መገናኛ ጀምሮ 50 ኪሎ ሜትር ዋሻ መቆፈርና: የበሽሎ ወንዝ ወደ ምሥራቅ ኢትዮጵያ እንዲፈስ ማድረግ:: አሁን የሚፈሰው ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ ወደ አባይ ነው::
3. በውጫሌ እና በመርሳ ከተሞች አካባቢ ሁለት ግድቦች በሚሌ ወንዝ ላይ በመሥራት 25 ቢሊየን ሜትር ኩብ የበሽሎ ወንዝ ውሀ እንዲጠራቀም ማድረግ::

3.3 የሚሰጠን ጥቅም

1. ለ2.5 ሚሊዮን አባዎራዎች ቋሚ ሥራ እንፈጥራለን
2. እነዚህ 2.5 ሚሊዮን አባዎራዎች 125 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ይመግባሉ ከዚያም ከእኛ ተርፈው ለጎብኚቻችም ሆነ ለሌሎች አፍሪካዊያኖች በቂ ምግብ ልናቀርብ እንችላለን::
3. 800 ኪሎ ሜትር የውሀ ላይ መንገድ ልንፈጥር እንችላለን:: ከጭስ አባይ ተነስተን በውጫሌ ከተማ አድርገን ወልድያ: ቆቦ: አለማታ ከተሞች ደርሰን በክልል አንድ በሚገኘው መሆኒ ከተማ ድረስ ሰዎችና እቃዎችን በትንሽ ዋጋ በመርከብ ላይ ለማጓጓዝ ያስችለናል::
4. 2000ሜጋዋት የኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጨት እንችላለን::

እነዚህን 3 እቅዶች ለማሰብ የቻልኩት ቀጥሎ በተመለከቱት ሁኔታዎች በመመርኮዝ ነው::

1. የአገራችን የኢትዮጵያ ጂኦግራፊ (ከፍታውን፣ ዝቅታውን፣ ሜዳውን፣ ወጣ ገባነቱ)
2. የአገራችን የዝናብ ሁኔታ (ጊዜውና የዝናብ መጠን)
3. በአገራችን ያሉ ወንዞችና ሀይቆች
4. በአገራችን ያለ የተንጣለለ ሰፊ ለም የእርሻ መሬት
5. አገራችን በአለም መቀነት (Equator) አጠገብ በመሆን ዓመቱን ሙሉ በቂ የፀሀይ ሙቀት
6. በአገራችን የሚገኘው በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር የወጣት ሀይል (ከ20 እስከ 40 እድሜ ያለው 18 ሚሊየን ይሆናል::)

እነዚህን ስድስት የተፈጥሮ ፀጋዎች በዘመናዊ እውቀት በማቀናጀት መሆኑን ለማስገንዘብ እወዳለሁ ::

በነዚህ 3 እቅዶች - ወንዞችን መገደብ: የተከማቸውን ውሀ በቦይ አድርጎ ሀይቅ መጨመር - ከዚያም በተፈለገው ጊዜና መጠን እየለቀቁ

እርሻው ቦታ ማድረስ - በእርሻው ማሳ ላይ ዘመናዊ አሰራር በመጠቀም እህል አትክልት ፡ ፍራፍሬ፡ አበባ ማምረት፡ ከብት ማርባት፡ በእውነቱ በጣም ቀላል ሥራ ነዉ:: በኮንስትራክሽኑም ሆነ በእርሻው ሥራ ብዙ ኢትዮጵያውያኖች ጥሩ ልምድ አግኝተዋል፡ ሥራውንም ተክነውታል:: የነዚህ እቅዶች ሥራው በጣም ብዙ ነው እንጂ ለመሥራት ከባድ እና ውስብስብ አይደለም:: ትንሽ ይከብዳል የሚባለው የእንጦጦን ተራራ ሽንቁር ለማለፍ እና ከዝዋይ ሀይቅ፣ ቆቃ ሀይቅ ድረስ ውሀውን ለመውሰድ ከቴራ ድልድይ ውጫሌ ድረስ በነዚህ 3 ቦታዎች በጠቅላላው 80 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ዋሻ (ታናል) የመቆፈር ሥራ ብቻ ነዉ::

በተጨማሪ የነዚህን እቅዶች ስኬታማነት ለማረጋገጥ በክቡር የውሀ ሀብት ልማት ሚኒስትርና በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን ብቻ ሊሠሩ የሚችሉ፡ <u>ሁለት ከባድ ሥራዎች</u> እንዳሉ እዚህ ላይ ለመግለጽ እወዳለሁ:: ከነዚህ ከባድ ሥራዎች የመጀመሪያ፡ ከአገራችን እየፈሰሰ የሚመጣውን ውሀ፡ ገድበን ለራሳችን ጥቅም ለማዋል የምናደርገውን ጥረት፡ የኢትዮጵያ አጎራባች አገሮች እና ሌሎችም በዚህ ውሀ የሚጠቀሙ ሁሉ፡ <u>ምናልባት ሊያነሱ የሚችሉት ተቃውሞ ቢኖር ይህንኑ ማክሸፍ ሲሆን፡</u> ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችንን የሚጠብቃቸው ሁለተኛው ከባድ ሥራ፡ ለዚህ ፕሮጀክት የሚያስፈልገውን <u>መዋዕለ ንዋይ፡</u> ከኢትዮጵያ ህዝብና መንግሥት፡ ከአለም አበዳሪ የፋይናንስ ተቋሞች፡ ከአለም በጎ አድራጊዎች እና እንዲሁም ከለጋሽ ድርጅቶችና ግለሰቦች ማሰባሰብ ናቸው:: በእኔ የመጀመሪያ ግርድፍ ግምት፡ እነዚህን 3 እቅዶች ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ 12 ቢሊየን ብር እና የ12 ዓመት የሥራ ጊዜ ይጠይቃል::ይህ ግምት ውሀን ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ለመውሰድና ለማከማቸት የሚሆን ወጭ ብቻ ነው ::

ይህ ግምት ግዙፍ ኢንቨስትመንት የሚጠይቀውን የ3 ሺህ ሜጋ ዋት ሀይድሮ ፓወር ማመንጫት ወጪ እንዲሁም የእርሻ ማሳዎች ለማዘጋጀት ሰውንም ለማስፈር የሚያስፈልገውን ወጭም አይጨምርም::

ክቡራን ጠቅላይ ሚኒስትራችን እና የውሀ ሀብት ልማት ሚኒስትር እነዚህን ሁለት ችግሮች በብልሀት፡ በእርቆ አስተዋይነትና በጥበብ፡ በታጋሽነት፡ ቢያስወግዱልን፡ አገራችን ውስጥ የሚሠራውን የኮንስትራክሽን እና የእርሻ ሥራ እኛው ኢትዮጵያውያኖች ተባብረን፡ "ሆ" ብለን በመነሳት፡ በ12 ዓመታት ውስጥ በማጠናቀቅ ሠርተን ጨርሰን፡ 300 ሚሊዮን ኩንታል እህል በየዓመቱ በማግኘት ረሀብን ከኢትዮጵያ እንደምናጠፋ ወዲያውም ድህነትን የምንቀርፍ መሆኑን እየገለጽኩ፡ በነዚህ 12 ዓመታት 100 ሺ የሚሆኑ ወጣት ኢትዮጵያውያኖች ከነዚህ እቅዶች ግንባታ የሚያካብቱት የኮንስትራክሽን የሥራ ልምድ፡ ቀሪውን አገራችንን ከጫፍ እስከጫፍ - ብሎም አፍሪካን - ለማልማት የማይበገሩ ጠንካራ የሥራ ብርጌዶች እንዲኖሩን ያስችለናል::

ይህን ሀሳብ በእኔ አቅምና ባለኝ እውቀት አጥንቼ፡ ሀሳቡ ለአገራችን የሚጠቅም መሆኑን አምኜበታለሁ:: የሰነዘርኳቸው ሀሳቦች በሙሉ ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ እንጂ ቅዥት ወይም ህልም እንዳልሆኑ እርግጠኛ ነኝ:: ሆኖም አሁን የማሳስበው ይህን ሀሳብ የበለጠ ለማዘጋጀትና፡ ለማርቀቅ፡ ስለእቅዶቹ የሚነሱትን ለማናቸውም ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ለማዘጋጀት፡ ብሎም በፋይናንስ በኩል፡ ወጭውንና ገቢውን ኢንቨስትመንቱን ለማወቅ፡ በሚከተሉት ስድስት አብይ የሥራ ዘርፎች የጠለቀ ጥናት እንዲደረግ የተመለከተውን በጀት በመመደብ የሚያጠኑ ኢትዮጵያውያኖችን መመደብ ተገቢ እንደሆነ ለማሳሰብ እፈልጋለሁ ::

ይህ ገንዘብ ወጭ የሚሆነው በአገራችን ተቋቁመው ለሚገኙ፡ ከላይ በጠቀስኳቸው ስድስት የሥራ ዘርፎች ጠለቅ ያለ እውቀትና የሥራ ልምድ ላላቸው ኢትዮጵያዊ ኮንሰልታንቶች፡ ግለሰቦች፡ ለድካም ዋጋ የሚከፈል ሲሆን በተጨማሪም ከሆንድ፣ ከእሥራኤል፣ ከቱርክ፣ ከአሜሪካ በዚህ በውሀ ቴክኖሎጂ ለብዙ ዓመታት ያካበቱትን እውቀትና የሥራ ልምድ እንዲያካፍሉን፣ እንዲሰሩልን፣ ስንጠይቅ ለሚያስከፍሉን የሚደረግ ወጭ ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ እወዳለሁ::

ይህን የመጀመሪያ ደረጃ ጥናት በአጭር ጊዜ ጨርሰን ብናቀርብ ፕሮጀክቱን ለመቀጠልም ሆነ ለማቆም ውሳኔ ለመድረስ ይረዳል:: እንቀጥል ከተባለ ከዚህ ጥናት ላይ በመነሳት፡ የእቅዶቹ ዝርዝር ጥናት ሊካሄድ ስለሚችል፡ አሁን የሚደረገው የሠላሳ ሚሊዮን ብር ወጭ፡ ባክኖ የሚቀር ሳይሆን፡ እቅዶቹ በአጭር ጊዜ ሥራ ላይ እንዲውል አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡ ለሚቀጥለው ዝርዝር ጥናት የሚያስፈልገንን ወጭ በዚሁ መጠን እንዲቀንስ ያደርጋል:: በእኔ ግምት እነዚህን እቅዶች ፕሮጀክት ደረጃ ለማድረስ ሥራውንም በዝርዝር ለማጥናት፡ ፕላኖችና የሥራ ዝርዝር፡ የጨረታ ሰነዶች ለማዘጋጀት ኮንስትራክሽኑንም ለመቆጣጠር፡ እስከ 500 ሚሊዮን ብር ይፈጃል:: እላይ የጠቀስኩት የ30 ሚሊየን ብር ወጭ ከዚህ ውስጥ የሚታሰብ ነው::

### ለመጀመሪያ ደረጃ ጥናት የሚያስፈልገው በጀት

| ተ.ቁ | ሥራው | ብር በሚሊዮን |
|---|---|---|
| 1 | ለቅየሳ፣ ለመስመር ምርጫ፣ለዲዛይን ሥራ እና ለሀይደሮሉጂ ጥናት | አምስት |
| 2 | ለግድቦች፣ ለካናል፣ ለእርሻ ቦታ፣ የመጀመሪያ ደረጃ የአፈር ምርመራ ለማድረግ | ሶስት |
| 3 | ከዚህ ፕሮጀክት የመብራት ኃይል ለማግኘት፣ አሁን ያሉትን በማስፋፋት፣ አዲስም በመጨመር፣ሊገኝ የሚችለውን ኃይል ለማጥናት | አራት |
| 4 | 200,000 ሄክታር የእርሻ መሬት ለማልማት: በተገኘው ሁለት ቢሊየን ሜትር ኩብ ውሀ በመጠቀም ልናመርት የምንችለውን አዝርዕት ዓይነቱን፣ ብዛቱን፣ የአሰራር ዘዴውን ጊዜና ወጭውን ለማጥናት | አምስት |
| 5 | የኢንቫይሮመንት ጥናት በአካባቢው ቦይና ግድቦቹ በመሥራታቸው የሚያመጡት ለውጥ እና ስለዚህ የውሀ ቦይ ሁላችንም ኢትዮጵያውያኖች ያለንን እውቀት ለማዳበር ለሚደረግ ወጭ | አምስት |
| 6 | በዚህ ፕሮጀክት ከመሣሪያ ይልቅ: በብዛት የሰው ኃይል የሚሰማራበትንና: የውጭ ምንዛሬም ማስቀረት ባይቻል የሚቀንስበትን መንገድ ፕሮጀክቱ ከምን: እንዴት? ቢሰራ: ለኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ይጠቅማል የሚለውን ለማጥናት: የግብጾችን ፒራሚዶችና የቻይና የግንብ አጥር በሰው ጉልበት ነው የተሰሩት :: | ሶስት |
| 7 | ለአስተዳደር: ለጥናታዊ ጉዞ: ለሌሎችም አስፈላጊ ለሆኑ ልዩ ልዩ ወጭዎች መሸፈኛ | አምስት |
| | በጠቅላላው | ሠላሳ ሚሊየን ብር |

<u>የአባይ ተፋሳሽ አገሮች ስብሰባ</u>

በአለፈው ዓመት ክቡር የውሀ ሀብት ልማት ሚኒስትር የአባይ ተፋሳሽ አገሮች ስለአደረጉት ስብሰባና ስለተደረሰው ስምምነት መግለጫዎች ሰጥተውናል:: ክቡርነታቸው በነዚህ መግለጫዎች ለኢትዮጵያ ህዝብ ያበሰሩት ታላቅ የምሥራች እነዚህ የአባይ ተፋሳሽ አገሮች የዚህን ትልቅ ወንዝ ውሀ ቢጋርዮሽ ለመጠቀም (Equitable Usage) በመስማማት ላይ መሆናቸውን ነው:: በክቡርነታቸው የተጀመረው ይህ ድርድር ለኢትዮጵያ ህዝብ ህልውና እጅግ በጣም ወሳኝ መሆኑን ሁላችንም ልንገነዘበው ይገባናል:: በዚህ ድርድር ውጤት የኢትዮጵያ ህዝብ ከረሀብ - ወደ ጥጋብ - ከድህነት ወደ ሀብታምነት - ከጨለማ ወደ ብርሀን የምንለውጥበት መሆኑን ልናጤነው ይገባናል::

ግብፅና ሱዳን ከባህር በላይ ከፍታቸው ከ600 ሜትር ያነሰ በመሆኑ: በኢኳተር አካባቢም ስለሚገኙ: በጣም ሞቃት የአየር ጠባይ አላቸው:: ከዚህም የተነሳ ከሀይቆቻቸው በሙቀት ምክንያት የሚተነው የውሃ መጠን በጣም ብዙ ነው:: ግብፆች ከሰሩው <u>ናስር ሀይቅ</u> በየዓመቱ 8 ቢሊየን ሜትር ኩብ ውሃ ይተንባቸዋል:: በኢትዮጵያ ደጋ አገር 1500 ሜትር ከፍታ አካባቢ የናስር ሀይቅ ተሰርቶ ቢሆንኖሮ: በትነት የሚጠፋው ውሃ ከሁለት ቢሊየን ሜትር ኩብ አይበልጥም ነበር:: ኢትዮጵያ ለግብጽ ጥቅም የሚውለውን ውሃ በአገሯ ገድባ በሚፈለገው መጠን ብቻ ብትለቅላቸው በዚህ አድራጎቷ ብቻ 6 ቢሊየን ሜትር ኩብ ውሃ ልታገኝ ትችል ነበር:: ድር ቢያብር አንበሳን ያስር እንደሚሉ: ኢትዮጵያ፣ ግብጽ፣ ሱዳን ከተባበሩ የአባይ ውሃ እነዚህን ሶስት አገሮች አጥግቦ: አምበሽብሾ: ለሌሎችም እንደሚተርፍ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነኝ::

እኛ ኢትዮጵያውያን እንደዚህ ከከፋ ረሀብና - ድህነት ለመውጣት ካለን ውሀ 2% ብቻ ለራሳችን ጥቅም አስቀርተን 98% ለሌሎች ብንለቅ የምትሠሩት ትክክል አይደለም ብሎ የሚፈርድብን ሰብአዊ ፍጡር ይኖራል ብዬ በጭራሽ አልጠረጥርም:: ከሁሉም በላይ የሚያስገርመው: ኢትዮጵያውያኖች ከእንቅልፋችን ሳንነቃ - በድህነት፣ በረሀብ ተወጥረን: ተይዘን- በአለም ላይ እንደሌለን ተቆጥረን - እንደኛው ሰው የሆኑት ግብጾች - የነቁ ! የበሉ፣ የተማሩ፣ የተባበሩ ስለሆኑ ብቻ የእኛን ውሀ ለሳውዲዎች ሜትር ኩቡን በ80 ብር ለመሸጥ እየተነጋገሩ ነው:: እስራኤልም ይህን ውሀ በግዥም ሆነ በኃይል ካልወሰደች የወደፊት የመኖር

ህልውናዋ አጠያያቂ ሊሆን ይችላል :: የዚህ ውሀ ምንጭ የሆነችው ኢትዮጵያ በአባይ በኩል ብቻ በየዓመቱ ከሚፈሰው፡ በሜትር ኩብ አንድ ብር እንኳ ቢከፈለን 80 ቢሊዮን ብር በየዓመቱ እናገኛለን:: ጎበዝ! ይህ ገንዘብ በጣም ብዙ ነው:: ቢሰጡን ማስቀመጫም የለንም እኮ! በአሁኑ ጊዜ የመንግሥታችን ጠቅላላ የአመት በጀት 17 ቢሊዮን ብር ብቻ መሆኑን አንርሳ!

በሌላ በኩል አባይ ሲነሣ ግብጽ ይነሣል፣ አባይን ብንነካ ግብጾች ጦርነት ያውጁብናል በሚል ፍርሀት መላው ኢትዮጵያውያን ተውጠናል:: ይህ ፍርሀት በተማሩት በፕሮፌሰሮችና በዶክተሮች ገኖ ይታያል::

ስለግብጽና ስለ አባይ ወንዝ ያለን እውቀት እጅግ የተዛባ ነው:: የምናውቀው ዘፈናችን : አባይ ከዳተኛ ነው ማለት ብቻ ሲሆን : አባይ አፈራችንን ጠራርጎ ወስዶ ለግብጾች ሰጠ፡ ተራቆትን፡ ደኸየን : የሚል እሮሮ እናስተጋባለን:: ይህ የአባይ ደለል : ለግብጾች ፤ ለሱዳኖች ፤ ትልቅ ችግር ፈጣሪያቸው መሆኑን ኢትዮጵያውያን አያውቁም : ግብጾች አሁን ነቅተው ደለላችሁን አስቀሩልን እያሉ ነው:: የናስር ሀይቅን በየጊዜው በደለል እየሞላ የውሀ መቋጠር ችሎታው እየቀነሰ ተቸግረዋል::

ሁለተኛ ስለአባይ የእውቀት ማነስ ጉዳይ አባይን ጣና ላይ ብንገድበው : ልናቆመው እንደምንችል በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ መታመኑ ነው :: ጣና ውስጥ የሚገባው የአባይ ውሀ በጠቅላላው ከአባይ ፍሳሽ ከ10% አይበልጥም : የግልገል አባይ ፍሳሽን ብቻ በጣና ማቆር እንችላለን እንጂ የሌሎችን አንችልም : አባይን አባይ ያደረጉት፡ ቀጥሎ የተመለከቱት ወንዞች ናቸው::

ከጎጃም 1. የግልገል አባይ ወንዝ
2. የአባያ ወንዝ
3. የበለስ ወንዝ
4. የብር ወንዝ
ከወሎ 5. የበሽሎ ወንዝ
ከሸዋ 6. የወልካ ወንዝ
7. የሸንኮራ ወንዝ
8. የጀማ ወንዝ
9. የሙገር ወንዝ
ከወለጋ 10. የዳቡስ ወንዝ
11. የዴዴሳ ወንዝ
12. የፈንጫ ወንዝ
13. የጉደር ወንዝ ናቸው

እነዚህ ሁሉ ጣና ሀይቅ ሊገቡ አይችሉም:: ጣና በ1800 ሜትር ከፍታ ሲገኝ እላይ የጠቀስኳቸው ወንዞች ግን ከ1500 ሜትር በታች ባለው መሬት ላይ የሚፈሱ ናቸው:: ስለዚህ ጣና ላይ ግድብ ብንሠራ አባይን እናቆማለን የሚለው ተረት ሆኖ ይቀራል::

ሌላው እውቀታችንን ማዳበር ያለብን በየጊዜው የነበሩ መሪዎቻችን ስለ አባይ ያደረጉትን ይሆናል::

አፄ ምኒሊክ እንደ ኢ.አ በ1902 አንድ እንሥራ የአባይ ወንዝን ውሀ ከመጠቀሜ በፊት፡ የእንግሊዞችን፣ የሱዳን መንግስትን፡ አስፈቅዳለሁ ወይም፡ እነግራለሁ፡ ወይም እወያያለሁ ብለው የተፈራረሙት ምን እንደሆነ በግልጽ ማጠቅ ይኖርብናል:: አሁንም የእንግሊዝኛ ውና የአማርኛው ቅጂ አይመሳሰሉም ሌላ የውጫሌ ውል ይመስላል::

አፄ ኃይለ ሥላሴ ግብጾችንና ሱዳኖችን አላነጋገርም፡ አልደራደርም፡ ሰላሉ ግብጾች ጥርስ ነክሰውብናል፡ እስካሁን በቁራኛ ዓይን ይመለከቱናል:: ጠንካራ ኢትዮጵያ እንዳትፈጠር ትልቁ ሥራቸው አድርገው ይዘውታል:: ግብጾች የመብራት ኃይል ከኢትዮጵያ ግዙ፣ ውሰዱ ብለው የአፍሪካ ልማት ባንክ ሀላፊዎች ሲጠቁሟቸው ግብጾች የመለሱት ኢትዮጵያ የሚለው ቃል በነሱ መዝገበ ቃላት እንደሌለ አድርገው ነው:: ሁላችንም ብዙ በማንበብ እውቀታችንን ማዳበር ይጠበቅብናል::

የአሁኑ የኢሕአዲግ መንግሥት ስለ አባይ ያለው አቋም ማናቸውንም የአባይ ወንዝ ጥያቄን በኢንተርናሽናል ህጎች መሠረት እንዳኛለን የሚል ነው:: እነዚህ ሕጎች ምን ምን ይሉ ይሆን? እንዲያውስ ኢንተርናሽናል ሕግ አለ ወይ? እኛ በረሀብ እያለቅን ግብጾች የአባይን ውሀ ለሌላ ለመሸጥ ይፈቀድላቸው ይሆን? ወይስ ሁላችንም በጋራ እንድንጠቀም ዘዴ ይፈጥርልናል? ወይም ለሚወስዱት ውሀ የተወሰነ ገንዘብ እንዲከፍሉን ይደርጋል ወይ? በኔ እምነት ኃይል ያለው ኢንተርናሽናል ሕግ አውጥቶ በሥራ ላይ እንድናውለው ያስገድደናል:: እኛ የምንፈልገውን የኢንተርናሽናል ሕግ ነው ብለን፡ በፓርላማችን አፅድቀን፡ የፈለግነውን በመሥራት ጠንካራ የመከላከያ ሠራዊት አቋቁመን መብታችንን ማስከበር አለብን:: ምርጫ የለንም በረሀብ ከማለቅ እንደጀግኖች በጦር ሜዳ በጥይት እንለቅ::

ለነገሩ የአባይ ውሀ : ከግብጽ፣ ከሱዳን፣ ከኢትዮጵያ፣ ፍላጎት ተርፎ ለሌሎችም ጥቅም ይበቃል:: በእውቀት ማነስ ብቻ ሳንተባበር እስከዛሬ ቆይተናል:: አፄ ኃይለ ሥላሴ የፕሬዝዳንት ናስርን ጥያቄ በመቀበል በጣና ላይ ግድብ እንዲሠራ ቢፈቅዱ ኖሮ አሁን የተሠራው የናስር ሀይቅ አይሠራም ነበር:: ግብጾች የናስር ሀይቅ በነሱ አገር በ500 ሜትር ከፍታ

በመሠራቱ የሚከተሉት 6 ችግሮች አሉባቸው::

1. በየዓመቱ 20 ቢሊየን ሜትር ኩብ ውሀ በትነት እና በሲፔጅ ያጣሉ
2. ለእርሻ የሚሆናቸውን 500,000 ሄክታር ለም መሬት ከሱዳን ሳይቀር ሀይቁ ወስዶባቸዋል::
3. ከዚህ እርሻ ቦታ በዓመት 50 ሚሊየን ኩንታል ሰብል በማምረት 25 ሚሊየን ህዝባቸውን እንዳይመግቡ አድርጓቸዋል:: ግብጾች በአሁኑ ጊዜ 4 ቢሊየን ዶላር እያወጡ ምግብ በየዓመቱ ከውጭ ይገዛሉ::
4. ይህ ሀይቅ እድሜው ከ100 ዓመት አይበልጥም ፡ አሁን 40 ዓመት ሆኖታል ከ30 ዓመት በኋላ በደለል ተሞልቶ ውሀ የመያዝ አቅሙ በጣም ይቀንሳል:: በዚያን ጊዜ ግብጾች ምን ይውጣቸዋል? ብልህ ቢሆኑ አሁኑኑ ከኢትዮጵያ ተደራድረው ይህን የአባይ ደለል እንዳንልክ ማድረግ አለባቸው:: በሌላ ቦታም ሀይቅ እንሠራለን ቢሉ የእርሻ ማሳቸውን ያጣሉ የበለጠ ችግር ውስጥ ይገባሉ::
5. ግብጾች በአሁኑ ጊዜ ኢንዱስትሪያቸው ብዙ እያደገ ሲሆን የመብራት ኃይል ፍላጎታቸው በጣም እየጨመረ ይገኛል:: ይህን የመብራት ኃይል በርካሽ ዋጋ ሊያገኙ የሚችሉት ከጎረቤታቸው ከኢትዮጵያ ብቻ ነበር:: አሁን እየሞከሩ ያሉት ከ6000 ኪሎ ሜትር ርቀት ከመሃል አፍሪካ የመብራት ኃይል ለመሳብ ነው:: 30 ቢሊየን ዶላር ያስወጣቸዋል:: ኢትዮጵያ አባይን ከ15 ባላነሱ ቦታዎች በመገደብ በጣም በጣም ብዙ የሆነ MW ማምረት ትችላለች፡ ይህ የመብራት ኃይል ከኢትዮጵያ፣ ከሱዳን፣ ከግብጽ አልፎ ተርፎ ለመላው አፍሪካ እና ለመካከለኛው ምስራቅ የሚበቃ ነው:: ግብጾች እና እኛ ብንተባበር ኖሮ ይህንን የ30 ቢሊየን ዶላር ፕሮጀክት ከ10 ቢሊየን ዶላር በታች እንሠራው ነበር::
6. ማር ሲበዛ ይመራል እንደሚባለው ማናቸውም ነገር በብዛት ከተፈለገው በላይ ቢወሰድ ከሚሰጠው ጥቅም ጉዳቱ ይበልጣል:: ውስኪ፣ቢራ ሲጠጣ ከመጠን በላይ ከሆነ ጉዳቱ ይበልጣል:: የአባይ ውሀም ሱዳኖችና ግብጾች ከሚፈልጉት ሚያጠራቅሙበት በላይ ብዙ በትንሽ ተከታታይ ቀኖች ቢደርስባቸው ካርቱምንም ካይሮንም አጥለቅልቆ በማፍረስ ግብጾች ብዙ ጊዜና ገንዘብ አውጥተው በዘመናዊ መድፎች፣ ታንኮች፣ አውሮፕላኖች የተገነባው ጦር ሠራዊትና አየር ኃይላቸው አንድ ጥይት ሳይተኩስ ከካምፑ ሳይንቀሳቀስ በአባይ ውሀ ተማርኮ ወድሞ ሊጠፋ እንደሚችል መገንዘብ ይኖርባቸዋል::

ባለፉት 10 ዓመታት አባይ ይህን ጥፋት ሊያደርስ እንደሚችል አንዳንድ ምልክቶች ታይተዋል:: በአለፈው ዓመት በመሀል አውሮፓ፣ በራሺያና በቻይና እንዲሁም በአርጀንቲና በ150 ዓመቶች ያልተመዘገበ የዝናብ ብዛት በመዝነቡ ብዙ ጉዳት አድርሷል:: እንደዚሁም በሞዛምቢክ የደረሰው የአገር መጥለቅለቅ የሚረሳ አይደለም::

ሆኖም ግብጾችና ሱዳኖች ይህ በውሃ ተጠራርጎ መጥፋት እንዳለ ተገንዝበው ከዚህ አርማ-ጌዶምን ለመትረፍ ከኢትዮጵያ ጋር ተባብረው መሥራት ይኖርባቸዋል::

ኢትዮጵያ የዚህ ችግር መፍቻ ዘዴው አለምንም ጥርጥር ያላት አገር ነች::

ባጭሩ ኢትዮጵያ አባይን በአገሯ ብትገድብ ከሁሉም በላይ ተጠቃሚዎች ግብጾችና ሱዳኖች ይሆናሉ:: እስካሁን ሁላችንም ከእውቀት ማነስ የተነሳ ሳንተባበር ራሳችንን እየጎዳን እንገኛለን::
እኔ የምመኘው የማልመው ይህ ትብብር በጣም ዳብሮ ግብጽ፣ሱዳን፣ ኢትዮጵያ ተዋህደው በዘመኑ አጠራር ግብጽ ክልል አንድ፣ ሱዳን ክልል ሁለት ፣ ኢትዮጵያ ክልል ሦስት፣ ሱማሌ ክልል አራት ፣ ኬንያና ኡጋንዳ ክልል አምስት እንዲሆኑ ነው:: ብንዋሀድ ሁላችንም እንጠቀማለን:: ክቡር የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር በኔፖድ በአፍሪካ ህብረት የያዙት አቋም በጣም የሚደገፍ ነው:: አሜሪካውያኖች በአባይ ወንዝ ጥናታቸው ኢትዮጵያ የአባይን ውሀ ለመስኖ ልትጠቀምበት አትችልም ብለው በመደምደማቸው ብዙ ጎድተውናል:: የመከራከሪያ ነጥብ አሳጥተውናል:: በምሥራቅ ኢትዮጵያ ብዙ ሚሊየን ሄክታር መሬት በመስኖ ሊለማ የሚችል አለን ፡ አሜሪካውያኖች በመስኖ ሊለማ የሚችል በቂ መሬት ኢትዮጵያ የላትም ብለው እንዴት ያውጃሉ:: ለዚህ ጥፋታቸው ካሣ መጠየቅ አለብን:: ሀብታምም ደጎችም ስለሆኑ ይህን ካሣ ይከፍላሉ::

ይህን ሀሳብ እዚህ ላይ ያነሳሁት የክቡር የውሀ ልማት ሚኒስትር ድርድር ለኢትዮጵያችን ምን ያህል ጥቅም ሊያስገኝ እንደሚችል ለመግለጽ ሲሆን - ለክቡርነታቸው ጤንነትና እድሜ እየጸለይን - የጀመሩትን የአባይ ፍሳሽ አገሮች ድርድር በመልካም ሁኔታ እንዲቋጩልን ያልተቆጠበ ጥረትና - ድጋፍ እንድናደርግላቸው በዚህ

ኢጋጣሚ አሳስባለሁ:: ይህን ሁሉ የጻፍኩት ከረሀብና ከድህነት እንድንላቀቅ ከፈለግን ስለ አባይ ያለንን እውቀት በጣም ማዳበር እንዳለብን ለማስገንዘብ ነው::

## የመስከረም 1/1994 የኒወርክ ፍንዳታ

በመስከረም 1/94 በኒውዮርክ በደረሰው ፍንዳታ ምክንያት ድህነት - መሀይምነት ከአለም ካልጠፋ: በስተቀር ሀብታም ሆኖ መኖር የማይቻል መሆኑን የአሜሪካና የበለጸጉ የአውሮፓ መሪዎች ቁልጭ አድርገው እንዲገነዘቡት ምክንያት ሆኗል::
ክብር ጠቅላይ ሚኒስትራችንም በሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ ተገኝተው በአደረጉት ገለፃ ከዚች ዓለም ሽብር ፈጣሪዎችን ለማጥፋት በመጀመሪያ ደረጃ ረሀብንና ድህነትን ማጥፋት አስፈላጊ መሆኑን ገልጸው ነበር::
ከዚህ ግንዛቤ በመነሳት በአሁኑ ጊዜ የአለም ባንክ በየዓመቱ 50 ቢሊዮን ዶላር ለድሀ አገሮች ለልማት ሥራ እንዲያውሉት ብድር ለመስጠት እቅድ አውጥቷል :: አገራችን ከነዚህ ድሀ አገሮች አንዷ ሆና በመገኘቷ በዚህ ገንዘብ ለመጠቀም: የምንችልበት ዕድል ሊፈጠርልን እንደሚችል እተማመናለሁ የአለም ህዝብ እነዚህን እቅዶች በሥራ እንድንተረጉም ይፈቀድልን እንጂ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ማግኘት ከባድ አይሆንም ::

## ማጠቃለያ

የዛሬ 10 አመት ግንቦት 20/83 የኢህአዴግ ጦር አዲስ አበባ ገብቶ ከተማውን ሲቆጣጠር ጓደኞቹና እኔ የተሰማን ደስታ ወሰን አልነበረውም:: ሁለተኛ የተወለድንበት ቀን አድርገን ቆጥረነዋል:: ለምን ብንባል የደርግ መንግሥት <u>የማሰብ! የመጻፍ! የመናገር! የመዘዋወር</u> መብቶቻችን ገፎን ስለነበር: በዚያች ቀን እነዚህን መብቶች እንደምንጎናጸፍ በማመናችን ነው::

አሁንም ይህን ፕሮጀክት <u>ለማሰብ እና ለመቅረጽ</u> የቻልኩት: በውሃ ሀብት ልማት ሚኒስቴር የሐይድሮሎጂ ዲፓርትመንት:የወንዞቹን የአመት ፍሳሽ የ30 ዓመት ሪኮርድ: እንዲሁም የካርታ ድርጅት የነዚህን ቦታዎች ካርታ (እንደ ለሀምሳ ሺህ በሆነ ስኬል) ሊሸጥልኝ በመቻሉ ነው:: እነዚህን ሁለት የመረጃ ሰነዶች መንግሥት እንደአሁኑ እንዲሰራጩ ባይፈቅድ ኖሮ: ይህን ፕሮጀክት በቁሜም በህልሜም በጭራሽ ላስበው አልችልም ነበር:: አሁንም "<u>ነፃ ፕሬስ</u> ! <u>ነፃ ሀሳብ! ነፃ መንፈስ</u>" በአገራችን ብልጭ ብልጭ በማለት ላይ ስለሆነ! ዘመኑም "<u>የእውቀት ዘመን በመሆኑ</u>" በዚህ ባቀረብኩት ሀሳብ ማናቸውም ኢትዮጵያዊ ይህን ጽሁፍ አንብቦ እቅዶችን ሰነጣጥቆ - በትኖ - አዳብሮ - ጥሎ አንስቶ ጠቀሜታውንና ጉዳቱን እንድንወያይበት ጥሪዬን አቀርባለሁ::

ረሀብን! ችግርን! ድህነትን ከኢትዮጵያችን ለማጥፋት የእሳት አደጋ መኪናዎችን: ሰብስበን ውሀቸውን ብንረጭ - ወይንም 60 ሚሊዮን የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ - ሁላችንም ተሰብስበን እፍ ብንል በጭራሽ አይጠፋም:: ገና ብዙ ያደክሙናል: <u>**በጥልቀት ማሰብ! በዘዴ መሥራት! በጥንቃቄ መራመድ**</u>: ይጠበቅብናል:: በተአምር ካልሆነ በስተቀር (እንደሻለቃ ኃይሌ ገ/ሥላሴ) በጡንቻ: በጉልበት: በመሮጥ: ሀብት ማፍራት አይቻልም:: ከችግር! ከድህነት ለመላቀቅ መማማር: <u>መማር : አሁንም መማር! ማሰብ ማሰብ አሁንም ማሰብ መሥራት መሥራት አሁንም ምርታማ ሆኖ</u> መሥራት ያስፈልጋል::

በአሁኑ ጊዜ መንግሥት መላው ኢትዮጵያውያን ከተዘፈቅንበት የድህነት ማጥ ለማውጣት: ብሎም በአገራችን ያለውን የረሀብና የበሽታን ችግሮች ለማቃለል ቀንና ሌሊት አለማቋረጥ ለሚያደርገው ጥረት: እነዚህ እቅዶች ተጨባጭ ውጤት ይሰጣሉ ብዬ በማመን እንድትመለከቱልኝ በአክብሮት እየለመንሁ ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ! የያንዳንዱን እቅድ ፕላኑንም አያይዣለሁ::

መግለጫዬን የሚከተሉትን አስተያየቶች በመስጠት ለመደምደም እወዳለሁ ::

ከኢትዮጵያችን ረሀብን ድህነትን ለማጥፋት ትንሽ ትልቅ ሳይባል ሁላችንም በሚከተሉት ጥያቄዎች የጠለቀ ግንዛቤ እንዲኖረን: በየቀበሌው: በየመንደሩ: በየቤተክርስቲያኑ በየመስጊዱ: በተገኘው ቦታ: ሁሉ ተሰብስበን: <u>ውይይት ማድረግ</u> ይገባናል::

እነዚህ ውይይቶች ለችግራችን መፍትሄ የሚሆኑ ሀሳቦችን ለማፍለቅ እንደሚችሉ ጥርጥር የለኝም ::

## የውይይት አርዕስቶች

1. የፀሀይ ሙቀትን: የምንተነፍሰውን አየር: ማነው የሚቆጣጠረው? ባለቤታቸው ማነው? ነገ ጉልበት ያለው ወይም እውቀት ያለው: ለዚህ የፀሀይ ሀይል ለአየሩም: ግብር እምጡ ቢለንስ? ወይስ የፀሀይ ሙቀቱን ቢቀንስብንስ: አየሩን ቢበክልብንስ? በአሁኑ ጊዜ በሜክሲኮ ከተማ እና በኢንዶኔዥያ ያሉት ሰዎች መተንፈስ እየተቸገሩ ነው::

አሜሪካውያኖች የኪዮቶ ውሉታ አንፈርምም፣ አናፀድቅም፣ አንቀበልም፣ ያሉበት ምክንያት ምንድን ነው:: የኪዮታ ውሉታ ምንድን ነው ?

2. በቤታችን ጣሪያ በትንሸዋ ግቢያችን ውስጥ የማዘንበው ውሀ የማን ነው? ይህን ውሀ ሰብስበን አጠራቀመን ብንጠቀምበት የውሀ ክፍል ዝም ብሎ ያየናል ወይ ? (ፕሮፌሰር ንጉሴ ተበጀ ይህንን እያደረጉ ነው::) ከውሀ ክፍል ምን አጨቃጫቀን ፤ እያንዳንዳችን ውሀችንን አጠራቅመን ለምን አንይዝም፣ አዋሽ ከማን የገበሬ ቀበሌ ተነስቶ ወደ ማን ቀበሌ ይሄዳል ? አዋሽ የማን ነው ? እንዲሁም አባይ፣ ዋቢሸበሌ፣ አሞ የማን ናቸው? ጎረቤት አገሮች ምን አገባቸው? ውሀው የኛ ወይስ የነሱ? አፄ ሚኒሊክ በ1902 እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ከሱዳንና ከእንግሊዝ የተፈራረሙት ምንድን ነው ? ሌላ የውጫሌ ውል የተደበቀ ይወጣ ይሆን! አፄ ኃይለሥላሴ እና ፕሬዝዳንት ጀማል ናስር ምን ሞክረዋል? ብዙ የምንማረው ስላለ መወያየት ይጠቅማል::

3. የመሬት ይዞታችን እንዴት ቢሆን ለሁላችንም በአጠቃላይ ለመላው፡ ዓለም ይጠቅማል? ወይም መሬት ይሸጥ አይሸጥ፣ ውሀ ይሸጥ አይሸጥ፣ የፀሃይ ሙቀት ይሸጥ አይሸጥ፣ ብዙ የሚያነጋግሩን ስለሆኑ እንወያይባቸው::

4. ዲሞክራቲክ መንግሥት ምን ማለት ነው? ከሰሙት አገሮች እንደሚመጣው የእርዳታ እህል፡ በስጦታ የሚገኝ፡ ተሸክመነው የምንሄድ፡ ወይስ መብትና ግዴታ? ይህም እንገብጋቢ ጥያቄ መሆኑን በመረዳት የዲሞክራሲ ዕንስ ሀሳቦችን ተሰብስበን መወያየት ይኖርብናል::

5. ምርታማ ገበሬ እንዴት ሊገኝ ይችላል? ኢትዮጵያችን 10 ሚሊዮን የገበሬ አባወራዎች የተራበበት አገር የሆነችው ለምንድን ነው ?

የነዚህ ጥያቄዎች፡ መልስ ለማግኘት የምንችለው ተሰብስበን ስንመክር ነው፡ መፍትሄው ቀልጭ ብሎ ይወጣልናል:: ስለዚህ የውይይት መድረክ በየቦታው በመክፈት፡ እንጨቃጨቅ፡ ነገር ሊገፋ የሚችለው በጭቅጭቅ እንጂ ከርከርን ፈርቶ በመደበቅ አይደለም::

አመሰግናለሁ::

አባሪ
ይህን ሰንጠረዥ እንመልከት

| | | ጤፍ እና ዘንጋዳ | አበባ | ጥጥ | ስኳር | አትክልት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ለአንድ ሄክታር ለማምረት የሚያስፈልገው የውሃ ብዛት በሺህ ሜትር ኩብ | 8 | 12 | 18 | 25 | 11 |
| 2 | እርሻ ቦታ የደረሰው የውሀ ብዛት 1 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ቢሆን ልናገኝ የምንችለው ምርት በሚሊዮን ኩንታል | 12 | 8 | 1.6 | 4 | 1 |
| 3 | እርሻ ቦታ የደረሰው የውሃ ብዛት 2 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ቢሆን ልናገኝ የምንችለው ምርት በሚሊዮን ኩንታል | 24 | 16 | 3.2 | 8 | 2 |
| 4 | እርሻ ቦታ የደረሰው የውሃ ብዛት 25 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ቢሆን ልናገኝ የምንችለው ምርት በሚሊዮን ኩንታል | 300 | 200 | 40 | 100 | 25 |
| 5 | እርሻ ቦታ የደረሰው የውሃ ብዛት 1 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ቢሆን ቋሚ ሥራ ልንሰጣቸው የምንችለው የአባወራዎች ብዛት | 100,000 አባወራዎች | | | | |
| 6 | እርሻ ቦታ የደረሰው የውሃ ብዛት 2 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ቢሆን ቋሚ ሥራ ልንሰጣቸው የምንችለው የአባወራዎች ብዛት | 200,000 አባወራዎች | | | | |
| 7 | እርሻ ቦታ የደረሰው የውሃ ብዛት 25 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ቢሆን ቋሚ ሥራ ልንሰጣቸው የምንችለው የአባወራዎች ብዛት | 2.5 ሚሊዮን አባወራዎች | | | | |
| 8 | እርሻ ቦታ የደረሰው የውሃ ብዛት 1 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ቢሆን ከረሀብ ልናላቅቀው የምንችለው የሰው ብዛት | 5 ሚሊዮን | | | | |
| 9 | እርሻ ቦታ የደረሰው የውሃ ብዛት 2 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ቢሆን ከረሀብ ልናላቅቀው የምንችለው የሰው ብዛት | 10 ሚሊዮን | | | | |
| 10 | እርሻ ቦታ የደረሰው የውሃ ብዛት 25 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ቢሆን ከረሀብ ልናላቅቀው የምንችለው የሰው ብዛት | 125 ሚሊዮን | | | | |

ማጠቃለያ

እነዚህ ሶስት እቅዶች የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደሚከተለው ያበለጽጉታል

| ተ.ቁ | እቅድ | ለመስኖ ሥራ ልናቀርብ የምንችለው<br>በቢሊዮን ሜ.ኩ | ተቀጣሪ አባወራ<br>ብዛት | ሊታረስ የሚችለው<br>በሄክታር | ሊገኝ የሚችለው ምርት<br>በሚሊዮን ኩንታል | ይህ ምርት ሊመገብ የሚችለው ሕዝብ ብዛት<br>በሚሊዮን | ሊገኝ የሚችለው የኤሌክትሪክ ኃይል<br>በሜጋ ዋት | በሀገር ውስጥ የመስኖ ውኃ መንገድ<br>በኪሎሜትር | የፕሮጀክቱ ሥራ ዋጋ ግምት<br>በብር | ለጥናትና ለኮንስትራክሽን የሚፈጀው ጊዜ<br>በዓመት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዋሽ ብላቴንንና ዲጆ ወንዝን ጠልፎ ወደ ዝዋይ ሀይቅ እንዲፈሱ ማድረግ | አንድ | 100,000 | 200,000 | 10 | 5 | 200 | ·50 | 500 ሚሊዮን | 3 |
| 2 | በሰሜን ሸዋ የሚኙትን 12 ወንዛችንና በምሥራቅ ሸዋ የሚገኙትን የቀበና እና የከሰም ወንዞችን በመጥለፍ መተሃራ አካባቢ ወዳለው አዲሱ ሀይቅ እንዲፈሱ ማድረግ | ሁለት | 200,000 | 400,000 | 20 | 10 | 1000 | 200 | 4 ቢሊዮን | 6 |
| 3 | በመሀል ኢትዮጵያ የሚገኘውን የበሽሎ ወንዝን ጠልፎ በመርሳና በውጫሌ ከተሞች መካከል ወደሚገኘው አዲስ ሀይቅ እንዲፈስ ማድረግ | ሃያ አምስት | 2.5 ሚሊዮን | 5,000,000 | 250 | 125 | 2000 | 800 | 7 ቢሊዮን | 12 |

THIS BULLETIN AND OTHER PYUBLICATIONS OF EEA ARE SPONSORED BY FREIDRICH EBERT STIFTUNG OF GERMANY (FES), EMBASSIES OF UK, SWEDEN, NORWAY AND THE AFRICAN CAPACITY BUILDING FOUNDATION (ACBF)

***Just pay less than 20 Birr and You will have Your 'Economic Focus' for the whole year !!***

*Make sure to look for your latest 'Economic Focus' at:*



- African Bookshop
- Book Center at AAU
- The Book World
- Ghion Hotels
- MEGA Bookshops
- Meseret Nega Stationery
- Alemu Shop (Near ECA)
- Hadia Supermarket
- Twins Supermarket
- Seyoum Shop (Near Kazanchis TOTAL)
- Hill-Belt Restaurant
- Semien Hotel
- Universal Bookshop

**PRICE BIRR 3.50**